አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር

# በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ

በ

ተመስገን በየነ አበጋዝ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ-ግብር ለኤም.ኤ.ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር

# በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ


በ

ተመስገን በየነ አበጋዝ

አማካሪ

አቶ ዘሪሁን አስፋው

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት


ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ-ግብር ለኤም.ኤ.ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሃ-ግብር

# በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ

በ

ተመስገን በየነ አበጋዝ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ — ፊርማ

ዘሪሁን ኪስለው ........................ ........................

ፈታኝ

........................ ........................

## ምስጋና

ይህ ጥናት እውን ይሆን ዘንድ ከትልመ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍፃሜ ድረስ ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በመጠቆም፣ የጥናቱን ይዘት በማስተካከል፣ በማረምና ገንቢ ሃሳቦችን በመለገስ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ አቶ ዘሪሁን አስፋውን አመሰግናለሁ፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቅንነትና በፍቃደኛነት ለሰጡኝ ለአውራ መረጃ አቀባዮቼ ለመሪ ጌታ ካሳ መንገሻ፣ ለመሪ ጌታ መስፍን ገብሬ፣ ለመሪ ጌታ(የኔታ) ጌታቸር ሸዋንግዛው፣ ለባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ እና ጌታነህ ታደሰ፤ እንዲሁም ለንዑስ መረጃ አቀባዮቼ ምስጋናዬ ባሉበት ይድረሳቸው፡፡

ከጥናቱ ጅምር እስከ ፍፃሜ ከጎኔ ላልተለየው የባህል ሐኪም አባቴ ደብተራ በየነ አበጋዝ፤ ለመረጃ አቀባዬ ለአቶ አሰፋ ዳኜ፤ የግሼ ወረዳ አስተዳደር ዋና ኃላፊ ለአቶ አወቀ ዘነበ፤ እንዲሁም የግሼና አካባቢው እድር አባልና አስተባባሪ ለአቶ ካሳ ጥላሁን እና ለአቶ በቀለ ሞላ ላደረጋችሁልኝ ትብብር እግዚአብሔር ውለታችሁን ይክፈላችሁ፡፡

ሁለተኛ(ኤም.ኤ) ዲግሪዬን ስማር ሙሉ የትምህርት ወጭዬን የሸፈነልኝን አክሱም ዩኒቨርሲቲን እና ለዚህ ጥናት ማስጀመሪያ የሚሆን ገንዘብ የመደበልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡

በሕይወቴ ልዩ ውለታ ለዋለልኝ እና ከአምላክ ቀጥሎ ለኔነቴ ቤዛ ለሆነኝ ጓደኛዬ ሳምሶን አየለ ከማንም በላይ ላቅ ያለ ምስጋናዬ ባለበት ይድረሰው፡፡ የኤም.ኤ ትምህርቴን ስማር በሐሳብና በገንዘብ ድጋፍ ላደረገችልኝና ላበረታታችኝ ፀሐይ አበራ እንዲሁም ዋቢ መጻህፍትን በመጠቆምና በማፈላለግ ረገድ እገዛና ቀና ትብብራቸው ያልተለየኝን የሙዚየም ላይብረሪ ሰራተኞችን አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረምሻ የጥናቱን ረቂቅ በማረምና ጠቃሚ ሃሳቦችን በመለገስ ትብብር ላደረጉልኝ የዩኒቨርሲቲ የስራ ባልደረቦቼ ለአቶ ደምሴ አለሙ እና ለአቶ ዮሐንስ ባሻዬ፤ ለክፍል ጓደኛዬ ለተስፋዬ ሞላ፣ መ/ር ሐብታሙ አቃናው፣ እስክንድር ተኮላ እንዲሁም ረቂቁን በመፃፍ ትብብር ላደረገችልኝ እርማዬን አደራ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# የአማራ ክልል ካርታ



N.Gondar
Addi Arkay
Beyeda
Debark
Sanja
Debat
Janamora
Metema
Lay Armacho
Wegera
Chilga
Belesa
Dembia
Gondar Zuria
Quara
Aleta
Lake Tana
Wag Hemra
Zikuala
Sekota
Dehana
Kemekem
Ebenat
Fogera
Farta
Lay Gayint
Dera
Este
T/Gayint
Bahir Dar
Achefer
S.Gondar
Simada
N.Wello
Bugna
Gidan
Kobo
Meket
Guba Lafto
Wadla
Dawuntna Delant
Habru
Ambasel
Tenta
Mekdela
Kutaber
Tehuledere
Dessie
Dessie Zuria
Werebabu
Bati
Kalu
Sayint
Legambo
Debresina
S.Wello
Were Ilu
Albuko
Wegde
Kelala
Jama
C/Gola
G/Rabel
Antsokiya Efrata
Oromia
Artuma Fursina Jile
W.Gojam
Merawi
Adet
Dangela
F/Lekoma
Bana
Sekela
Kuarit
Agew Awi
Guangua
Ankesha
Jabi Tehnan
Dega Damot
Dembecha
Bure Wemberma
Machakel
Hulet Ej Enese
Goncha Siso Enese
Enbise Sar Midir
Enarj Enawga
Enemay
Shebel Berenta
Guzamn
Debay Telatgen
East Gojam
Awabel
Dejen
Baso Liben
Weremo Wajtuna Mida
Gera Midima Keya Gebriel
M/Midr
Lay Bet
Tach Bet
N.Shewa
Moretna Jiru
M/Mezezo
Kewet
Siyadebrina Wayu
Ensaro
D/Berhan
Angolela Asagrt
Ankober
Hegere Mamamna
Berehet
Minjama Shenkora
0
35
70
140
210
280 Km

# የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ካርታ






## መግለጫ

- የዞን ወሰን
- የወረዳ ወሰን
- የገበሬ ማኅበር ወሰን
- የበጋ መኪና መንገድ
- የማይደርቅ ወንዝ
- የወረዳ ዋና ከተማ
- ትምህርት ቤት
- ክሊኒክ
- ወፍጮ ቤት

| ኮድ | ገበሬ ማኅበር | ኮድ | ገበሬ ማኅበር |
|---|---|---|---|
| 01 | ጫጩራ | 14 | ሞጌና አይመተር |
| 02 | ጠበልና እዴ | 15 | ጎልታ |
| 03 | ጎጅርና መስቀል ደብር | 16 | አልጌና ወንተላ |
| 04 | ግራር አምባ | 17 | ሴት አምባ |
| 05 | አደስ አምባ | 18 | ደራት |
| 06 | ቀይ አምባ | 19 | ሴቶች ዋሻ |
| 07 | ግጅማ | 20 | ወፍለቆ |
| 08 | እስናፊት ተገን | 21 | ቆደጽ |
| 09 | አራጣ | 22 | ልጋ |
| 10 | ወጠሬ | 23 | መስክ አምባ |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ምን እንደሚመስሉ ከልማድ፣ ከእምነትና ከባህል አኳያ መመርመር ነው።

ጥናቱ፤ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች መግለጽ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶችን መጠቆም፤ የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችንና የባህል ህክምና ምስጢራዊነትን ማሳወቅ፣ በባህል ህክምና ለመድኃኒት አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን መለየት እና ለግብዓቶቹ መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ቀናት ትዕምራታዊ ፋይዳ ማመልከት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከአውራና ከንዑስ የባህል ሐኪሞች፣ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎችና ከባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች ተሰብስበዋል። እነዚህ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በታላሚ ቡድናዊ ውይይት በመጠቀም በማስታወሻ፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ተሰብስበዋል። ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በምድብ በምድብ ተደራጅተው በገላጭና በተንታኝ የምርምር ስልት ተተንትነው ቀርበዋል።

በትንታኔው መሰረት በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በዋናነት በሽታን የመለያ ዘዴዎቻቸው እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጅካዊ እና የህሙማንን ማኅበራዊ ሁኔታ በማጤን (በመጠየቅ) ምርመራ እንደሚያካሂዱና በሽታን እንደሚለዩ ጥናቱ አሳይቷል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለመድኃኒት አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን በአብዛኛው ከእፀዋት ጥቂቱን ደግሞ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፍሳት እንደሚሰበስቡ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል። የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት ልዩነት ምክንያት `የባህል ሐኪሞቱ ግላዊ እውቀት፣ ጥበቡን እንዳገኙበት ደረጃ፣ ለመድኃኒት የሚውሉ ግብዓት መገኛ ቦታ፤ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል። የመድኃኒት ቅመማ ሂደቱም፣ በማድረቅ፣ በመውቀጥ፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍና በመቀቀል ይተገበራል። በዚህ ሁኔታ የተቀመሙ መድኃኒቶች ደግሞ በተለያየ መልክ ተመጥነው በሚሸተት፣ በሚቀባ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታኘክ፣ በሚጠጣ፣ በሚዋጥ፣ በሚቀበር እና በመሳሰሉት መልኮች እንደሚሰጡ ጥናቱ አሳይቷል።

በግሼ ወረዳ የሚገኙ፤ አብዛኞቹ የባህል ሐኪሞች ከእምነት ተቋም የወጡ መሆናቸው፣ ለህሙማን ስነልቡናዊ ድጋፍ ማድረጋቸው፣ በዝቅተኛ ወጭ አገልግሎት መስጠታቸው እና ህሙማን በህክምናው እንፈወሳለን የሚል ጽኑ እምነት ማሳደራቸው የህክምና ዘርፉን ተመራጭ አድርጎታል። ይሁን እንጅ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ከበሽታ መለያ ዘዴያቸው፣ ከመድኃኒት ቅመማ፣ ምጣኔና አሰጣጥ ስልታቸው ጋር በተያያዘ በህሙማን ላይ ጉዳት እንደሚያደርሱ በጥናቱ ታውቋል።

ይህን የባህል ህክምና ለማዘመን፤ በዘርፍ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የዘመናዊ ህክምና አስተማማኝ አጋር እንዲሆን ለማድረግ፤ የባህላዊና የዘመናዊ ህክምና ባለሙዎች ተቀራርበው ቢወያዩና ቢመካከሩ፣ በጋራ የሚሰሩበትን አጋጣሚ ቢያመቻቹ የተሻለ መሆኑን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል።

# የአርዕስት ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................ I

የአማራ ክልል ካርታ ........................................ II

የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ካርት ........................................ III

የግሼ ወረዳ ካርታ ........................................ IV

አጠቃሎ ........................................ V

የአርዕስት ማውጫ ........................................ VI

ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 2

1.2 የጥናቱ ዳራ ........................................ 3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........................................ 3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታዎች ........................................ 4

1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................ 4

1.6 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................ 5

1.6.1 ተሣትፏዊ ምልከታ ........................................ 5

1.6.2 ዕሞናዊ ምልከታ ........................................ 6

1.6.3 ቃለ መጠይቅ ........................................ 6

1.6.4 ታላሚ የቡድን ውይይት ........................................ 7

1.7 የጥናቱ ዘዴ ........................................ 7

1.8 የመስክ ተመክሮ ........................................ 7

1.8.1 ከመስክ በፊት ........................................ 8

1.8.2 መስክ ላይ ........................................ 8

1.8.3 ከመስክ መልስ ........................................ 9

1.9 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 9

1.10 በጥናቱ ሂደት ላጋጠሙ ችግሮች የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................................ 9

1.11 በጥናቱ ሂደት የተገኙ ጠቃሚ ልምዶች ........................................ 10

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 11

የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብና አካባቢያዊ ዳራ ........................................ 11

2.1 የግሼ አመሰራረትና የህዝቡ አኗኗር አጭር ቅኝት ........................................ 11

2.2 የግሼ ወረዳ መልክዓ ምድር፣ቋንቋና ሃይማኖት ........................................ 12
2.2.1 የግሼ ወረዳ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ ........................................ 12
2.2.2 የግሼ ወረዳ ህዝብ ቋንቋና ሃይማኖት ........................................ 14
2.3 የወረዳው የትምህርትና የጤና ሁኔታ ........................................ 15
2.3.1 ትምህርት ........................................ 15
2.3.2 ጤና ........................................ 15
2.4 የህዝቡ መተዳደሪያ ........................................ 16
ምዕራፍ ሶስት ........................................ 17
ክለሳ ድርሣን ........................................ 17
3.1 ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ........................................ 17
3.1.1 የባህላዊ ህክምና ፅንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ........................................ 17
3.1.2 የባህላዊ መድኃኒት ብያኔ እና ፅንሰ ሃሣብ ........................................ 19
3.1.3 የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ምንነትና ምድብ ........................................ 21
3.1.3.1 የባህል ህክምና ባለሙያዎች ምንነት ........................................ 21
3.1.3.2 የባህል ሐኪሞች ምድብ ........................................ 22
3.1.4 የባህል ህክምና አይነቶች እና የልዩ ሙያተኞች ምድብ ........................................ 24
3.1.4.1 ከእፅ መድኃኒት ተቀምሞ የሚሰጥ ህክምና ........................................ 24
3.1.4.2 በወጌሻ የሚሰጥ ህክምና ........................................ 24
3.1.4.3 በመንፈሳዊ ኃይል የሚሰጥ ህክምና ........................................ 25
3.1.4.4 በቅይጥ ቴክኒካዊ እውቀት የሚሰጥ ህክምና ........................................ 25
3.1.5 በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች ........................................ 25
3.1.5.1 እይታዊ ምርመራ ........................................ 26
3.1.5.2 ክሊኒካዊ ምርመራ ........................................ 26
3.1.5.3 ባዮሎጂካዊ ምርመራ ........................................ 27
3.1.5.4 የህሙማንን ማኅበራዊ ሁኔታ በማጤን ........................................ 27
3.1.6 የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ........................................ 27
3.1.7 የባህላዊ ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶች ........................................ 29
3.1.8 የባህላዊ ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት ........................................ 29
3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................ 30
3.2.1. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ........................................ 30

3.2.2 ለስነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች.......................32
3.2.3 ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናቶች...........34
3.2.4 ለታሪክ ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት.............................................36
3.2.5 በውጭ አገር የታተሙ የፒ.ኤች.ዲ ጥናቶች ..................................36
3.2.6 በአለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ የቀረቡ ጥናቶች ቅኝት.......................38
ምዕራፍ አራት..........................................................................................40
በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ.....................40
4.1 በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች ................................................0
4.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶችና አሰባሰብ ..........................46
4.2.1 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶች ......................................46
4.2.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት አሰባሰብ እና ስርዓተ ገቢር .......................................................................................48
4.2.2.1 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት አሰባሰብ ................48
4.2.2.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር....................................................................................50
4.2.3 ለባህላዊ መድኃኒት መቁረጫና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እና ቀናት ትዕምርታዊነት ...................................................................52
4.3 የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ..........................................................57
4.3.1 የባህል መድኃኒት ቅመማ...................................................................57
4.3.2 የባህል መድኃኒት አሰጣጥ...................................................................63
4.4 የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶች ............................................66
4.5 የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት..........................................................70
4.6 የባህል ሐኪሞች ከማኅበረሰቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት ..................................72
4.6.1 የባህል ሐኪሞች ከባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት.72
4.6.2 የባህል ሐኪሞች ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት.75
4.6.3 የባህላዊ ሐኪሞች የእርስ በርስ ግንኙነት ...........................................78
4.7 የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብ ለባህላዊ ሐኪሞች ያላቸው አመለካከት.....................80
4.8 በግሼ ወረዳ ጎልተው የሚታዩ የበሽታ አይነቶች ........................................82
ምዕራፍ አምስት.......................................................................................86
ማጠቃለያ...............................................................................................86

የተጠቀሱ ጽሑፋዊ ምንጮች.....................................................................90

አባሪዎች

አባሪ-1 የአውራና የንዑስ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

አባሪ-2 የአውራ መረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ የሚያሳይ

አባሪ-3 የመረጃ አቀባይ ታካሚዎች ዳራዊ መግለጫ

አባሪ-4 የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት መግለጫ

አባሪ-5 በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐከሞችን ምርጫ መሰረት በማድረግ በቅደም ተከተል የተሰደሩ በሽታዎች

አባሪ-6 በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት በ2001 እና 2002 ዓ.ም ጎልተው የታዩ በሽታዎች ዝርዝር

አባሪ-7 በግሼ ወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ የባህል መድኃኒት አዋዊዎች፣ ወጌሻዎች፣ የልምድ አዋላጆችና የፀበል ቦታዎች ዝርዝር መግለጫ ሰንጠረዥ

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

እንደ Agonafir[1] ገለፃ፣ እስከ 90% የሚገመተው የኢትዮጵያ ህዝብ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ ነው (2004፣49)። Fekadu ደግሞ 80% የሚገመተው የኢትዮጵያ ህዝብ የባህል መድኃኒት እንደሚጠቀም ገልፀው፣ በዋናነት የገጠሩ ህዝብ እንደሆነ አትተዋል (2001፣X)። ከነዚህ ሁለት መረጃዎች የምንረዳው በሀገሪቱ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ ቁጥር ከዕለት ወደ እለት እየጨመረ የመጣ መሆኑን ነው።

የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብም ከዘመናዊ ህክምና ይልቅ ለባህላዊ ህክምና ያለው ትውውቅ የጎላ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም በወረዳው አንድ ጤና ጣቢያና በ2001ዓ.ም የተከፈቱ አስር የጤና ኬላዎች ይገኛሉ። እነዚህ ጤና ጣቢያና ኬላዎች ከህዝቡ ቁጥር አንፃር ሲታዩ ለጤና አገልግሎት ሽፋኑ በቂ ናቸው ማለት አይቻልም። ስለዚህ ባህላዊ ህክምናን በአግባቡ የተጠቀሙ የሚፈወሱበት፣ በአንጻሩ ደግሞ የበሽታውን ምልክት፣ አይነትና ጸባይ ካለመለየት፣ ከመድኃኒት ምጣኔና አሰጣጥ ስርዓት ግድፈት ጋር በተያያዘ በሚፈጸም ስህተት እስከ ሞት የሚዳረጉበት አጋጣሚ እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ አንፃር በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በሽታን የመለያ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው? የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደቱ ምን ይመስላል? የሚሉትን በትኩረት ይመረምራል።

የግሼ ወረዳ የሚገኘው በአማራ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር በሰሜን ሸዋ ዞን ነው። በወረዳው ሰባ ሶስት ሺ ሶስት መቶ ዘጠና የሚጠጋ ህዝብ ይኖርበታል። ከኗሪው ህዝብ ውስጥ አብዛኛው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትናን የሚከተል ሲሆን ጥቂቶች ደግሞ ሌሎቹን የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታይ ናቸው። ጥናቱ በኦርቶዶክስ ክርስትና አማኒያን ላይ የተከረ ነው።

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ስር፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ ሃሳቦች እና የተገኙ ጠቃሚ ልምዶች ቀርበዋል።

---

[1] የፀሃፊው/ዋ ስም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፈ ከሆነ የአውሮፓውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚያሳይ ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈው ደግሞ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር የሚያመለክት መሆኑን ልብ ይሏል።

በምዕራፍ ሁለት፤ የግሼ ወረዳ አመሰራረትና የህዝቡ አኗኗር፣ መልክዓ ምድር፣ ቋንቋና ሃይማኖት፣ የወረዳው የትምህርትና የጤና ሁኔታ፣ የህዝቡ መተዳደሪያ ዳሰሳ ተደርጓል።

በምዕራፍ ሶስት፤ የባህላዊ ህክምና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ እና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ተካተዋል። በንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፉ የባህላዊ ህክምና ፅንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ፤ የባህላዊ መድኃኒት ብያኔና ትወራዊ ዳራ፤ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ምንነትና ምድብ፤ የባህል ህክምና አይነቶች፤ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ፤ የባህላዊ ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶች፤ የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት፤ የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ታይተዋል። ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ስራዎች ምን ገፅታ እናዳላቸው ቅኝት ተደርጓል።

ምዕራፍ አራት፤ በግሼ ወረዳ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ምን እንደሚመስል ገለፃ የቀረበበት እና ትንታኔ የተሰጠበት ክፍል ነው። በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት፤ የጥናቱ ማጠቃለያና የዋቢ መጻህፍት ዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከነዚህ በመቀጠል ፣ የመረጃ አቀባዮች ዳራ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ተካተው ቀርበዋል።

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ርዕስ ለመምረጥ ያነሳሳኝ ምክንያት፤ በአደኩበት ማኅበረሰብ የባህል መድኃኒት ተጠቃሚ ቁጥር ብዙ ቢሆንም ከአጠቃቀምና ከአሰጣጥ ግድፈት የተነሳ ለከፋ ስቃይና ህልፈተ ሕይወት እንደሚዳረጉ እሰማ ነበር። በአንጻሩ በአግባቡ የተጠቀሙ ህሙማን ከህመማቸው የሚፈወሱበት ሌሎች ደግሞ የበሽታን ምልክት፣ ዓይነትና ሀባይ በደንብ መርምሮ ካለመረዳትና መለየት፤ ከመድኃኒት አመጣጠንና ቅመማ፣ አሰጣጥና አጠቃቀም ግድፈት ጋር በተያያዘ ሕይወታቸውን የሚያጡበት ተቋም ነው ተብሎ ይታሰባል። ከዚህ አንጻር በባህላዊ ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎችን፤ በሽታ የመለያ ዘዴያቸውን፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልታቸውን መቃኘት እና ማጥናት ተገቢ በመሆኑ ለጥናት መርጬዋለሁ።

ሌላው ደግሞ በኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውስጥ "ሀገረሰባዊ መድኃኒት" አንዱ የጥናትና ምርምር መስክ መሆኑን በተማሪነት ጊዜዬ ተረድቼ ስለነበር፤ ሳይንሱንና ባህሉን በመቃኘት የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት በተመረጠው ርዕስ ዙሪያ ትኩረት አደረግሁ።

## 1.2 የጥናቱ ዳራ

እንደ Molvaer ገለፃ፤ "የባህል ህክምና ሥርዓቶች ከጤና ጋር በተያያዘ የግለሰብን ወይም የቡድን እውቀትን፣ እምነቶችን፣ ቴክኒኮችን፣ ሚናዎችን፣ ደንቦችን፣ እሴቶችን፣ ፍልስፍናዎችን፣ አመለካከቶችን፣ ልማዶችን፣ ሥርዓቶችን እና ትዕምርታዊ ውክልናዎችን መሰረት ያደረገ አጠቃላይ ድምር ውጤት ናቸው" (1987፣12)። ከዚህ አንጻር የማኅበረሰብን የህክምና ሥርዓት፣ እውቀትና ልማድ ማጥናት አንዱ የፎክሎር መስክ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ (Yoder፣1972፣192)።

ይህ የባህል ህክምና ዘርፍ ከፎክሎር ጥናት መስኮች "ሃገረሰባዊ ልማድ" (Social Folk Customs) ምድብ ውስጥ የሚፈረጅ ሲሆን በንዑስ ክፍል "ሃገረሰባዊ መድኃኒት" (Folk Medicine) በመባል ይጠናል። ባህላዊ ህክምና ተፈጥሯዊ (ኔቸራዊ) መድኃኒትን እና መለኮታዊ ተግባራትን የሚያካትት ጥናት ነው (Huffored፣ 1986፣307፤ Murdock፣ 1980፣6 እና ፈቃደ፣1991፣13)። ተፈጥሯዊ መድኃኒት ደግሞ እፅዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድናትና ነፍሳትን በመጠቀም የሚቀመም መድኃኒት ሲሆን በዘርፉ የሚሰጠውን የህክምና ተግባር ያጠቃልላል።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በግሼ ወረዳ የሚካሄደውን፤ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ምን እንደሚመስል በመመርመር፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን ማሳየት ሲሆን በተጓዳኝ የማኅበረሰቡን ታሪክ፣ አኗኗር፣ ማኅበራዊ ና ኢኮኖሚያና ዳራዎችን ይዳስሳል። የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች መግለጽ፤
- በባህላዊ ህክምና የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶችን መጠቆም፤
- በባህላዊ ህክም ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶችን መለየት፤
- ለባህላዊ መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ቀናት ትዕምርታዊ ፋይዳ ማመልከት፤
- የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችና ምስጢራዊነት መግለጽ፤
- የባህል ሐኪሞች ከማኅበረሰቡ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ማኅበረሰቡ ለባህል ሐኪሞች ያለውን አመለካከት መቃኘት፤
- በግሼ ወረዳ የሚካሄደውን፤ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ሰንዶ ማስቀመጥ፤ የሚሉ ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፦

1ኛ. የባህል ህክምናው ዘርፍ ለአካባቢው ማኅበረሰብ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ለመረዳት፤ ለክልሉ መንግስት፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ጤና ቢሮዎች፣ ለባህላዊ መድኃኒት አስተዳደር ቢሮ፣ ለብሔራዊ እፀዋት ማዕከል፣ ለዘመናዊ ህክምና ምርምር ጥናት መረጃዎችን ይጠቁማል ተብሎ ይታሰባል።

2ኛ የማኅበረሰቡን የባህላዊ ህክምና ጥበብና አስተሳሰብ ለመገንዘብ፤ ሀገረሰባዊ ልማዶችንና ተጓዳኝ ጥናቶችን ለሚያካሂዱ የፎክሎር፣ የሶሽሎጂ፣ የአንትሮፖሎጂ እና የታሪክ ባለሙያዎች መረጃን ይጠቁም ይሆናል ተብሎ ይታመናል ።

3ኛ. የወረዳውን፤ የባህላዊ ህክምና አገልግሎት፣ በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ሰንዶ የሚያስቀምጥ ጥናት በመሆኑ ለቀጣይ ተመራማሪና ትውልድ ፤የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል ተብሎ ይገመታል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት[2] በግሼ ወረዳ በሚገኙ የባህል ሐኪሞች እና መድኃኒቶቻቸው ላይ ብቻ ያተኩራል። መረጃዎቹም ከባህላዊ ሐኪሞችና ከባህላዊ መድኃኒት ጥናት አንጻር የሚመረመሩ ሲሆን የመድኃኒቶቹን ንጥረ ነገር፣ በሽታን የማዳን ኃይልና ጊዜ አይመረምርም። ለዚህም ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉት ግብዓት በቤተ-ሙከራ ተፈትሸው የንጥረ ነገር (የኬሚካል) ደረጃቸው የሚወሰን በመሆኑ እና ከዚህ ጥናት አላማና ይዘት ጋር የማይዛመዱ በመሆናቸው ጥናቱ እነዚህን ጉዳዮች አይዳስስም።

ጥናቱ በግሼ ወረዳ በሚገኙ አስራ አንድ ቀበሌዎች የተገደበ ነው። ከነዚህ ቀበሌዎች ዘጠኙ የተመረጡ ሲሆን ሁለቱ (አስናፊትና አራጣ ወጠፊ) ቀበሌዎች ከወረዳው ርቀት አላቸው ከሚባሉ ቀበሌዎች ግንባር ቀደም በመሆናቸው በዚህ ጥናት አልተካተቱም። ከተመረጡ ቀበሌዎች የታወቁና እራሳቸውን ችለው በባህላዊ ህክምና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች ብዛት አስራ ሶስት እንደሆኑ ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች፤ ከወረዳው አስተዳደርና ከቀበሌ አመራሮች

---

[2] ይህ ጥናት የተካሄደው በወጥ (indigenous) ና አነስተኛ በሆነ አካባቢ ነው። የሚሸፍነው አካባቢና ጉዳይ እጅጉን የተቀነበበ ነው ማላት ይቻላል። ጥናቱ ታላሚ ባደረገው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በብዛት የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የሃይማኖት ስርጭቱም፤ 98.13%ቱ የኦረቶዶክስ፣1.03% የካቶሊክና 0.84% የሙስሊም ሐይማኖት ተከታዮች ናቸው። በጥናቱ ቦታ ከኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሌላ በባህል ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች ማግኘት ባለመቻሉ በዚህ ጥናት ውስጥ ማካተት አልተቻለም። የባህላዊ የህክምና አሰጣጡም ቢሆን አሁን በወረዳው ያሉትን የባህል ሐኪሞች እንጅ በወረዳው የባህል ህክምና የተጀመረበትን ዘመንና ያሳለፈውን ሂደት ሁሉ አይመለከትም። ሌሎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በእግረ መንገድ ካልሆነ በስተቀር በዝርዝር አልታዩም።

ለማረጋገጥ ተችሏል። ከነዚህ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ውስጥ አስራ አንዱን በዓላማ ተኮር ናሙና ዘዴ በመምረጥ የጥናቱ ተተኳሪና ታላሚ አካል ሆነዋል። ከነዚህ የባህል ሐኪሞች መካከል አምስቱ አውራ የመረጃ አቀባይ በመሆን ተመርጠዋል።

## 1.6 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይ እና ከካልዓይ[3] የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል። ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ታላሚ ቡድናዊ ውይይት ተመርጠዋል። እነዚህ የቀዳማይ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት ተመራጭና ታላሚ ሲሆኑ ዘዴዎቹን እንደአስፈላጊነታቸውና አመቺነታቸው እያፈራረቁ መጠቀም ለመረጃው ግብዓትና ጥራት ከፍተኛ አስተዋጽኦና ጠቀሜታ እንዳላቸው የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ፤ (Goldstein፣ 1964፣ 77-104፤ Kottak፣ 1991፣23 እና ፊቃደ፣ 1991፣ 90-99)።

ከምልከታ ተሳትፏዊ ምልከታ እና ጽሞናዊ ምልከታ የተመረጡ ሲሆን ከቃለ መጠይቅ ደግሞ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ ተመርጠዋል። እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተወሰነ ማኅበረሰብ ባህል፣ ልምድ፣ ትውን ጥበብ ማጥናት ሲታሰብ ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንደሆኑ ይጠቁማሉ፤ (Kottak፣ 1991፣ 23-24 እና Goldstein፣ 1964፣ 78-99)።

በአጠቃላይ ዋና ዋና በሚባሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ታላሚ በማድረግ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች እንደአመቺነታቸው በቪዲዮ ካሜራ (2 ሲዲ)፣ በፎቶ ግራፍ(70 ፎቶዎች)፣ በመቅረጸ ድምጽ (17 ካሴት) እና በማስታወሻ ተቀርጸዋል፣ ተቀድተዋል፣ ተሰንደዋል። ከላይ የተጠቀሱት ድብልቅ (የተውጣጡ) የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፤ የተመረጡበትን ምክንያት፣ አስፈላጊነት፣ ጥቅምና አገልግሎት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 1.6.1 ተሣትፏዊ ምልከታ (Participant Observation )

ተሣትፏዊ ምልከታን ተጠቅሜ ከአውራ መረጃ አቀባዮች ጋር በመሆን የባህላዊ መድኃኒት የሚገኙበት ቦታ ድረስ በመሄድ ከእፀዋትና ከማዕድናት ናሙና ሰብስቤያለሁ፤ ከእፀዋት ስር፣

---

[3] ከካልዓይ ምንጮች፤ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት የቤተ መጻህፍት ጥናት ተደርጓል። በዚህ መሰረት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ(ስድስት ኪሎ ሙዚየምና ኬኔዲ፣ አምስት ኪሎ ፋርማሲ፣ አራት ኪሎ ብሔራዊ እፅዋት ማእከል፣ ጥቁር አንበሳ)፣ በፓስተርና ሀብት ጥበቃ ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በቅድስት ስላሴ ኮሌጅ፣ በብዝሃ ሀይወት ጥናትና ምርምር ተቋም በሚገኙ አብያተ መጻህፍት ውስጥ ነው። ለንባብ የተመረጡትም በመስኩ ምሁራን የተዘጋጁ የትወራ መጻህፍት፣ የጥናት መጽሔቶች፣የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያና የፒ.ኤች.ዲ ጥናቶች ናቸው።

ቅጠል፣ ፍሬ፣ ቅርፊት፣ ግንድ ለመድኃኒትነት እንደሚያገለግሉ አጢኛለሁ፤ የተወሰኑትን ለይቻለሁ። ለየትኛው በሽታ እንደሚውሉ እና እንዴት እንደሚቀመሙ አጢኛለሁ፣ የባህል ሐኪሞቹ የህመምተኛውን በሽታ እንዴት እንደሚለዩ ፈትሼ ለማየት ሞክሬያለሁ፣ የባህላዊ መድኃኒት ተጠቃሚ ህመምተኞችን ስለህመማቸው አጀማመር፣ ሁኔታ እና ስላገኙት ህክምና እንደቤተሰብ አይነት ቀረቤታ በመፍጠርና በመወያየት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቀጥታ ሰብስቤያለሁ።

## 1.6.2 ዕሞናዊ ምልከታ (None Participant Observation )

የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብ ስለጤንነቱና ህክምና ልምዱ፣ ለባህላዊ ሐኪሞች ያለው አመለካከት፣ ማኅበረሰቡ ከባህላዊና ከዘመናዊ ህክምና የትኛውን እንደሚመርጥ፤ የጤና አጠባበቁ፣ ልምዱና ተሞክሮው ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለማንሳትና፤ ለመታዘብ አመቺ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ዕሞናዊ ምልከታ ያካሄድኩት በባህላዊና በዘመናዊ ህክምና ቤቶች በመገኘት፣ ህሙማንን በመጎብኘት፣ አልፎ አልፎ ስለህመማቸው ሁኔታ በማነጋገር፣ ስለሚወስዱት ህክምና ያላቸውን አመለካከትና እምነት ቃኝቻለሁ፤ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመገንዘብ እጅጉን የተመቸ በመሆኑ ዕሞናዊ ምልከታን ተጠቅሜያለሁ።

## 1.6.3 ቃለ መጠይቅ

ከቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ንዑሳን ውስጥ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ መረጃዎችን ከመስክ ሰብስቤያለሁ። ከእነዚህ የቃለ መጠይቅ ዓይነቶች ውስን ቃለ መጠይቅ፣ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅ እና ነፃ ቃለመጠይቅ በማድረግና እንደአመቺነታቸው እያፈራረቅሁ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። በመሆኑም፤ መደበኛ ቃለ መጠይቆችን በብዛት ያቀረብኩት ለአውራ መረጃ አቀባዮች ነው።

ለኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ ተግባራዊ የሆነው ነፃ ቃለ መጠይቅ ነው። ይህንን ቃለ መጠይቅ በመስክ ላይ እያለሁ፤ ወቅትና ጊዜ በፈቀደልኝ ቦታ ከአውራና ከንዑስ መረጃ አቀባዮቹ (የባህል ሐኪሞች)፣ ከህመምተኞች፣ ከዘመናዊ የሕክምና ባለሙያዎች እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ ለባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ያላቸውን አመለካከት ለመገንዘብ አመቺ አጋጣሚዎችን ፈጥሮልኛል።

ከዚህም በተጨማሪ ለተጠኚ አካላት ነፃ ቃለ መጠይቅ እንደአመቺነቱ አቅርቤያለሁ። ይህ ዘዴ፤ የጥናቱ ታላሚ አካላትም ሳይፈሩ፣ ሳይጠነቀቁ፣ ሳይጨነቁ ተፈጥሯዊ የሆነውን

አመለካከት፣ ግንዛቤና እውቀት ለመቃኘት አመቺ ሆኖ ያገኘሁት በመሆኑ ተጠቅሜበታለሁ። የጥያቄዎቹን ስርዓታዊነት እንደ የባህላቸው፣ እንደ የዕድሜ እርከናቸው፣ እንደ የማኅበራዊ ደረጃቸውና ሁኔታቸው በማለዘብ ትህትና በተሞላበት መልኩ እንዲቀርቡ ተደርጓል።

### 1.6.4 ታላሚ የቡድን ውይይት (Focused group discussion)

መስክ ላይ እያለሁ በአንደኛና በሁለተኛ ዙር ያልተሟሉና የተዘነጉ መረጃዎችን ለማሟላት እና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ታላሚ የቡድን ተኮር ውይይት[4] አካሂጃለሁ። ከታላሚ የቡድን ውይይት በፊት በሁለቱ ዙር የሰበሰባኳቸውን መረጃዎች፤ ከማስታወሻ፣ ከፎቶና ከቪዲዮ መረጃን በመምረጥና በስርዓት በመሰደር አደራጅቼ አቅርቤያለሁ። ለቡድን ተኮር ተወያዮች ነፃ፣ ከፊል ነፃና ውስን ቃለ መጠይቆች ቀርበዋል። ይህም በመሆኑ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአውራ መረጃ አቀባዮቼና በታላሚ የቡድን ውይይት ተሳታፊ አባላት እንዲወያዩባቸው አድርጌያለሁ።

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ ጥናት እና የይዘት ትንተና ስልትን መሰረት ያደረገ ነው። ገላጭ ጥናት ዘዴን የተጠቀምኩት የባህል ህክምና ባለሙያዎች የሰጡትን መረጃ ለመግለጽ (ለመተረክ)፣ የይዘት ትንተናን ደግሞ የባህል ሐኪሞቹ፤ በሽታ የመለያ ዘዴያቸውን፣ በመድኃኒት ቅመማ ጊዜ የሚጠቀሙትን ስልት፣ የተምሳሌቶችን ትዕምርታዊነት (ትርጉምና ፋይዳ) ከነተጠቃሽ ምክንያታቸው ለማብራራት ተጠቅሜበታለሁ።

## 1.8 የመስክ ተመክሮ

አንድ የመስክ ተመራማሪ ከመስክ በፊት፣ መስክ ላይና ከመስክ መልስ ምን ምንተግባራትን ማከናወን እንዳለበት Goldstein እና ፈቃደ በዝርዝር ምክር ይለግሳሉ (1964፣ 37-40፤ 1991፣124-138)። እኔም ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት፣ መስክ ላይ እና ከመስክ በኋላ ምን ምን ተግባርትን እንዳከናወንኩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

---

[4] በታላሚ የቡድን ውይይቱ እሉት የቀረቡ ዓበይት ነጥቦች፤ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የባህል መድኃኒቶች ሲሰበሰቡ፣ ሲቀመሙና ሲሰጡ የሚፈጸሙ ስርዓቶች፤ ለባህላዊ መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ቀናት ትዕምርታዊነት ፋይዳና ትርጓሜ፤ የመድኃኒት ቅመማ ሂደት፤ የመድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ፤ የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችና ምስጢራዊነት፤ በባህል ህክምናው የሴቶች ተሳትፎ፤ የባህል ሐኪሞች ከህመምተኛ፣ ከዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችና እርስ በርስ ያላቸው ቀረቤታ፤ ማኅበረሰቡ ለባህል ሐኪሞች ያላቸው አመለካከት፤ የባህል ሐኪሞች በተደጋጋሚ የሚፈውሷቸው የበሽታ አይነቶች ላይ ውይይት ተደርጓል፤ (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)።

### 1.8.1 ከመስክ በፊት

ይህ ጥናት በትምህርት ክፍሉ ከጸደቀልኝ እለት ጀምሮ ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ሁለት ዋና ዋና ተግባራትን አከናውኛለሁ፡፡ የመጀመሪያው ተግባር ለጥናት በተመረጠው አካባቢ የባህል ሐኪሞች መኖራቸውን ፣ ብዛታቸውን፣ መገኛ አካባቢያቸውን፣ ስማቸውን እና ለዚህ ጥናት ፍቃደኛ መሆናቸውን በማረጋገጥ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሁለተኛው ለጥናቱ ተዛማጅ የሆኑ ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን የመረመርኩበትና ያሰባሰብኩበት ወቅት ነው፡፡

በመጀመሪያው ዙር አላማና እቅዴ ታላሚ የሆኑ ተጠኚ አካላትን ለማግኘት ሶስት ቁልፍ ተግባራትን ፈጽሜያለሁ፡፡ አንደኛ የግሼና አካባቢው ተወላጅ የሆኑትን አቶ ካሳ ጥላሁንን ተዋወቅሁ፡፡ አቶ ካሳ ደግሞ የግሼ ወረዳ አስተዳዳሪ ዋና ሃላፊ ከሆኑት አቶ አወቀ ዘነበ እና ሁለት የባህል ሐኪሞችን አስተዋወቁኝ፡፡ ሁለተኛው የመረጃ አቀባዬ አቶ በቀለ ሞላ ይባላሉ፡፡ አቶ በቀለ የባህል ሐኪም መሪ ጌታ ዲበኩሉ እና ደብተራ ጌታነህን አስተቃወቁኝ፡፡ መሪ ጌታ ዲበኩሉ ደግሞ ፣ ከመሪ ጌታ መስፍን ገብሬ እና ከታለእግዜር ይናዱ ጋር አስተዋወቁኝ፡፡ ሶስተኛው መረጃ አቀባዬ ደብተራ በየነ አበጋዝ ናቸው፡፡ ከሳቸው በተጨማሪ ሁለት የባህል ሐኪሞን አነጋግረው መረጃ ላኩልኝ፡፡

### 1.8.2 መስክ ላይ

የመስክ ስምሪቱ ከመጀመሩ በፊት ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ደብዳቤ አፅፌ ለሰሜን ሸዋ ዞን እና ለግሼ ወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በመያዝ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ካጠናቀቅሁ በኋላ ሚያዝያ 7/2003 ዓ.ም ወደ ግሼ ወረዳ ጉዞ ጀመርኩ፡፡

ሚያዝያ ዘጠኝ በግሼ ወረዳ ራቤል ከተማ ደርሼ አቶ አሰፋ ዳኜ ቤት አረፍኩ፡፡ ከሚያዝያ አስር እስከ አስራ ስድስት በወረዳው ኃላፊና በቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ አሰፋ ዳኜ በመታገዝ በወረዳው ቀበሌውች አሉ ከሚባሉና በማኅበረሰቡ አመኔታና ከበሬታ የተቸራቸውን የባህል ሐኪሞች ተዋወቅሁ[5]፡፡

---

[5]የመስክ ምርምር ጥናቱ አንድ ወር የፈጀ ሲሆን በባህላዊ ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎችን ታላሚ በማድረግ በሶስትና በአራት ዙር ተከፍሎ ተካሂዷል፡፡ በመጀመሪያው ዙር ከአውራና ንዑስ መረጃ አቀባዮቼ ትውውቅ ማድረግና አድራሻቸውን በመያዝ ላይ ያተኮረ (በዋናነት በቅድመ መስክ ጊዜ አድራሻቸው ተጠቁሟል) ነው፡፡ በሁለተኛው ዙር በተያዘው ቀነ ቀጠሮ መሰረት በመገናኘት የመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ የተካሄደበት ወቅት ነው፡፡ ሶስተኛው ዙር ከሁለተኛው ዙር ቃለ መጠይቅ የቀጠለና ያልተዳሰሱ፣ የተዘነጉና ያልተብራሩ ጥያቄዎች ካሉ በድጋሚ የቀረበበት ዙር ሲሆን አራተኛው ዙር ደግሞ አምስት አውራ የመረጃ አቀባዮችንና አንድ ንዑስ መረጃ አቀባይን ያካተተ የቡድን ውይይት በማካሄድ መረጃ የተሰበሰበበት ነው፡፡ በመረጃ አሰባሰቡ ወቅት ለጥናቱ ታላሚ የሆኑ ባለሙያዎችን በማነጋገሩ ረገድ እንዲሁም አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰቡ ሂደት የመረጃ ክፍተትና እጥረት አላጋጠመኝም፡፡

ከሚያዝያ 17 እስከ ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም ድረስ አስራ አንድ ታዋቂ የባህል ሐኪሞችን፣ ሁለት የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችን እና አምስት በባህላዊ ህክምና ሲረዱ የነበሩ ህሙማንን በማነጋገር መረጃ ሰብስቤያለሁ።

### 1.8.3 ከመስክ መልስ

ከመስክ መልስ የተከናወነው ቀዳሚው ስራ በተለያዩ የድምፅና የምስል መመዝገቢያ ካሴቶች የተገኙ የድምፅና የምስል መረጃዎችን ወደ ጽሁፍ መመለስ (transcription) ነበር። መረጃዎቹ ሲመለሱ ርዕሰ ጉዳዩን፣ የተገኙበትን ቀን፣ የመረጃ አቀባዮችን ስም፣ ፆታና እድሜ ተጠቁሟል።መረጃዎቹም በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ የመመደብና የመለየት ስራ ተሰርቷል። በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ በመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዙሪያ የተገኙ መረጃዎች ከአላማዎቹ ጋር በማገናዘብ ገለፃና ትንታኔ ተደርጎባቸዋል።

## 1.9 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ዐበይት ችግሮች፦

1ኛ. አንዳንድ የባህል ሐኪሞች ከመድኃኒት ቅመማ፣ አሰጣጥና መጠን ጋር በተያያዘ አልፎ አልፎ በመንግስት አካላት መጠየቃቸው፣ ፎቷቸውና ድምፃቸው በመቅረፀ ድምፅ እንደሚያዝ ሲገለፅላቸው በህግ ያስጠይቀናል ከሚል ፍራቻ ፍቃደኛ አልነበሩም።

2ኛ. ለጥናት የተመረጠው ወረዳ የመሰረተ ልማት ማለትም የመንገድ፣ የመብራትና የስልክ አገልግሎት የተሟላበት ባለመሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ከተጠኚ አካላት በርቀት ለመለዋወጥ አለመቻሉ፤ የመብራትና የፎቶ ኮፒ ማባዣ ማሽን አለመኖሩ የወረዳውን ዳራ ና የግለሰብ መረጃዎችን ኮፒ በማድረግና በማሰባሰቡ ሂደት አድካሚ አድርጎታል።

3ኛ. የወረዳው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ወጣ ገባና ገደላገደል መሆኑ እንዲሁም የጥናቱ ታላሚ ባለሙያዎች የሚኖሩበት አካባቢ መራራቅ፤ ሌላው የመስክ ስምሪቱ ፈታኝ ገጽ ነበር።

## 1.10 በጥናቱ ሂደት ላጋጠሙ ችግሮች የተወሰዱ መፍትሔዎች

በአንዳንድ የባህል ሐኪሞች የተፈጠረውን ሥጋትና ፍራቻ ለማቃለል በአውራ የመረጃ አቀባዮቹ እና በወረዳው አስተዳደር ዋና ኃላፊ በመታገዝ ችግሮቹን ለማቃለል ተችሏል። አውራ መረጃ አቀባዮቹ አራሳቸውን ምሳሌ በማድረግ ፤ የወረዳው አስተዳደር ደግሞ የሚሰጡት መረጃ ለጥናትና ምርምር መሆኑን በማስረዳት፣ የጥናቱ ውጤት ለአካባቢው ህዝብና ለነሱም ጠቃሚ መሆኑን በማስገንዘብ፣ ወደፊት በባህል ህክምናው ዘርፍ ለሚደረግ ስልጠናና ድጋፍ ይህ ጥናት እንደመነሻ ሊጠቅም እንደሚችል በመጠቆም፤ የነበረውን ፍራቻ ለመቅረፍ ተችሏል።

በወረዳው የመሰረተ ልማት አለመሟላት፤ የመብራትና የፎቶ ኮፒ ማባገር አለማግኘት መሰረታዊ ችግር ቢሆኑም፤ የወረዳውን ዳራ ከሚያዚያ 10 እስከ ሚያዚያ 12/2003 ዓ.ም ድረስ በሚመለከታቸው ቢሮዎች በመግባትና የምፈልጋቸውን መረጃዎች በቢጋር መልክ በማዘጋጀት ሰብስቤያለሁ። የተወሰኑ መረጃዎችን ማህል ሚዳ ኮፒ አድርገው እንዲያመጡልኝ ትብብር በመጠየቅ የተፈጠረውን ችግር ለማቃለል ተሞክሯል።

በመጨረሻም የአካባቢው መልክዓ ምድር ለጥናት አመቺ አለመሆንና ተጠኚ አካላት በተራራቀ ቦታ መገኘት፤ የጥናቱን ሂደት አድካሚ ቢያደርገውም፤ ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች የአካባቢ ጥናት በማካሄድ፤ የግዜ መግለጫ ሰንጠረዥና እቅድ በማዘጋጀትና ለተጠኚ አካላት እንዲደርሳቸው በማድረግ፤ ከአውራ ተጠኚ አካላትና ከዘመድ ቤት በማረፍ፤ ሌት ከቀን በመጓዝ ችግሩን ለመቅረፍ ተችሏል።

## 1.11 በጥናቱ ሂደት የተገኙ ጠቃሚ ልምዶች

የመስክ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ሲታቀድ በተቻለ መጠን ተወልደው ባደጉበት፣ በተማሩበትና በሚሰሩበት አካባቢ አልያም ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ልማዱን፣ ጠንቅቀው በሚያውቁት ማኅበረሰብ ውስጥ ጥናትና ምርምር ማካሄድ በቂ መረጃን ለማግኘት፣ አመቺ የጥናት እቅዶችን ለመተግበርና የተሻለ ስራ ለመስራት ሰፊ አጋጣሚዎችን የሚፈጥር መሆኑን በመስክ ቆይታዬ ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ። ፊቃደም፤ አንድ የራሱን ባህል የሚያጠና ግለሰብ መረጃ አቀባይ እንደልብ የማግኘት፣ በአካባቢው በነፃነት የመንቀሳቀስ፣ በባህሉ የሚከለከሉና የሚፈቀዱ ጉዳዮችን የማወቅ እድል ይኖረዋል፤ በማለት ገልጸውታል (1991፣118፤1999፣5)።

በአጠቃላይ ጥናትና ምርምር በሚያካሂዱበት ማኅበረሰብ ውስጥ ተግባብቶና ተረዳድቶ መኖር መቻልን፤ የማኅበረሰቡን አኗኗርና ባህል ጠንቅቆ ማወቅን፤ አስፈላጊ መረጃዎችን ከአካባቢው ማኅበረሰብ በማሰባሰቡ ሂደት ተግባብቶ መስራት፤ ለዘለቄታዊው ግንኙነት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ከመስክ ቆይታዬ ተምሬበታለሁ።

# ምዕራፍ ሁለት

## የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብና አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የግሼ ወረዳ አመሰራረትና የህዝቡ አኗኗር፣ መልክዓ ምድር፣ ቋንቋና ሃይማኖት፣ የወረዳው የትምህርትና የጤና ሁኔታ እና የህዝቡ መተዳደሪያ በዋናነት ተዳሰዋል። ዝርዝር ጉዳዩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 2.1 የግሼ አመሰራረትና የህዝቡ አኗኗር አጭር ቅኝት

የግሼ ወረዳ አመሰራረት፣ ስያሜና ከየት መጣነት ለማወቅ በተደረገ ጥረት በአፈ ታሪክም ሆነ በጽሑፍ ደረጃ መረጃ ማግኘት ባይቻልም፤ በአካባቢው ህዝብ የሰፈረው በጣም ጥንት እንደሆነ ከአንዳንድ አፈ ታሪኮችና የታሪክ መዛግብት መገንዘብ ይቻላል።

የግሼ ወረዳ አብያተክርስቲያናት አስተዳዳሪና የሰባ ዘጠኝ አመት አዛውንት የሆኑት መሪጌታ ደመረ አለሙ "የግሼ ህዝብ ኗሪነቱ ጥንት ነው። ለምሳሌ ከዳየር ማርያም ቤተክርስቲያን ታሪክ እንኳ ብንነሳ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት እንደተመሰረተች አባቶች ይናገራሉ፤ ሌላው በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ [ኢብን ኢብራሂም መሐመድ እ.ኤ.አ ከ1531 ጀምሮ ለአስራ አምስት ዓመታት ያህል እስከ ሰሜን ዘልቆ መቆየቱ አይዘነጋም][6] ተድባበ ማሪያምና ኪዳነ ምህረት የተባሉት ሁለት ቤተክርስቲያናት ተቃጥለዋል" በማለት በአካባቢው ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ይኖር እንደነበር ጠቁመዋል። ስለግሼ አመሰራረትና ስያሜ ሲያስረዱም "የግሼ አመሰራረት በውል አይታወቅም፤ አንዳንድ አባቶች ሲናገሩ የአካባቢው ገዥ የነበሩ ባላባቶች አንዳንድ አድባራትንና አብያተክርስቲያናትን ሲያሰሩ መኖሪያቸው እዚህ ራቤል ነበር ይባላል። የአካባቢው ገዥ የነበሩ ባላባቶች ሹም ሽር የሚያደርጉበት፣ አድባራት የሚገናኙበት ቦታ በመሆኑ ድሮ መናገሻ ይባል ነበር። ይህ መናገሻ በኋላ ግሼ ተባለ" በማለት የግሼን አመሰራረትና የህዝቡን ጥንት ኗሪነት ከአፈ ታሪክ አኳያ ገልጸዋል (ሚያዚያ 11/2003 ዓ.ም)።

ከታሪክ መዛግብት አንፃር ተክለፃዲቅ ሲገልጹ፤ በግራኝ አህመድ ወረራ ጊዜ በግሼ፣ በተጉለትና በመንዝ አብያተ ክርስቲያናት እንደተቃጠሉ ጠቁመዋል። ሌላው ከ1682 እስከ 1706 ዓ.ም ባሉት ዓመታት የጊዜው ባላባት የነበረው አውሳቢዮስ ለጎንደሩ ቀዳማዊ አፄ እያሱ አዳም ሰገድ(1660-1698ዓ.ም) ባለሟል ለመሆን በአካባቢው ከነበሩ ሌሎች አስራ አንድ ባላንጣዎቹ ጋር ይፎካከር እንደነበር ተተርኳል። እነዚህም በወቅቱ የነበሩ ተፎካካሪዎች "በግሼ አውሳቢዮስ፣ በአንፆኪያ መርዕድ አዝማች ዘሚካኤል፣ በኤፍራታ ወልደገብርኤል፣

---

[6] ተጨማሪ ፍቺዎችን ወይም ገለጻዎችን ለመስጠት [ ] ምልክት ተጠቅሜአለሁ።

በደባ ለታ፣ በመንዝ ማማና ላሎ፣ በደባ ጌታቸው፣ በደብብ ጸጋ፣ በምሑይ አዛዥ መሒዴ፣ በመርሀ ቤቴና በኮራ ወልዱ፣ በሞረት ጥጉ፣ በተጉለት ይገባዋልና በውግዳ ሐሪያቆስ" እደነበሩ ተዘርዝሯል(1965፣ 183-184)።

በኋላም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አፄ ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ የቆየችውን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ የሰሜኑን ተቆጣጥረው ወሎን አስገብረው ወደ ሸዋ ሲገቡ ግሼን ይገዛ የነበረው ሀብተማሪያም በ1848ዓ.ም ተዋግቶ ለመመለስ ቢሞክርም ድል አድርገው ግሼን ተቆጣጥረውት እንደነበር ተክለፃዲቅ ጠቁመዋል (1936፣15)።

በ1857 ዓ.ም ደግሞ አፄ ምኒልክ በዐፄ ቴዎድሮስ ከታሰሩበት ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ በተመለሱ ጊዜ ከሸዋ በመጀመሪያ የገቡላቸው የግሼው ሹም ጀጃች ወልዴና የአንፆኪያው ሹም ከሲል ነሚ እንደነበሩ ጳውሎስ ኞኞ ገልፀዋል። በወቅቱ የምኒልክን ወደ መሃል ሸዋ መግባት የሰሙ የጋዳሎ ገዥ የነበሩት አቶ በዛብህ ጦር ለመግጠም ተሰልፈው እንደነበር ተገልጿል። በዚህን ጊዜ አንዲት ሴት፡-

ማነው ብላችሁ ነው ጋሻው መወልወሉ
ማነው ብላችሁ ነው ጦራችሁ መሾሉ
ማነው ብላችሁ ነው ካራችሁ መሳሉ
የጌታችሁ ልጅ ነው እረ በስማም በሉ

ብላ ገጠመች በማለት ተዘግቧል (1984፣ 21) ።

በልጅ ኢያሱ(1913-1916 ዓ.ም) ዘመነ መንግስት በወረዳው ውስጥ ለልጅ እያሱ ማረፊያ ከተማ መመስረት ተጀምሮ እንደነበር ተገልጿል። ልጅ እያሱ ቤተመንግስታቸውን በዳራትና በሴታምባ መካከል በሚገኘው ሜዳ ከፍ ባለው ኮረብታ ቦታ ላይ ቀርቁረው ነበር ይባላል። ይህም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በፈረስ ስማቸው ስያሜ ጤና አምባ ሲባል በደርግ ዘመን ስሙ ተለውጦ ደብረሰላም ተብሏል። አሁን በቦታው ላይ የባለወልድ ቤተክርስቲያን እንደተሰራበት ተጠቁሟል(የግሼ መነጽር መፅሄት፤ቅፅ1፣ ቁጥር1፣4-5)።

## 2.2 የግሼ ወረዳ መልክዓ ምድር፣ ቋንቋና ሃይማኖት

### 2.2.1 የግሼ ወረዳ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

የግሼ ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን የሚገኝ ሲሆን በሰሜን ቃሉ ወረዳ ፣ በደቡብ ጌራ ምድርና ቀያ ወረዳ፣ በምዕራብ ወረኢሉ ወረዳ በምስራቅ አንፆኪያና ገምዛ ወረዳ ያዋስኑታል። የወረዳው አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 75,409 ሄክታር (ሰባ አምስት ሺህ አራት መቶ ዘጠኝ ሄክታር) ይሸፍናል።

<u>የግሼ ወረዳን የሚያሳይ ካርታ</u>




ምንጭ፡-ከማዕከላዊ ካርታዎች ድርጅት በ1999 ዓ.ም በህዝብና ቆጠራ ወቅት ለወረዳው የተላከ ኮፒ ( ገጽ IV የቀረበውን መረጃ ልብ ይሏል)

የግሼ ወረዳ ዋና ከተማ ራቤል[7] ሲሆን የወረዳው ህዝብ ብዛት፤ በከተማ 2,208(ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ስምንት ህዝብ)፣ በገጠር 71,182(ሰባ አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ህዝብ)፤ በድምሩ 73,390 (ሰባ ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና) ህዝብ ይኖራል። ወረዳው ከአዲስ አበባ 588 ኪ..ሜ፣ ከአማራ ክልል ርዕሰ ከተማ ከባህርዳር 915 ኪ..ሜ፣ ከሰሜን ሸዋ ዞን 258 ኪ..ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። የወረዳው ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥ በመቶኛ ሲሰላ ተራራማ 50%፣ ሜዳማ 5%፣ ወጣ ገባ 30% እና ገደላ ገደል 15%ቱን ይሸፍናል።

የወረዳው የአየር ንብረት ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በጣም ውርጫማ የሆነ ክፍልም አለው። የአየር ንብረቱ በመቶኛ ሲሰላ 16.2% ቆላ፣ 43% ደጋ፣ 36% ወይና ደጋ፣ እና 4.8% ውርጫማ ነው። ከፍተኛ የሙቀት መጠኑ 19.63 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ዝቅተኛው 7.17 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው። የወረዳው ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎች ከባህር ጠለል በላይ ያላቸው ከፍታ ሲሰላ ከፍተኛ ቦታዎች እስከ 4000ሜትር /አራት ሺህ ሜትር/ ከፍታ ያላቸው ተራራዎች በወረዳው የሚገኙ ሲሆን ዝቅተኛ ቦታዎች ደግሞ 1800 ሜትር /አንደ ሺህ ስምንት መቶ ሜትር/ ከባህር ጠለል በላይ ይገኛሉ (ከግሼ ወረዳ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳይ ጽህፈት ቤት የ2003ዓ.ም የግማሽ ዓመት ሪፖርት ተሻሽሎ የተወሰደ (ያልታተመ)።

---

[7]"ራቤል" የሚለውን ስያሜዋን ያገኘችው ዘመኑ በትክክል ባይታወቅም በአካባቢው ሽማግሌዎች እንደሚነገረው ከሆነ "አንዲት መንገደኛ ሴት በቦታው ላይ ስታልፍ ርሃብ ይዟት አረፍ ትላለች። በወቅቱ አካባቢው በሾላ፣ በአጋምና በቀጋ ፍሬ የተሞላ ስለነበር። ይህንን የሾላ የአጋምና የቀጋ ፍሬ በልታ ርሃቧ መለስ ሲልላት "እዚህስ ራብ የል" ስላለች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ "ራቤል ተባለ" በማለት ይተርካሉ (መረጃ አቀብዩ፤መሪጌታ አድገህ አራጋው፤ሚያዚያ12/2003ዓ.ም)።
ራቤል በከተማነት የተቆረቆረችው በ1930ዓ.ም የጣሊያን ጦር ወረዳውን ለመቆጣጠር ወደ ግሼ በኃይል ከገባ በኋላ ነው። በ1932 ዓ.ም ጣሊያን አካባቢውን ለቆ ከወጣ በኋላ የመንግስት መዋቅሮች እንደአስተዳደር፣ ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ግምጃቤትና የመሳሰሉት ተቋቋሙ አስተዳደራዊ መዋቅር ሲዘረጋ ረቤል ከ1934ዓ.ም ጀምሮ የወረዳ ከተማ መሆኗ ሀደቀ (የግሼ መነዕር መጽሔት.ቅፅ1.ቁ.1፣7)።

የወረዳው ፀሐያማና ዝናባማ ቦታዎች እንደመልክዓ ምድሩ አቀማመጥ ከቦታ ቦታ መጠነኛ የሆነ ልዩነት ቢፈጠርም ፀሐያማ ወራቶች የሚባሉት ከጥቅምት እስከ ግንቦት ያሉት ሲሆኑ ከሰኔ እስከ መስከረም ያሉት ወራቶች ደግሞ የክረምት ወቅት ናቸው።

የወረዳው ህዝብ መተዳደሪያ በዋናነት ግብርና እና ንግድ ናቸው። ግብርና 98%ቱን ፣ ንግድ ደግሞ 2%ቱን ይሸፍናሉ። በግብርናው ዘርፍ የሚመረቱ የሰብል ዓይነቶች በመቶኛ ሲሰሉ ስንዴ18%፣ ባቄላ 15% ፣ ገብስ 13% ፣ ምስር 12%፣ ጤፍ 10%፣ አተር 9%፣ ጓያ 8%፣ ሽምብራ 7%፣ ዘንጋዳ 3%፣ በቆሎ 3%፣ ኑግ 1%፣ ተልባ 0.6% እና የጓሮ አትክልት ደግሞ 0.4% ያህሉን ይሸፍናል። የሰብሎችን ስብጥር በፐርሰንት ስንመለከት የብዕር እህል 36.61% ፣የጥራጥሬ እህል 32.48%፣ የአገዳ እህል 25.42%፣ የቅባት እህል 3.01% እና የጓሮ አትክልት 2.48% ናቸው። በየዓመቱ ከሚመረተው የምርት መጠን በፐርሰንት ሲሰላ በአማካይ 85% ከመኸር፣ 5% ከበልግ፣ 10% ከመስኖ ሆኖ እናገኘዋለን። የአፈሩ ዓይነት፤ በአብዛኛው የያዘው 94.5% አቦልሴ(ሸክላማ) ዓፈር፣ 4.3% ዋልካ (ጥቁር ዓፈር) እና 1.2% ቀይ ዓፍር እንደሆነ ተጠቁሟል (የግሼ ወረዳ ግብርናና ማስታወቂያ ጽ/ቤት የ2003ዓ.ም የግማሽ ዓመት ሪፖርት)።

## 2.2.2 የግሼ ወረዳ ህዝብ ቋንቋና ሃይማኖት

በግሼ ወረዳ በአመዛኙ የአማራ ብሔረሰብ ተወላጆች የሚገኙ ሲሆን ሌሎች ብሄረሰቦችም ይኖሩበታል። የወረዳው ህዝብ መግባቢያና የስራ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን አልፎ አልፎ ትግረኛ ይነገራል።

በወረዳው ያለውን የሃይማኖት ስብጥር በፐርሰንት ስንመለከት 98.13% ኦርቶዶክስ፣ 1.03% ፕሮቴስታንት እና 0.84% የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በኦርቶዶክስ 71(ሰባ አንድ) አብያተ ክርስቲያናት፣ 13 (አስራ ሶስት) አድባራትና 2(ሁለት) ገዳማት ይገኛሉ። 1(አንድ) የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የሚገኝ ሲሆን በእስልምና ሃይማኖት የተሰራ መስጊድ የለም (ከግሼ ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት 2003 ዓ.ም የግማሽ ዓመት ሪፖርት ከመረጃ አስተዳደር የስራ ሂደት ተሻሽሎ የተወሰደ መረጃ)።

በግሼ ወረዳ አበይት ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት መካከል የዳየር ማሪያም ቤተክርስቲያን፣ የኮባው አማኑኤል፣ አፄ ዋሻና አኖርዮስ ገዳም በዋናነት ይጠቀሳሉ። በነዚህ ቦታዎች ጥንታዊ የብራና መፃህፍት፣ ጌጣጌጦች፣ ንዋያተ ቅድሳት…እንደሚገኙና በተጓዳኝ መልኩ የባህል ህክምና እንደሚሰጥ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ከግሼ ወረዳ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳይ ጽህፈት ቤት የ2003ዓ.ም የግማሽ ዓመት ሪፖርት ተሻሽሎ የተወሰደ (ያልታተመ)።

## 2.3 የወረዳው የትምህርትና የጤና ሁኔታ

በዚህ ርዕስ ስር በግሼ ወረዳ ያሉ የትምህርትና የጤና ተቋማት ስርጭትና የአገልግሎት ሽፋን ምን ገፅታ እንዳላቸው ማብራሪያ ቀርቧል።

### 2.3.1 ትምህርት

በግሼ ወረዳ 39 መደበኛ ትምህርት፣ 24 ሳተላይት እና 10 አማራጭ ትምህርት ቤቶች በድምሩ 74 ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ።

በግሼ ወረዳ በመንግስት መደበኛ ትምህርት የሚሰጥባቸው 40 የትምህርት ተቋማት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ ተቋማት መካከል 27 የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች፣ 11 የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል፣ 1፤ የሁለተኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል እና 1፤ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ16,297/አስራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት/ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በ551 በሚሆኑ መምህራን አማካይነት በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

በሳተላይት ትምህርት ቤቶች 2,030 ተማሪዎች እና 54 መምህራን ይገኛሉ። ወረዳው 10 አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች አሉ። በነዚህ ትምህርት ቤቶች 809 ተማሪዎች በ39 መምህራን አማካይነት ትምህርታቸውን ይከታተላሉ ።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ጥቅል የትምህርት ሽፋኑ 89% የደረሰ ሲሆን ንጥር ቅበላ ደግሞ 104% ደርሷል (የግሼ ወረዳ ማስታወቂያ ጽ/ቤት በየስድስት ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት፣ ነፀብራቅ 3ኛ ዓመት ቅ.2፣ ቁ.3፣ መጋቢት 2003፤7-12)።

### 2.3.2 ጤና

በግሼ ወረዳ በመንግስት የተሰሩ የጤና ተቋማት 15፣ በግል 2፤ በድምሩ 17 የጤና ተቋማት ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። የጤና ጣቢያዎቹና የጤና ኬላዎቹ ስርጭት ሲታይ በራቤል ከተማ አንድ ጤና ጣቢያ እና ሁለት የግል ክሊኒክ ፤ በድምሩ ሶስት የጤና ተቋማት ይገኛሉ። አራት ታዳጊ ጤና ኬላዎች (ወደፊት ወደ ጤና ጣቢያነት ያድጋሉ ተብሎ የታቀዱ) በግራር አምባ፣ በደል፣ በፈረስ ቤትና በወጅት የሚገኙ ሲሆን የቀሩት አስር የጤና ኬላዎች በእያንዳንዱ ቀበሌ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

የሙያተኞችን ቁጥር በተመለከተ አንድ ጤና መኮንን፣ ስምንት ነርሶች፣ አንድ የላብራቶሪ ቴክኒሺያን፣ ሁለት ፋርማሲስቶች፣ ሁለት ጤና ረዳቶች፣ አስራሰባት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፤ በድምሩ 31/ሰላሳ አንድ/ የጤና ባለሙያዎች በስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

የባለሙያዎቹ ጥምርታ ከህዝቡ ቁጥር አንፃር ሲታይ አንድ የጤና መኮንን ለ73,390 ሰዎች፣ አንድ ነርስ ለ9,175 ሰዎች፣ አንድ ላብራቶሪ ቴክኒሺያን ለ73,390 ሰዎች፣ አንድ ፋርማሲስት ለ36,695 ሰዎች፣ አንድ ጤና ረዳት ለ36,695 ሰዎች፣ አንድ የኤክስቴንሽን ጤና ባለሙያ ለ4,318 ሰዎች አገልግሎት እንደሚሰጡ ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ለመረዳት ተችሏል (ከግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የ 2003 ዓ.ም የግማሽ ዓመት ሪፖርት ተሻሽሎ የተወሰደ) ።

## 2.4 የህዝቡ መተዳደሪያ

የግሼ ወረዳ ህዝብ መተዳደሪያ በዋናነት ግብርና እና ንግድ ናቸው። የግብርናው መስክ በግብርና ባለሙዎች በመታገዝ በአፈርና ውሃ ጥበቃ አያያዝ፣ በማዳበሪያ አቅርቦት፣ በእንስሳት ሃብት እርባታ ልማት ማኅበረሰቡ እየተሳተፍ መሆኑ ተጠቁሟል። በወረዳው የሚገኙ ገባር አርሶ አደሮች ብዛት ወንድ 15,861 (አስራ አምስት ሺ ስምንት መቶ ስልሳ አንድ)፣ ሴት 5,869 (አምስት ሺ ስምንት መቶ ስልሳ ዘጠኝ) በድምሩ 21,730(ሃያ አንድ ሺ ሰባት መቶ ሰላሳ) ገባር አርሶ አደሮች ናቸው።

በንግዱ ዘርፍ ደግሞ፤ ከ 2000 ዓ.ም እስከ አሁን ያለውን በንግድ ሥራ የሚንቀሳቀሱ ነጋድዎች በዓይነት ስናይ 2 በጅምላ፣ 367 በችርቻሮ እና 401 በአገልግሎት ሰጭነት ተሰማርተው ይገኛሉ። ወረዳው ወጣቱን ኃይል በማደራጀት ከ1998 ዓ.ም- 2001 ዓ.ም ከ396 በለይ የሚሆኑ ወጣቶችን በተለያየ የሙያ መስክ በማሰልጠን ከ205,000 ብር በላይ ብድር በመስጠት እራሳቸውን እንዲችሉ ድጋፍ አድርጓል። በአሁኑ ወቅት በአነስተኛና ጥቃቅን በከተማና በገጠር በማደራጀት የልማት ተጠቃሚ የሆኑ ወንድ 558፣ ሴት 288፤ በድምሩ ለ 946 ወጣቶች የስራ እድል ተከፍቶ አገልግሎት እየሰጡ ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

## ክለሳ ድርሣን

በዚህ ምዕራፍ በመጀመሪያ የባህል ህክምና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ የቀረበ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ቀርቧል፡፡

## 3.1 ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በዚህ ንዑስ ክፍል የተለያዩ ምሁራን ስለባህላዊ ህክምና ንድፈ ሃሳቦች፣ የባህላዊ መድኃኒት[8] ብያኔዎችና ተጓዳኝ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ የቅኝቱ ይዘትና ትኩረትም በባህላዊ ህክምና እውቀት፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

### 3.1.1 የባህላዊ ህክምና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

የባህል ህክምና በአንድ ወገኑ ፎክሎር በሌላ በኩል ደግሞ ህክምና በመሆኑ የባህልንና የሳይንስን የእርስ በእርስ መስተጋብር አጣምሮ የያዘና የሁለቱን ግንኙነት በውል የሚያሳይ ሙያ እደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይጠቁማሉ (Hurreize፣ 2006፣120)፡፡

እንደ Yoder ገለፃ፤ ባህላዊ ህክምና በሁለት ዐበይት ዘርፎች ይከፈላል፡፡ አንደኛው ተፈጥሯዊ የባህል ህክምና[9] ሲሆን ሁለተኛው መለኮታዊ የባህል ህክምና ዘርፍ ነው፡፡ ተፈጥሯዊ የባህል ህክምና ሲባል ከአካባቢ ከሚገኙ ግብዓቶች ቅጠላ ቅጠልን፣ እፀዋትን፣ ማዕድናትን እና እንስሳትን በመጠቀም የሚቀመሙ መድኃኒቶችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ የባህል ሐኪሙ በሽታን ለመከላከል እና ህመምተኛን ለመፈወስ ከተፈጥሮ የሚገኙ ንጥረ ነገሮችን ቀምሞ የሚያዘጋጃቸውን መድኃኒቶች እና የሚተገበረውን ቴክኒካዊ እውቀት ጭምር በዋናነት ያካትታል፡፡

ሁለተኛው የባህል ህክምና ዘርፍ መለኮታዊ የባህል ህክምና ነው፡፡ በዚህ የህክምና ዘርፍ ስር በሽታን ለመከላከልና ህመምተኛን ለመፈወስ፤ የባህል ሐኪሙ የሚጠቀመው መንፈሳዊ መዝሙር፣ መንፈሳዊ ድርጊት (ፆም፣ ፀሎት፣ ስግደት) እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል (1972:192)፡፡

---

[8] ባህላዊ መድኃኒት (Traditional Medicine) የተለያዩ መጠሪያዎች አሉት፡፡ ለአብነት ያህል፤ ህገረሰባዊ መድኃኒት (Folk medicine) ፣አማራጭ መድኃኒት (alternative medicine) ፣ ሀገር በቀል መድኃኒት (indigenous medicine) ዕፀ መድኃኒት (Herbal Medicine)፣ አጋዥ መድኃኒት(complementary medicine)፣ ነገድ መድኃኒት (ethno medicine) በመባል በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል (Sofowora፣ 1982፣3-5)፡፡ ይህን የስያሜ ልዩነት ለማስወገድ ሲባል ባህላዊ መድኃኒት የሚለውን ስያሜ በዚህ ጥናት ውስጥ በወጥነት ተጠቅሜበታለሁ፡፡

[9] ይህ ጥናት በተፈጥሯዊ የባህል ህክምና ዘርፍ ተሰማርተው፤ ከእፀዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፍሳት መድኃኒት በመቀመም በሽታን ለመፈወስ እና ለመከላከል ጥረት የሚያደርጉ የባህል ህክምና ባለሙያዎችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

Murdock ዋና ዋና የሚባሉ የበሽታ መንስኤ ንድፈ ሀሳቦችን[10] በሁለት ይመድቧቸዋል፡፡ እነርሱም በተፈጥሯዊ እና በመለኮታዊ (በአስማታዊ) ኃይል የሚከሰቱ የበሽታ መንስኤዎች ናቸው፡፡ በተፈጥሯዊ ኃይል የሚከሰቱ የበሽታ መንስኤዎች የሚባሉት በድንገተኛ አደጋዎች፣ በወረርሽኝ፣ በተበከለ ምግብና ውሃ፣ በነፍሳት መነደፍና በመሳሰሉት የሚመጡ በሽታዎች በዚህ ምድብ ስር ይጠቃለላሉ፡፡ በመለኮታዊ (አስማታዊ) ኃይል የሚከሰቱ የበሽታ መንስኤዎች፣ ከፈጣሪ፣ ከቀድሞ አያቶች መንፈስ፣ ከሰይጣን፣ ከመተት፣ ከእርግማን፣ ከቡዳና ከመሳሰሉት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ማኅበረሰቡ ስለበሽታ መንስኤ፣ መከላከያ እና መፈወሻ ያላቸው አመለካከትና ግንዛቤ፤ ለጉዳዩ የሚሰጡት ምክንያት በባህል ህክምና ሥርዓተ ጥናት ውስጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች እንደሆኑ ጠቁመዋል (1980፣8-9) ፡፡

ተፈጥሯዊና መለኮታዊ የበሽታ መንስኤዎች በባህል ህክምና ጥናት ውስጥ በዋናነት ይጠናሉ፡፡ በመስኩ ጥናት ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች የጥናታቸው ማዕቀፍ (framework) በመሆን ያገለግላሉ ፡፡ እነዚህ የባህል ህክምና ዘርፎች አንድም በተናጠል አለያም በንጽጽር የሚጠኑ መሆናቸውን ያስረዳሉ (Murdock፣ 1980፣6)፡፡ Hufford የባህል ህክምና ባለሙያዎች ያላቸውን እውቀት እና ሙያ መሰረት በማድረግ ተፈጥሯዊና መለኮታዊ በማለት በሁለት ይመድቧቸዋል፡፡ ከነዚህ የህክምና ዘርፎች አንዱን መርጦ ማጥናት፤ የጥናት አቅጣጫና ትኩረትን ለመወሰን ያስችላል፤ በማለት ያስረዳሉ (1986፣309) ፡፡ Hufford በባህላዊ ህክምና ከሚጠኑ ዐበይት ጉዳዮች መካከል የባህል ሐኪሙና በሽተኛው ቀዳሚውን ቦታ ይወስዳሉ፡፡ በተለይ በጤና ስርዓት ዘዴ ጥናት (A Health systems approach) የባህል ሐኪሙና በሽተኛው ቀዳሚውን ስፍራ ቢወስዱም ማኅበረሰቡና መገልገያ ቁሳቁሶቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዳቸው ያላቸው ፋይዳ (ተግባራዊ ቅንጣት) መጠናት እንዳለበት ያትታሉ፡፡ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ከሚጠኑ ጉዳዮች መካከል በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልቶች፣ በሽታን ለመፈወስ የሚደረጉ ተግባራዊና ንድፈ ሀሳባዊ ክህሎቶች፣ የማኅበረሰቡ ልማድና እምነት በዋናነት ይገኙበታል (1986፣307)፡፡

ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Mesfin የጤና ስርዓትን በሶስት ምድብ ይከፍሉታል፡፡ አንደኛ የማኅበረሰብ እውቀት (በልምድ የሚደረግ የቤት ውስጥ የመጀመሪያ እርዳታና በተለያዩ

---

[10] Murdock፤ የበሽታ መንስኤ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ የተሰጠው ክፍፍል አንጻራዊ በሆነ መልኩ እንጂ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደማይሆን ይገልፃሉ፡፡ አንዳንድ በሽታዎችን በተፈጥሮም ሆነ በመለኮታዊ ኃይል ስር ለመመደብ ስንነሳ ችግር እንደሚገጥመን ያትታሉ፡፡ ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የተፈጥሮ መዛባት የመሳሰሉትን በተፈጥሮም ሆነ በመለኮታዊ ሃይል ስር ለመመደብ እና የመንስኤ ምንጩን ለመለየት እንደማይቻል ያስረዳሉ(1980:6)፡፡

ግብዓቶች እራስን ማከም)፤ ሁለተኛ. የቡድን (folk) እውቀት (የሰፈር የባህል ሐኪሞች፤ ማለትም የእፀ መድኃኒት ባለሙያዎች፣ ወጌሻዎች፣ የልምድ አዋላጆችና በመለኮት ኃይል ፈዋሾች ይጠቀሳሉ)፣ ሶስተኛ መደበኛ ስልጠና በመውሰድ ባለሙያ (Professinal) የሆኑ ዘመናዊ ሐኪሞች በማለት የጤና ዘርፍን በሶስት ይመድቡታል (1996፣10)::

በአጠቃላይ በባህል ህክምና ጥናት፤ የባህል ሐኪሙና ታካሚው ከተመሳሳይ ቡድን፣ ባህልና ማኅበረሰብ የፈለቁ ከሆነ የባህል ሐኪሙ የሚቀምመው መድኃኒትና የሚሰጠው ትዕዛዝ ባህላዊ ትርጓሜ እና ስነልቡናዊ ተጽዕኖ እንዳለው ያትታሉ (Gumede፣ 1990፣ 203)::

### 3.1.2 የባህላዊ መድኃኒት ብያኔ እና ፅንሰ ሃሣብ

ባህላዊ መድኃኒት ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ፤ የዘርፉ ምሁራን ተቀራራቢና ተመሳሳይ ብያኔዎችን እና ፅንሰ ሀሳቦችን ያቀርባሉ። ባህላዊ መድኃኒት ማለት፤ የተለያዩ ብያኔዎችንና ፅንሰ ሀሳቦች የሚያካትት፤ የማኅበረሰብ እውቀት፣ ተሞክሮና ቴክኒክ አጠቃላይ ድምር ውጤት የሆነ፤ ከእፀዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት መድኃኒት በመቀመም አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማኅበራዊ የጤና ጠንቆችን ለመከላከልና ለመፈወስ የሚተገበር ሙያ እንደሆነ ያትታሉ (Sindiga፣ 1995፣ 19፤ Gumede፣ 1990፣ 208፤ Yilma and et al 1996፣ 1፤ Richter፣ 2003፣ 6-7)::

እንደ WHO ገለፃ፤ የሰው ልጆች ጤንነታቸውን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከልና ከህመማቸው ለመፈወስ ሲሉ የባህል ህክምናን ከሺህ ዓመታት በላይ ሲጠቀሙ የኖሩበት ስርዓት፣ ልማድና ጥበብ እንደሆነ አትተዋል። ይህ ተቋም የራሱ የሆነ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ህግና ተመክሮ ያለው፤ በአንዳንድ ማኅበረሰብ በግልፅ የሚተገበር፣ በሰፊው የተለመደ፣ ስልታዊ አጠቃቀምን ያጣመረ አካል ነው። በሌላ ማኅበረሰብ ደግሞ በጣም ጥብቅና ድብቅ፣ ምስጢራዊና ውስን የሆነ አካባቢያዊ እውቀትን መሰረት ያደረገ ሙያ ነው፤ በማለት WHO ያብራራሉ (2002፣ 6-7)።

Alemayehu ስለባህላዊ መድኃኒት ምንነት ጠቅለል ያለ ብያኔ ሰጥተዋል። ባህላዊ መድኃኒት ማለት ስነ-ልቡናዊ፣ አካላዊ እና ማኅበራዊ የጤና ጠንቆችን ከሚያመጣ እና ከሚያስከትል፣ ከሚታይና ከማይታይ ህመም፣ ከበሽታ አምጭ ረቂቅ ተህዋሲያን እና ከአዕምሮ በሽታና ችግር የሚፈውስ ማንኛውም ኃይል፤ በባህላዊ መድኃኒት ስር እንደሚካተት ይገልፃሉ (1984፣114)።

የባህል መድኃኒት ምንነትን በተመለከተ Kannon ሲገልጹ፡-

> ባህላዊ መድኃኒት ማለት የዘመናዊ ጤና ሳይንስ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በሰው ልጆች ማኅበረሰባት ውስጥ የነበረ (ያለ) ጥንታዊ እና በባህል ላይ የተመሰረተ የህክምና ተግባር ነው። ባህላዊ መድኃኒትን መጠቀም በአብዛኛው ስምምነት

> የተደረሰበት አጠቃቀም እና በግል ልምድ (እውቀት) ላይ የተመሰረተ ሲሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ተግባር ነው፡፡ ባህላዊ መድኃኒት ጤናን በመጠበቁና በሽታን በመፈወሱ ባለው ሚና በማኅበረሰቡ እውቅና የተሰጠውና ተቀባይነት ያገኘ ነው፤ በማለት በይነዋል (2004፣ 32)፡፡

Good ደግሞ ለባህላዊ መድኃኒት የሚከተለውን ብያኔ ሰጥተዋል፡-

> ንጥረ ነገሮችን የማዘጋጀትና የመጠቀም አጠቃላይ የእውቀትና የቴክኒኮቹ አካል፤ አጠቃቀም ላይ ያሉ ልኬቶች እና ልምዶች ግልፅ የሆኑም ቢሆን ወይም ባይሆኑም፤ በቃልና በጽሁፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ፤ በግል ገጠመኞች፣ ልምዶች እና ምልከታዎች (መረዳቶች) ላይ የተመሰረቱ እና በአካላዊ፣ በአዕምሯዊ ወይም በማኅበራዊ ጤና ላይ ያሉ መዛነፎችን ለመመርመር፣ ለመከላከል ወይም ለማስወገድ ሲባል ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው (1987፣ 2)፡፡

ከነዚህ ጥቅሶች በመነሳት ባህላዊ መድኃኒት ማለት ዘመናዊ የጤና ሳይንስ ከመጀመሩ በፊት የነበረ፤ የሰው ልጆች ጤንነታቸውን ለመጠበቅና ከበሽታ ለመፈወስ ባህላቸውን፣ ልማዳቸውን፣ እውቀታቸውን እና ያአኗኗር ስልታቸውን መሰረት በማድረግ የሚተገብሩት የህክምና ጥበብ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

Steiner ደግሞ የባህል መድኃኒትን ምንነት እንደሚከተለው ይገልፁታል፡-

> ባህላዊ መድኃኒት ሁሉን አቀፍ የሆነ የቃልም ሆነ የጽሑፍ እውቀትንና ልምድን አካቶ በመያዝ አጠቃላይ ጤናን ለመጠበቅ፤ በሽታዎችንና ህመሞችን የመመርመር፣ የመከላከል እና የመፈወስ እውቀትን ይይዛል፡፡ ይህ በመሆኑም አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ጤንነትን በመገንባቱ ሂደት ሁሉን አቀፍ እንደሆነ ይገልፃሉ (1986፣ 67)፡፡

የአለም ጤና ድርጅት ለባህላዊ መድኃኒት የሚሠጡ ብያኔዎችና ፅንሰ ሃሳቦች የአለምን ማኅበረሰብ የሚያግባቡ አይደሉም ሲል የሚከተለውን ተግባራዊ ብያኔ (Working definition) ያትታል፡-

> ባህላዊ መድኃኒት የተለያዩ የጤና ህክምናዎችን፣ ዘዴዎችን፣ እውቀቶችንና እምነቶችን ያካትታል፡፡ ይህም ከእፀዋት፣ ከእንስሳት እና/ወይም ከማዕድናት የሚዘጋጁ መድሃኒቶችን ያጠቃልላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መንፈሳዊ ህክምናን፣ የእጅ ህክምና ስልቶችን (ብልሃቶችን)፣ ጤንነትን ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል በተናጠልም ሆነ በቡድን የሚተገበሩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ለህመምተኛ የሚደረጉ እንክብካቤዎችን፣ አካላዊ ምርመራዎችን፣ ህመምን ለመከላከል የሚደረጉ እርምጃዎችን ያጠቃልላል (2002፣ 7)፡፡

Fekaduም ስለ ባህላዊ መድኃኒት ምንነት ከ WHO እና ከ Sofowora ጋር የተቀራረበ ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ ባህላዊ መድኃኒት የተለያዩ መጠሪያዎች እንዳሉት ሁሉ፤ በብያኔ በኩልም እንደ አቀማመጡና አተገባበሩ፤ እንደ ከዋኙ ማኅበረሰብ ባህል፣ ልምድና እውቀት የተለያዩ ብያኔዎችና ስያሜዎች እንደሚሰጡት ገልፀዋል፡፡ ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፊያ መንገዱ በቃል የሆነ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማኅበራዊ የጤና ቀውሶችን በአገር

በቀሉ ጥበብና እውቀት ለመከላከል፣ ለማከምና ለመፈወስ ሲባል የሚከወን የእውቀትና የተግባር አጠቃላይ ድምር ውጤት ነው፤ በማለት አትተዋል (2001፣ 1-2)።

ከነዚህ ብያኔዎች በመነሳት፤ ባህላዊ መድኃኒት[11] ማለት የሰው ልጅ ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል፣ ከህመም ለመፈወስ፤ አካላዊ፣ አዕምሮና ማኅበራዊ በሽታዎችን ለማስወገድ ሲባል የሚተገበር ሙያ ነው፤ ማለት ይቻላል። ለሙያ ዘርፉ የሚሰጠው ብያኔ እንደ ማኅበረሰቡ አመለካከት፣ ደንብና ባህል የተለያየ መሆኑን ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ምሁራን አትተዋል። በአጠቃላይ የባህል ህክምና ጥበብ ከእፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት የሚገኙ ግብዓቶችን በዋናነት የሚጠቀም ሲሆን መንፈሳዊ ህካምናን፣ ቴክኒካዊ የህክምና ስልትን፣ ለህመምተኛ የሚደረጉ እንክብካቤዎችን የሚያካትት አጠቃላይ (holistic approach) ዘዴ ነው፤ ማለት ይቻላል።

## 3.1.3. የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ምንነትና ምድብ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የባህል ህክምና ባለሙያዎች ምንነት እና የባህል ሐኪሞች ምድብ ቀርበዋል።

### 3.1.3.1. የባህል ህክምና ባለሙያዎች ምንነት

የባህል ህክምና ባለሙያ ምንነትን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን ተቀራራቢ ብያኔና ፍቺ ይሰጣቸዋል። ከነዚህም መካከል Sindiga የሚጠቀሱ ሲሆን የሚከተለውን ብያኔ ሰጥተዋል፦

> የባህል ህክምና ባለሙያ ማለት የእፅዋት፣ የእንስሳት እና የማዕድናት ንጥረ ነገሮችን በመጠቀም በማኅበራዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ዳራዎች እንዲሁም በማኅበረሰቡ ውስጥ በሰፊው ተለምዶ ባለው እውቀት፣ ዝንባሌና እምነት ላይ በመመስረት፣ ሌሎች አንዳንድ ዘዴዎችን በመጠቀም ፤የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው። ይህ ሰው በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ የጤና እንክብካቤን ወይም ህክምና ለመስጠት ብቃት አለው ተብሎ ተቀባይነት የሚያገኘው፤ በሽታዎችን እና የአካል ጉዳቶችን ለመከላከል እና መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ማኅበራዊ ጤናን በማስገኘት (ማስጠበቅ) ረገድ በማኅበረሰቡ እውቅና ያገኘ ሰው እንደሆነ ያትታሉ (1995፣19)።

ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው የባህል ህክምና ባለሙያ ምንነትን ሲበይኑ፤ የማኅበረሰቡን ጤና በማስጠበቅ፣ በሽታን በመከላከል እና ህመምን በመፈወስ ሙያ ያላቸው፤ ከእፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት የሚገኙ ግብዓቶችን በማዘጋጀት መድኃኒት ቀምመው የሚሰጡ እና

---

[11] ባህላዊ መድኃኒት በምዕራቡ አለም ያለው ፍቺና ትርጓሜ ከዘመናዊ መድኃኒት ጋር በአቻነት የሚጠሩ፣ በአማራጭነት (Aleternative Medicine) የሚያገለግል እና ማሟያ መድኃኒት (Complimentary Medicine) በመባል እንደሚጠሩ ይጠቁማሉ (Fekadu፣ 2001፡1-2)። የባህል ህክምና ስርዓተ ዘዴውም በህግ የተደነገገ፣ ሳይንሳዊ ዘዴዎችንና ፈለጎችን የተከተለ፣ በቤተ ሙከራ የተፈተነ፣ በማንኛውም ቦታ የሚመረት፣ የባህል ሐኪሞቹም አንድ ዓይነት ተግባራትን በመፈጸም (Healers make one-track mind activities) የሚሰጡት ህክምና እንደሆነ ያትታሉ (Gumede፣ 1990፣ 205)።

በማኅበረሰቡ የተመሰከረላቸው የባህል ሐኪም እንደሚባሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተቀራረበ መልኩ Kannonም የባህል ህክምና ባለሙያን ምንነትን እንደሚከተለው ገልፀውታል፡-

> የባህል ህክምና ባለሙያ ማለት፤ በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ እፅዋትን፣ እንስሳትን፣ የማዕድናት ንጥረ ነገሮችን እንዲሁም ሌሎች በማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ልምዶች ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎችን በመጠቀም፤ የጤና እንክብካቤን በማድረግ ብቃት አለው ተብሎ ተቀባይነትን ያገኘና የታወቀ ሰው ማለት ነው (2004፣ 32) ::

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ሃሳቦች በመነሳት የባህል ህክምና ባለሙያ የሚባሉት ልማድና ባህልን፣ እምነትና ሃይማኖትን፣ ማኅበራዊ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ለተለያዩ ህመሞች መፈወሻ የሚሆኑ መድኃኒቶችን ከእፅዋት ከእንስሳትና ከማዕድናት ግብዓቶች በማዘጋጀት በሽታን የሚከላከሉና በማኅበረሰቡ አንቱታን ያተረፉ ባለሙያዎች ናቸው፤ ማለት ይቻላል፡፡

### 3.1.3.2 የባህል ሐኪሞች ምድብ

የኢትዮጵያ የባህል ህክምና ባለሙያዎች[12] በሁለት ዐበይት የህክምና ዘርፍ ስር ይመደባሉ፤ (Mekkonen፣ 1988፣ 82፤ Young፣ 1970፣ 27-29፤ Wondwosen፣ 2006፣ 32-34):: እነዚህም አለማዊ እና መንፈሳዊ በመባል ይመደባሉ፡፡ የአመዳደቡ ሥርዓት ጊዜያዊ የህክምና እውቀታቸውን፣ ዘዴያቸውን፣ ቴክኒካዊና መንፈሳዊ ክህሎታቸውን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የነዚህን ምሁራን የአከፋፈል ስርዓት በመከተል ልዩ ሙያ፣ ልዩ ንዑስ ሙያ እና የፈውስ ኃይል ምንጭ ምን እንደሆነ እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡-

ሀ. አለማዊ የባህል ህክምና ባለሙያዎች

አለማዊ የባህል ህክምና ባለሙያዎች የሚባሉት መድኃኒት አዋቂዎች፣ ወጌሻዎች እና የባህል አዋላጆች ናቸው፡፡ የነዚህ ባለሙያዎች ልዩ ሙያ እና የፈውስ ኃይል ምንጭ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከተው ነው፡፡

---

[12] የኢትዮጵያ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በሁለት ምድብ ከፍሎ ማጥናት ከኢትዮጵያ አውድ አንጻር ሲታይ በጣም ውስብስብና አስቸጋሪ ነው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በአንድ በኩል በመንፈሳዊ ኃይል የሚፈውሱ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አለማዊ የህክምና ተግባራትን በመፈፀም ህክምና ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በባህላዊም ሆነ በመንፈሳዊ ህክምና ምድብ ውስጥ ለማካተት ባለሙያዎቹ የፈለቁበትን ተቋም፣ የሚተገብሩትን የህክምና አይነትና ጊዜያዊ ሁኔታ በማጤን አንፃራዊ በሆነ መልኩ መፈረጅ እንደሚቻል ይገልጻሉ (Mekkonen፤ 1988፣ 81-82፤ Wondwosen፤ 2006፣32)፡፡

ሠንጠረዥ 1. የአለማዊ የህክምና ባለሙያዎች አጠቃላይ ዝርዝር

| ተ.ቁ | ልዩ ሙያ(ችሎታ) | ልዩ ንዑስ ሙያ | የፈውስ ኃይል ምንጭ |
|---|---|---|---|
| 1. | መድኃኒት አዋቂ | ሀ. መድኃኒት ቆራጭ | በተግባራዊ ልምምድ በሚገኝ እውቀት |
| | | ለ. መድኃኒት ሰጪ | ” |
| | | ሐ. መድኃኒት አዋቂ | ” |
| | | መ. መድኃኒት ቀቢ | ” |
| | | ሠ. መድኃኒት አጠጪ | ” |
| 2. | ወጌሻ | ሀ. ጠጋኝ | በተግባራዊ ልምምድ የሚገኝ እውቀት |
| | | ለ. እንጥል ቆራጭ | ” |
| | | ሐ. ጥርስ አውላቂ | ” |
| | | መ. ወጋሪ (ነቃሽ) | ” |
| | | ሰ. ገራዥ (መግረዝ) | ” |
| | | ረ. አጋሚ (ማገም) | ” |
| 3 | አዋላጅ | - | ” |

የመረጃ ምንጮች፡- Young (1970፣ 28) Mekkonen (1988፣82)፣ Wondwosen (2006፣ 32)

ለ. መንፈሳዊ የባህል ህክምና ባለሙያዎች

ሰንጠረዥ 2. የመንፈሳዊ የባህል ህክምና ባለሙያዎች አጠቃላይ ዝርዝር

| ተ.ቁ | ልዩ ሙያ(ችሎታ) | ልዩ ንዑስ ሙያ | የንዑስ ንዑስ ስም | የፈውስ ኃይል ምንጭ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ጠንቋይ | ሀ. ባለዛር | - | ምስጢራዊ ስጦታ ከመለኮት |
| | | ለ. ደብተራ | - | ” |
| | | | ሀ. ጋኔን ሳቢ | ” |
| | | | ለ. መጽሐፍ ገላጭ | ” |
| | | | | ” |
| 2. | አጥማቂ | ሀ. ቄስ | - | ” |
| | | ለ. መነኩሴ | - | ” |
| 3 | ሼክ | - | - | ከአላህ በሚገኝ መንፈሳዊ ሃይል። |

የመረጃ ምንጭ፡- Young (1970፣28) Mekkonen (1988፣83)፣ Wondwosen (2006፣ 34)

በአጠቃላይ የባህል ህክምና ባለሙያ የሚባሉት ሳይንሳዊ ባልሆነ መንገድ እንደአካባቢያቸው ማኅበረሰብ እምነት፣ ልማድ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና ማኅበራዊ ሁኔታ ለተለያዩ በሽታዎች መፈወሻና መከላከያ የሚሆኑ መድኃኒቶችን ከእፀዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፍሳት ተዋፅኦ እያዘጋጁ የሚሰጡና በማኅበረሰቡ አንቱታን ያተረፉ አለማዊ የባህል ሐኪሞች እንደሚባሉ፣ በመለኮት ኃይልና ተሰጥኦ የሚፈውሱ ደግሞ መንፈሳዊያን በመባል እንደሚጠሩ ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች በማኅበረሰቡ የተለያየ ስያሜ[13]

---

[13] ከዚህ በላይ የተጠቀሱ የመረጃ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የባህል ሐኪሞች በሚኖሩበት ማኅበረሰብ የተለያዩ ስያሜዎች ይሰጣቸዋል። በዚህ ጥናት ማኅበረሰቡ ለባህል ሐኪሞች የሚሰጠውን ከበሬታ፣ ተቀባይነትና መጠሪያ መሰረት በማድረግ የባህል ህክምና ባለሙያዎችን፤ የባህል ሐኪም፣ የባህል ህክምና ባለሙያ፣ ባለመድኃኒተኛ፣ የእፀመድኃኒት አዋቂ የሚሉትን መጠሪያ ስያሜዎች እንደአመቺነታቸው እያፈራረቁ ለመጠቀም ተሞክሯል።

እንደሚሰጣቸው ምሁራኑ ይጠቁማሉ፤ (Wondwosen፣ 2006፣32-34፤ Mekkonen፣ 1988፣83፤ Fekadu፣ 2001፣23-24፤ Chavunduka፣ 1994፣8፤ WHO፣ 2004፣51)።

## 3.1.4 የባህል ህክምና አይነቶች እና የልዩ ሙያተኞች ምድብ

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የባህል ህክምና አይነቶች በአራት ዋና ዋና ምድብ ይከፈላሉ። በነዚህ የህክምና አይነቶች ውስጥ የሚመደቡ ልዩ ሙያ/ልዩ ችሎታ ያላቸው የባህል ሐኪሞች በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። የአመዳደቡን ሥርዓትና አይነት በተመለከተ የተለያዩ አገሮች ምሁራን የተለያየ አመለካከት ቢኖራቸውም የኢትዮጵያን የባህል ህክምና ባጠኑ ባለሙያዎች የተሰጠውን ምድብ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረው ነው፤ (Young፤ 1970፣ 23-26፤ Molvaer፤ 1987፣14፤ Desta፤ 2004፣67 እና Yilma and et al፤ 1996፣4-5)።

### 3.1.4.1 ከእፀ መድኃኒት ተቀምሞ የሚሰጥ ህክምና

Young፤ ከእፀ መድኃኒት የሚሰጥ ህክምና ከእፀዋት የሚገኙ ግብዓቶችን መሰረት ያደረገ የህክምና አይነት ነው። በዚህ ስር የሚመደቡ የባህል ሐኪሞች "የእፀ መድኃኒት አዋቂ/ባለሙያ" በመባል የሚጠሩ ሲሆን ከሚሰጡት አገልግሎትና ሙያ አንጻር ሲታይ ከፍተኛውን ቁጥር እንደሚይዙ የዘርፉ ምሁራን ያትታሉ (1970፣24)። የእፀ መድኃኒት ባለሙያዎች በብዛት እፀዋትን ለመድኃኒትነት ስለሚጠቀሙ በዚሁ ስያሜ ይጠራሉ። እነዚህ ባለሙያዎች የተወሰኑ ማዕድናትን እና እንስሳትን በመጠቀም ከተፈጥሮ ግብዓቶች መድኃኒት ይቀምማሉ። እነዚህ ባለሙያዎች በአካባቢያቸው የሚበቅሉ የእፅዋት አይነቶችን፣ መገኛ ቦታዎችን፣ የአካባቢያቸውን የአየር ንብረት፣ የበሽታ አይነቶችና የህክምና አሰጣጥ መመሪያዎችን፣ በሽታ የመለያ ዘዴዎችን የመድኃኒት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣ አቀማመምና አሰጣጥ ስልቶችን በማቀነባበር ረገድ የሙሉ፣ ወይም የግማሽ ቀን ሰራተኛ ሲሆኑ ይችላሉ (Chavuduka፣ 1994፣ 56፤ Yilma and et al፣1996፣5፤ Read፣ 1966፣ 19) ።

Wondwosen ደግሞ የእፀ መድኃኒት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ሥርዓት ላይ ጉልህ ሚና አላቸው። እነዚህ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ከዕፀዋት ስር፣ ቅጠል፣ ግንድ፣ ፍሬ፣ አበባ፣ ዘር፣ ቅርፊት፣ ቁጥቋጦ፣ ፈሳሽ፣ ተቀጽላ፣ አትክልትና ፍራፍሬ መድኃኒት በማዘጋጀትና ሁሉንም የእፀዋት አካል በሚያስብል መልኩ ጥቅም ላይ በማዋል ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ (1999፣ 29-30፤ 2006፣79) ።

### 3.1.4.2 በወጌሻ የሚሰጥ ህክምና

ይህ የህክምና አይነት ከአጥንት ጋር በተያያዘ የሚሠጡ ህክምናዎችን መሰረት ያደረገ ነው። እንደ Yilma and et al ገለጻ በዚህ ምድብ ስር የሚካተቱ ባለሙያዎች "ወጌሻ" በመባል

ይጠራሉ። ወጌሻ ሲባል አጥንት ጠጋኞችን፣ ጥርስ አውላቂዎችን ያካትታል (1996፣ 5)። Young ደግሞ መለስተኛ የአጥንት ጉዳቶችን፣ የተሰነጠቁና የተሰበሩ አጥንቶችን የሚጠግኑ ባለሙያዎች "ወጌሻ" ይባላሉ። እነዚህ ወጌሻዎች የተለያዩ እፀዋትን እና እንስሳትን እንደ አመቺነታቸው ከሞላ ጎደል በመጠቀም የተሰበሩ፣ የተሰነጠቁና የወለቁ አጥንቶችን በማስተካከል፣ በማገምና በመጠገን የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ (1970፣ 34)።

#### 3.1.4.3 በመንፈሳዊ ኃይል የሚሰጥ ህክምና

በዚህ ክፍል ሁለት አይነት ህክምናዎች ይሰጣሉ። አንደኛው በሃይማኖት ተቋም ስር የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው ከመናፍስት በሚገኝ እውቀትና ክህሎት የሚሰጥ ነው። በመጀመሪያው የሚካተቱ የህክምና ባለሙያዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመታገዝ ፀሎት በማድረግ፣ ፀበል በመርጨት፣ መስቀል በማሳለም፣ ቅዱስ ቁርባን በመስጠት፤ በቄሶች፣ በሼኮችና በመሳሰሉት ባለሙያዎች የሚደረግ ነው። እነዚህ ባለሙያዎች የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት፣ ፀበል በመርጨት እና የመሳሰሉትን ቅዱስ ተግባራት በመፈጸም የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። በሁለተኛው ምድብ የሚጠቀሱ ባለሙያዎች ከመናፍስት በሚያገኙት እውቀትና ክህሎት በመታገዝ የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። እነዚህን ሙያተኞች ከዛር መንፈስ፣ ከአጋንንት፣ ከሰይጣን እና ከመሳሰሉት መንፈስ፤ በሚያገኙት እውቀት እና ጥበብ በመታገዝ ህመምተኛን እንደሚፈውሱ ይገልፃሉ(Yilma and et al፣ 1996፣ 5፤ Desta፣ 2004፣ 67)።

#### 3.1.4.4 በቅይጥ ቴክኒካዊ እውቀት የሚሰጥ ህክምና

በቅይጥ ቴክኒካዊ እውቀት የሚሰጥ ህክምና የተለያዩ ክሂሎችን እና አካባቢያዊ ልምዶችን መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ ስር የባህል አዋላጆች፣ አጋሚዎች፣ የሰውነትና የጥርስ ነቃሾ ይካተታሉ። የባህል አዋላጆች ከእርግዝና እና ከህፃናት ማዋለድ ጋር በተያያዘ የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። ይህን የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች በብዛት ሴቶች ሲሆኑ ግርዛት፣ ማገም፣ ንቅሳት፣ የሰውት ቁስል ማድረቅን በተጓዳኝ ያከናውናሉ (Yilma and et al፣ 1996፣ 5፤ Desta፣ 2004፣ 67)።

### 3.1.5 በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች

Sofowora (1982፣26-28) በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች ከተለያዩ ገጽታዎች አኳያ ሊታኝና ሊመረመር ይችላል። በሽታን የመለያ ዘዴዎች እንደ የባህል ሐኪሞቹ እውቀት፣ ማኅበራዊ ልማድ፣ ባህልና ስርዓት ከቦታ ቦታ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ ይለያያል። ስለዚህም የባህል ሐኪሙ የሚኖርበትን ማኅበረሰብ ልምድና አካባቢ መሰረት በማድረግ

የበሽታዎችን መንስኤ፣ አይነትና ጸባይ ይገነዘባል። ማኅበረሰቡ የበሽታ መንስኤ ናቸው ብሎ የሚፈርጃቸውን አለማዊ (ድንገተኛ አደጋ፣ የተበከለ ምግብ፣ እርዛትና ርሃብ) እና መለኮታዊ (ከፈጣሪ፣ ከመናፍስት፣ ከጥንቆላ፣ ከድግምት፣ ከአስማት) ምክንያቶች፣ ለባህል ሐኪሙ እውቀት እና ሙያ መነሻ መሰረት በመሆናቸው፤ የህክምና አሰጣጥ ስርዓቱና ልምዱ እንደ ባህል ሐኪሙ ክህሎትና ማኅበረሰባዊ ልማድ ይወሰናል።

እንደዘርፉ ምሁራን ገለጻ፣ በባህላዊ ህክምና የተለመዱ የበሽታ መለያ ዘዴዎች እይታዊ ምርመራ ክሊኒካዊ ምርመራ ባዮሎጂካዊ ምርመራ እና የህሙማንን ማኅበራዊ ግንኙነት በማጤን የሚባሉት ናቸው። የባህል ህክምና ባለሙያዎች ከነዚህ ጎቅል ይዘት አንጻር በመነሳት የበሽታን መንሥኤ፣ ምልክት፣ ፀባይና አይነት ይለያሉ (Konadu፣ 2007፣67፤ Young፤ 1970፣34-36፤ እና Sofowora፣ 1982፣29-30)። ከጥለን ዘዴዎቹን በዝርዝር እንመለከታለን፦

### 3.1.5.1 እይታዊ ምርመራ

የባህል ሐኪሞች የተለያዩ የበሽታ አይነቶችን ለመለየት እይታዊ ምርመራን[14] አዘውትረው ይጠቀማሉ። እይታዊ ምርመራ ሲባል የህመምተኛውን አይን፣ ቆዳ፣ ሽንትና ሰገራ በመመልከት እና በመፈተሽ የህመሙን አይነት ለመለየት የሚደረግ ሙከራ ነው። ይህ ተግባር በዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ተዘውተሮ የተለመደ ቢሆንም በባህላዊ ሐኪሞች ተግባራዊ መሆኑ ሊደንቀን አይገባም በማለት Sofowora አትቶዋል። ከዚህ አንፃር የባህል ህክምና ባለሙያዎች የህሙማንን በሽታ ለመለየት፣ የበሽታውን ምልክትና ፀባይ ለመረዳት የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን እና ከሰውነት የሚወጡ ፍሳሾችን በማጤን መድኃኒት ቀምመው ለህሙማን እንደሚሰጡ ገልፀዋል(1982፣29) ።

### 3.1.5.2 ክሊኒካዊ ምርመራ

ክሊኒካዊ ምርመራ ሲባል የህመምተኛውን አጠቃለይ አቋም፣ የመገጣጠሚያ አካላት እንቅስቃሴ፣ የልብ ምት፣ የሰውነት ትኩሳት፣ የጅማት መሸማቀቅ፣ የአጥንት መሰንጠቅና መሰበር፣ የሰውነት መጠን መቀነስ፣ መዝለፍለፍ እና መድከም፣ እራስን መሳት፣ ማላብ፣ የሆድ ቁርጠት እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤ (Young፣ 1970፣2-4፤ Konadu፣ 2007፣ 67)።

ከነዚህ ገለጻ በመነሳት፤ የባህል ሃኪሞች የህሙማንን አካላዊ ሁኔታ (አቋም) በመፈተሽ የህመሙን አይነት፣ የመገኛ ቦታ፣ ሁኔታና ምልክት ይለያሉ ማለት ይቻላል። ከዚህም

---

[14] በመስክ ስምሪቴ፤ የባህል ሐኪሞች በአብዛኛው እይታዊ ምርመራን በመጠቀም በሽታን እንደሚለዩ የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ ፣ መሪጌታ መስፍን ገብሬ እና ሌሎችም ገልጸዋል።

በተጨማሪ የህሙማንን ሰውነት በማንቀሳቀስ፤ የጡንቻ መሸማቀቅ፣ ወለምታ፣ የአጥንት ስብራትና መሰንጠቅ፣ የሰውነት መዝለፍለፍና እራስን መሳት በባህል ሐኪሞች ይጤናሉ ማለት ይቻላል።

### 3.1.5.3 ባዮሎጂካል ምርመራ

ባዮሎጅካል ምርመራ በዘመናዊ ህክምና በስፋት የሚተገበር ቢሆንም በባህላዊ ሐኪሞች በተወሰነ መልኩ ተግባራዊ ይሆናል። የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ሳይንስ ያፈራቸውን መሳሪያዎች በመጠቀም በቤተ-ሙከራ ምርመራ የሚያካሂዱ ሲሆን የባህል ሐኪሞች ደግሞ የሰውነት ህዋሶቻቸውን በመጠቀም የህመሙን አይነት ይለያሉ። የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ሳይንሱ ካፈራቸው መመርመሪያ መሳሪያዎች አንድም ከግንዛቤ ማነስ ወይም አጋጣሚን ካለማግኘት የተነሳ ዘመኑ ካፈራቸው ቴክኖሎጂዎች የተፋቱ ናቸው ማለት ይቻላል። የባህል ሐኪሞች የስሜት ህዋሶቻቸውን በመጠቀም፤ በማሽተት፣ በመንካት እና በማየት በሽታዎችን እንደሚለዩ Sofowora ይገልጻሉ (1982:30)።

### 3.1.5.4 የህሙማንን ማኅበራዊ ሁኔታ በማጤን

የባህል ሐኪሞች የህሙማንን አጠቃላይ ማኅበራዊ ሁኔታና ግንኙነት በመገንዘብ፣ ፍላጎትና የሰውነት እንቅስቃሴ በማጤን የህመሙን አይነት ይለያሉ። በዚህ የምርመራ አይነት ህሙማን የሚውሉበትን፣ የሚኖሩበትን፣ የሚሰሩትንና የቤተሰቦቻቸውን እንክብካቤ ያጤናሉ (ይመለከታሉ)። ይህ የምርመራ ስልት በባህላዊ ሐኪሞች የተዘወተረና የተለመደ ነው። የባህል ሐኪሞች አንዳንድ ጊዜ የህመምተኞቻቸውን የሕይወት ታሪክ በማዳመጥ፤ የህመማቸውን ሁኔታ፣ መንስኤና ምክንያት ይገነዘባሉ፤(Sofowora፣1982፣29)።
በአጠቃልይ የህሙማንን በሽታ ለመለየት የባህል ሐኪሞች የተለያዩ ሙከራዎችንና ዘዴዎችን ተግባራዊ እደሚያደርጉ ከዚህ በላይ የቀረቡ መረጃዎች ያስረዳሉ። Pankhurst ደግሞ የባህል ሐኪሞች ለህሙማን እንክብካቤና በሽታን ለመከላከል ሲሉ፤ ህሙማን ከሰው እንዳይገናኙ በማድረግ፣ መለስተኛ ቀዶ ጥገና በማካሄድ፣ በመብጣት፣ በመሰንጠቅ፣ በመተኮስ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ድርጊቶችን በመፈጸም ህሙማንን እንደሚንከባከቡና በሽታን እንደሚከላከሉ ይገልፃሉ (1990፣27)።

## 3.1.6 የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ

በባህል ህክምና ስርዓት ከመደኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የመድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ ስልቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ። የባህል ሐኪሞች የእፀዋት መድኃኒቶችን በሁለት መልኩ ይሰበስባሉ። በአካባቢያቸው በማልማት እና ከዱር በመሰብሰብ መድኃኒት

ያዘጋጃሉ (Assefa፣ 1992፣88)። Alemayehuም መድኃኒት የመቀመም እውቀት ያላቸው ሰዎች ከቤት ወይም ከዱር የሰበሰቧቸውን ግብዓቶች፤ በተለያየ ሁኔታ ቀምመው በማዘጋጀት ይሰጣሉ፤(1984፣124)።

የባህል ሐኪሞች እፀ መድኃኒቶችን በተለያየ መልክ አዘጋጅተውና ቀምመው ያስቀምጣሉ። እነዚህ ባለሙያዎች ከእፀዋት አበባ፣ ፍሬ፣ ቅጠል፣ ስር፣ ቅርፍት...የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም መድኃኒት ይቀምማሉ። የአቀማመሙ ሂደትም በማድረቅ፣ በመሰለቅ፣ በመዘፍዘፍ፣ በመቀቀልና በማጥለል...፤የሚዘጋጅ ሲሆን በሚጠጣ፣ በሚሸተት፣ በሚታኘክ...መልኩ ይሰጣሉ (Baquar፣1995፣ 149-150)።

Young ደግሞ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ለመሰብሰብ፣ ለመቀመምና ለመስጠት በቂ እውቀትና ተሰጥኦ ያስፈልጋል። ለዚህም እፀዋት የሚበቅሉበትን ቦታ፣ የሚጠሩበትን ስያሜ፣ የሚሰበሰቡበትን ጊዜና ወቅት ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚገባ ያትታሉ። ከዚህም በተጨማሪ የመድኃኒት ሰብሳቢው ብቃት፣ የመሰብሰቢያ ቁሳቁስ፣ እፀዋት የሚሰበሰቡበት ሁኔታ (Situations) ከግምት ውስጥ እንደሚገቡ ያስረዳሉ (1970፣45)።

እንደ Alemayehu ገለፃ፤ የኢትዮጵያ የባህል መድኃኒት አሰጣጥና መመሪያ እንደ መድኃኒት ሰጭው እውቀት ይወሰናል። ምንም እንኳ የመድኃኒት አሰጣጡና አተገባበሩ ቢለያይም በዋናነት በመጠጣት፣ በመቀባት፣ በማሸተት፣ በመማግ፣ በሚታኘክ፣ በማጨስና በክታብ መልክ ተሰርቶ በአንገት ላይ ማንጠልጠል የሚባሉትን ያጠቃልላል። ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያን የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ እንደሚከተለው ገልጸውታል፦

1. በእፀዋት ግብዓቶች ላይ በመድገም (አስማታዊ ጥበብን በመጠቀም) የሚሰጥ መድኃኒት
2. ህመምተኛው በሌለበት ወይም በህመምተኛውና በመድኃኒቱ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይኖር ዕፅን በማዘዝ ህመምተኛን መፈወስ
3. ህመምተኛው ሳይውጥና ሳይቀባ እንዲያንጠለጥለው (እንዲይዘው) በማድረግ የሚሰጥ መድኃኒት
4. እንደ ዘመናዊ ህክምና፤ በባህላዊ ህክምና ስርዓትም በአፍንጫ ወይም በአፍ የሚሸተቱና የሚማጉ፣ የሚቀቡና በመርፌ መልክ የሚሰጡ መድሃኒቶች ...ተጠቃሽ ናቸው (1984፣124)።

በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋትን በሁለት መልኩ ይሰበሰባሉ። አንደኛው እፀዋትን በአካባቢ በማልማት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከዱር የሚገኙ እፀዋትን በመሰብሰብ መድኃኒት ያዘጋጃሉ። የተዘጋጁ እፀዋት እንደ የባህል

ሐኪሙ እውቀት እና አላማ በተለያየ መልኩ ተቀምመው ይዘጋጃሉ። እነዚህ መድኃኒቶች በተለያየ መልክ የሚሰጡ ቢሆንም በዋናነት፣ የሚጠጡ፣ የሚሸተቱ፣ የሚቀቡና አንገት ላይ በክታብ መልክ የሚንጠለጠሉ መሆናቸውን ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ምንጮች ያስረዳሉ።

## 3.1.7 የባህላዊ ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶች

የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶች እንደየማኅበረሰቡ ልማድ እና ትምህርት ይለያያሉ። Alemayehu የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችን በሶስት ይፈረጇቸዋል። አንደኛ ከቤተሰብ በውርስ (በዘር) በሚገኝ እውቀት፣ ሁለተኛ ሙያው (እውቀቱ) ያላቸውን ሰዎች ለረጅም አመት በማገልገልና አብሮ በመስራት በሚገኝ ጥበብ፣ ሶስተኛ አውደ ጥበብን በመስረቅ የህክምና እውቀቱ እንደሚተላለፍ አትተዋል፣(1984፣119)።

Young ደግሞ፣ የባህል ህክምና ጥበብ በአራት መንገድ ሊተላለፍ እንደሚችል ይጠቁማሉ። አንደኛ ከጓደኛ በመማር፣ ሁለተኛ የአብነት መምህሩን ለረጅም አመታት በቅንነት በማገልገል፣ ከሚገኝ ልምድና ስልጠና፣ ሶስተኛ እውቀቱን በገንዘብ በመግዛት፣ አራተኛ የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ በሚያደርጉት የእርስ በእርስ የሃሳብ ልውውጥ፣ የህክምና እውቀቱ እንደሚተላለፍ ገልፀዋል (1970፣143)።

## 3.1.8 የባህላዊ ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት

የባህል መድኃኒት ምስጢራዊ መሆኑ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎችን ለመጪው ትውልድ በውል እንዳይተላለፍ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ አንድ የባህል ሐኪም ሊሞት በተቃረበበት ሰዓት እና እለት በጣም ለሚቀርቡት ቤተሰቦቹ በቃል ያስተላልፋል። በቃል የሚተላለፈው መረጃ ደግሞ የተጓደለ፣ የተቆራረጠ፣ የተዘለለ እና የአድማጩን ክህሎት የሚጠይቅ በመሆኑ ቀድሞ የነበረው እውቀት ውጤት አልባ ይሆናል፣ (Kokawaro፣ 1976፣1፣ Fekadu፣ 2001፣27)።

Wondwosen ደግሞ ባህላዊ ሐኪሞች ያላቸውን የህክምና እውቀት ይደብቃሉ። በተለይ የመድኃኒቱን አሰባሰብ፣ አቀማመምና አሰጣጥ በተመለከተ ከራሳቸው ውጭ ሌላ ሰው በፍጹም እንዲያውቅ አይፈልጉም። ይህ ሲባል ግን መንግስታዊ በሆኑ ጉባኤዎች፣ ሰሚናሮች፣ ሲምፖዚየሞች ማለት አይደለም። እነዚህ ባለሙያዎች መንግስታዊና ተቋማዊ በሆኑ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት መድኃኒቱን እንዴት እንደሚሰበስቡ እና እንደሚቀምሙ በልበ ሙሉነት ይናገራሉ (2006፣48)።

Young የባህል ሐኪሞች የመድኃኒት አሰባሰባቸው፣ ቅመማና አሰጣጥ ቴክኒካቸው በምስጢር የተያዙ ናቸው። እነዚህ የህክምና ባለሞያዎች ህዝቡ በተሰበሰበበት አደባባይ ስለ

ባህላዊ መድኃኒት ጠቀሜታ እና ጉዳት አይመሰክሩም፡፡ አጠቃላዩ ተግባራቸው ከህዝቡ እይታ የተሰወሩ በመሆናቸው ለመድኃኒት የሚጠቀሙባቸው ግብዓቶች፣ ቁሳቁሶች እና መረጃዎች ምስጢራዊ ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን በህክምና ባለሞያዎች መካከል የእውቀትና የልምድ ሽግግር አይኖርም ማለት አይደለም በማለት አትተዋል (1970፣51-52)፡፡

## 3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከባህላዊ መድኃኒት (ህክምና) ቅመማና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የተካሄዱ ጥናታዊ ስራዎች ይዳሰሳሉ፡፡ የዚህ ቅኝት ዓቢይ ዓላማ ተዛማጅ የሆኑ ጥናቶችን መርምሮ፤ የጥናታቸውን ትኩረት መጠቆም፣ ከቀዳሚ ጥናቶች የሚለዩበትን ማመልከት፣ ከኔ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት መግለጽ፣ ይህ ጥናት የሚሞላውን ክፍተት እና ለመስኩ ጥናት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ መጠቆም የሚሉ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ሶስት፣ ለስነ-ሰብዕ ሶስት፣ ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ሁለት፣ ለታሪክ ትምህርት ክፍል አንድ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ በድምሩ ዘጠኝ ጥናታዊ ስራዎች የተቃኙ ሲሆን፤ ለፒ.ኤች. ዲግሪ ማሟያ ቀርበው የታተሙ ሶስት ጥናታዊ ጽሑፎች፤ ሁለት ለአለም አቀፍ ኮንፈረንስ የቀረቡ የምርምር ውጤቶች በድምሩ አስራ አራት የሚሆኑ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡

### 3.2.1 ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች

እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በባህላዊ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ዙሪያ ሶስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበዋል፡፡

ከነዚህ ጥናቶች መካከል አለማየሁ ዘሪሁን ይጠቀሳሉ፡፡ አለማየሁ "የኑዌር ማኅበረሰብ ባህላዊ ሕክምና እውቀት፣ አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ" በሚል ርዕስ በ 2000 ዓ.ም ቀረቡት ጥናት አንዱ ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የኑዌር ማኅበረሰብን የባህል ህክምና እውቀት፣ አመለካከት፣ የመድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደት ከነክዋኔው ምን እንደሚመስል መርምሮ ማሳየት ነበር፡፡ በአካባቢው በባህላዊ ህክምና የሚድኑ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ህክምናውን የሚሰጡ እነማን ናቸው? የመድኃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደት ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ መልስ ተሰጥቷል፡፡

በኑዌር ማኅበረሰብ ባህላዊ ህክምና ከሚድኑ በሽታዎች መካከል የሰውነት ቁስል፣ ወባ፣ የሆድ ትላትል፣ ስብራት እና የመሳሰሉትን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በአካባቢው ከሚከሰቱ የጤና ችግሮች ለመፈወስ፤ የተለያየ የህክምና እውቀት ባላቸው ቱትዋል (tetwal)፣ ይስ

(yieth)፣ ጋም (gam) እና ጎክ (gok) በሚባሉ የባህል ሐኪሞች አማካይነት ህክምና እንደሚደረግ አለማየሁ በጥናታቸው አትተዋል። እነዚህ የባህል ህክምና ባለሙያዎች መድኃኒቶችን በአብዛኛው ከእፅዋት፣ ቀሪውን ደግሞ ከእንስሳትና ከማዕድናት ውጤቶች በመቀመም፤ ቴክኒካዊ የህክምና ተግባራትን በማከናወን እና በአንዳች መንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ የህብረተሰቡን የጤና ችግር እንደሚፈቱ ጠቁመዋል። ከዚህም በተጨማሪ የህክምና ስርዓቱ በብዛት በመንፈሳዊ ሐኪሞች የሚተገበር መሆኑን ገልጸዋል።

ምህረት ዳኘው "በአዲስ አበባ ከተማ የባህል መድኃኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም" በሚል ርዕስ ሐምሌ 2000 ዓ.ም ጥናት አቅርበዋል። የጥናታቸው ማዕከላዊ ጉዳይ፤ የዘመናዊ ህክምና አገልገሎት በተሻለ ሽፋን የሚሰጥበት የአገራችን ዋና ከተማ፤ የባህል ህክምና በስፋት የሚሰጥበትን ምክንያት፤ በመረጃ በማስደገፍ የህክምና አሰጣጡን መከታተልና ውጤታማነቱን ከታማሚዎች ማረጋገጥ፣ ከዚህም በተጨማሪ፤ እምነት በባህላዊ ህክምና ያለውን ሚና ማሳየት የሚሉ ናቸው፡

ምህረት በጥናታቸው ሂደት ዘመናዊ ህክምና በተሻለ ሁኔታ በሚገኝበት አዲስ አበባ፣ የባህላዊ መድኃኒት ህክምና አገልግሎት በስፋት እየተሰጡ መሆኑን ጠቁመዋል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች አዘውትረው የሚፈውሷቸው በሽታዎች አልማዝ ባለጭራ፣ ኪንታሮት፣ ችፌ፣ የወፍ(የጉበት) በሽታ እና የሰውነት ቁስል እንደሆኑ ገልጸዋል።
በጥናታቸው ማጠቃለያ ዘመናዊ ህክምና በተሻለ ሁኔታ በሚሰጥበት አዲስ አበባ፣ የባህል ህክምና አገልግሎት በስፋት እየተሰጠ መሆኑን አረጋግጠዋል። ይህ ሲባል ግን የበሽታን ስም የዘረዘሩ ሁሉ እውነተኛ የባህል ሐኪም ናቸው ማለት ባይቻልም የሚመለከታቸው የጤና ቢሮዎች ጉዳዩን በመፈተሽና በመመርመር እውቀቱና ክህሎቱ ላላቸው ባለሙያዎች ህጋዊ ፍቃድ መስጠት እንዳለባቸው አትተዋል።

የምህረት ጥናት ከአለማየሁ አንጻር ሲታይ፤ በክለሳ ድርሳናቸው በቂ ንድፈ ሃሳቦችን (የቲዎሪ መጻሕፍትን)፣ ጽንሰ ሀሳቦችንና ትንታኔዎችን አቅርበዋል ማለት አይቻልም። የተጠቀሟቸው መጻሕፍት ከማነሳቸው ባሻገር እንደ አቢይ ንድፈ ሃሳባዊ መረጃ መጻሕፍት የሚጠቀሱ አይደሉም። ከነዚህ መጻሕፍት ይልቅ ሃይማኖት እና እምነት በባህላዊ መድኃኒት ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ የሚያትቱ መጻሕፍት ይበዛሉ። ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ በክለሳ ድርሳናቸው ክፍተት ይታያል።

መስፍን ፍቃዱ በ2002 ዓ.ም በባህል መድኃኒት ዙሪያ ጥናት አድርገዋል። መስፍን ያቀረቡት ርዕስ "የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዎ" የሚል ነበር። የጥናታቸው ትኩረት ሃገረሰባዊ መድኃኒቶች አቀማመማቸውና

ባህላዊ አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ የባለሙያዎቹ የህክምና ጥበብ መነሻና መተላለፊያ መንገድ ምን እንደሆነ መጠቆም፣ ለሃገረሰባዊ መድኃኒቶች መሰብሰቢ የሚያገለግሉ ቁሶች ትዕምርታዊ ፋይዳ የሚሉትን በጥናታቸው መርምረዋል።

በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የባህል ሐኪሞች በብዛት መሪጌታዎች፣ ደብተራዎች፣ ሃጂዎች እና ሼኾች ሲሆኑ የህክምና ጥበቡን ከየመጡበት ሃይማኖታዊ ተቋም እንደተማሩት አትተዋል። ሀገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎች ለበሽተኞች የሚያደርጉት የሥነ-ልቡና ድጋፍ እንዲሁም ህብረተሰቡ በመድኃኒቶቹ እፈውሳለሁ ብሎ ማሰቡ የህክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው ጠቁመዋል። "ከመድኃኒት ምጣኔና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በአብዛኛው ህሙማን ላይ ጉዳት እንደሚያደርሱ" በጥናታቸው አረጋግጠዋል። ይህን ችግር ለመፍታት ዘመናዊና ሃገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎችን በማቀራረብ የእውቀት ሽግግር የሚያደርጉበትን እና በጋራ የሚሰሩበትን ስልት መንደፍ የተሻለ መሆኑን በመጠቆም ጥናታቸውን ቋጭተዋል።

### 3.2.2 ለስነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች

በዚህ የትምህርት ክፍል ሶስት ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ተቃኝተዋል። ከነዚህ ጥናቶች መካከል Mirgissa ቀዳሚውን ቦታ ይዘዋል። Mirgissa (1993) "Indigenous Medical Beliefs and Practices among the Oromo of Illubabor" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል። የጥናታቸው ትኩረት በኢሉባቦር የሚካሄደውን የባህል ህክምና ከማህበረሰቡ እምነትና ተግባራት አንፃር መመርመር ነበር።

እንደ Mirgissa ገለጻ ዘመናዊ ህክምና ከመስፋፋቱ በፊት ባህላዊ ህክምና በማኅበረሰቡ ዘንድ ለበርካታ ዓመታት ሲተገበር የኖረ ነው። ባህላዊ ህክምና የማህበረሰቡን ልማድ፣ እምነት፣ እና አመለካከት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከማኅበረሰቡ አምልኮና ተግባራዊ አውድ አንጻር መቃኘት እንዳለበት አትተዋል። ከዚህ አንጻር በኢሉባቡር ኦሮሞ ልማድ፤ የባህል ህክምና እውቀት የሚገኘው ራቢ (Rabby) ከሚባል ሃገረሰባዊ እምነት እንደሆነ ገልጸዋል።

Mirgissa የባህል ህክምና ባለሙያዎች መንፈሳዊና አለማዊ በመባል በሁለት እንደሚከፈሉ አብራርተዋል። በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ ህመምተኛን ለመፈወስ ጥረት የሚያደርጉ የባህል ሐኪሞች የጫት መቃም ስነ-ስርዓት እንዳላቸው ገልጸው በሽታን ለማስወገድ፣ ህመምተኛን ለመፈወስ፤ ልመና፣ ጸሎትና ዱአ (Duai) እንደሚያደርጉ አትተዋል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች በአካባቢው ልማድ አጠራር "Shekota" ፣ "Woliy" እና "Quallu" በመባል የሚታወቁ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ዱአ (Duai) በማድረግ ሕመምተኛን

እንደሚፈውሱ ጠቁመዋል። ዓለማዊ የባህል ሐኪሞች የሚባሉት ደግሞ በአካባቢው የሚገኙ እፀዋትን፣ እንስሳትንና ማዕድናትን እንደግብአት በመጠቀም መድኃኒት አዘጋጅተው የሚሰጡ ባለሙያዎች ናቸው፤ በማለት አብራርተዋል። በመጨረሻም በኢሉባቡር አካባቢ ወፍ፣ ወባ፣ የእብድ ውሻ በሽታና የሰውነት ቁስል አዘውትረው የሚከሰቱ ሲሆን እነዚህን በሽታዎች ለመፈወስ ከዘመናዊ ህክምና ይልቅ ባህላዊ ህክምና ተመራጭ እንደሆነ በመጠቆም ጥናታቸውን አጠቃለዋል።

ከMirgissa በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ ባህላዊ ህክምናን ያጠኑ Abraraw ናቸው(1998) “Traditional Medicine in an Urban Center: Beliefs and Practices (The Case of Dessie Town, Northern Ethiopia)” በሚል ርዕስ ለሥነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል አቅርበዋል። የጥናታቸው አላማ በደሴ ከተማ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ለጤና የሚሰጡት ምላሽና፣ ለባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ያላቸው አመለካከት፣ የባህል ሐኪሞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና፣ ባህላዊ ህክምና ለዘመናዊ ህክምና ያለውን አጋዥነት በመመርመር ላይ ያተኮረ ነበር።

እንደ Abraraw ገለጻ፤ በደሴ ከተማ ሰዎች የጤና እክል ሲገጥማቸው ሁለቱንም የባህል ህክምና አይነቶች በአማራጭነት ይጠቀማሉ። በአካባቢው ዘመናዊ ህክምና የሚገኝ ቢሆንም አብዛኛው ማኅበረሰብ ባህላዊውን የህክምና ዘርፍ እንደሚመርጥ በጥናታቸው አረጋግጠዋል። ለዚህም ባህላዊ ሐኪሞች ከማኅበረሰቡ በአካል፣ በመንፈስና በስነ-ልቦና የሚገናኙ በመሆናቸው፣ በተፈጥሯዊም ሆነ በመለኮታዊ ሐይል የሚመጡ የጤና ጠንቆችን በመፈወስ በኩል ጉልህ ሚና አላቸው በማለት አትተዋል።

በአጠቃላይ ባህላዊ ህክምና በማህበረሰቡ ዘንድ ተመራጭ ያደረገው መንፈሳዊና መለኮታዊ የህክምና አማራጮችን ያካተተ መሆኑ፣ የማህበረሰቡን የኢኮኖሚ አቅም ያገናዘበ፣ የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች እንደማህበረሰቡ ልማድ እና ሁኔታ ተዓምራዊ ፈውስ የሚያደርጉ በመሆናቸው፤ የህክምና ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው አረጋግጠዋል። በዘመናዊ እና በባህላዊ ህክምና ያለውን ግንኙነት መቃኘታቸው፣ የማኅበረሰቡን የህክምና አማራጭ መዳሰሳቸው፣ ማኅበረሰቡ የትኛውን የህክምና ዘርፍ ተመራጭ እንደሚያደርግ ማጥናታቸው ከMirgissa እንዲለዩ አድርጓቸዋል።

በሶስተኛ ደረጃ በባህላዊ መድኃኒት ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ ባለሙያ Zerihun Doda ናቸው። Zerihun (2001) “Culture, Belief and Mental Illness Among the Zay” በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የጥናታቸው ትኩረት በዛይ ማኅበረሰብ ለአእምሮ በሽተኞች ያለው

አመለካከት፣ ክትትልና ቁጥጥር መጠቀም፤ ለአእምሮ ህመም መንስኤ የሆኑ መለኮታዊ፣ ማኅበረባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና መልክዓ ምድራዊ መንስኤዎችን መግለጽ ነበር፡፡

Zerihun የአእምሮ ህመም ከመንፈስ ጭንቀት፣ ከመልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ ከኢኮኖሚ ቀውስ እና ከፖለቲካ አንጻር የሚከሰት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ለአእምሮ ህመምተኞች የሚደረገው እንክብካቤና ከማኅበረሰቡ ያለው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በአካባቢው የአእምሮ ህመምተኞችን በመፈወስና በመንከባከብ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው የዛይ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፣ የኦሮሞ ባህላዊ እምነትና ዘመናዊ ህክምና በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በቤተሰብ፣ በጎረቤት፣ በግለሰቦችና በማኅበረሰቡ ዘንድ በቂ ትምህርትና ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ፣ ለአእምሮ ህመምተኞች ልዩ ትኩረትና እንክብካቤ መደረግ እንዳለበት አትተዋል፡፡

የአእምሮ ህመምን በተመለከተ በባህላዊ እና በዘመናዊ ሐኪሞች መካከል የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡ ባህላዊ ሐኪሞች በጸበል፣ በጸሎት እና በመለኮታዊ ሐይል በመታገዝ ህመምተኞችን እንደሚፈውሱ የተገለጸ ሲሆን የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ከዘመናዊ ህክምና ውጪ የሚደረጉ ህክምናዎች በታካሚው ላይ የባሰ ጉዳት እንደሚያስከትሉ ተጠቁሟል፡፡ በጥናታቸው ማጠቃለያ የስነ-ልቡና አማካሪዎችንና የባህል ሐኪሞችን በማቀናጀት የሕክምና አገልግሎቱ፣ የጤና አጠባበቅ ስርዓቱ እንዲሻሻል፤ በሁለቱ መካከል የልምድ ልውውጥ ቢደረግ ለአእምሮ ህመምተኞች ተገቢውን ህክምና እና እንክብካቤን ለመስጠት ያስችላል በማለት አጠቃለዋል፡፡

Zerihun የአእምሮ ህመምተኞችን ነጥለው ማጥናታቸው ከቀደሙ ጥናቶች ውስንነትና ግልጽነት ይታይበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአእምሮ ህመም ጋር በተያያዘ ባህላዊውንና ዘመናዊውን የህክምና ዘርፍ የዳሰሱ በመሆኑ፣ ለአእምሮ ህመም መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችን መመርመራቸው፣ በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት መፈተሻቸው ከቀደሙ ጥናቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡

### 3.2.3 ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናቶች

ባህላዊ መድኃኒትን በተመለከተ Mekonen Workineh በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ Mekonen (2008) "The Attitude of Traditional Practitioners Biomedical workers and the public towards traditional Medicines with Particular Reference to Rabies Healers in West Gojjam" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናታቸው ትኩረት የእብድ ውሻ በሽታን ለመፈወስ በሚደረገው የባህል ህክምና፤ የባህል

ሐኪሞች፣ የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች እና ህዝቡ ያላቸውን አመለካከት ምን እንደሚመስል መመርመር ነበር።

እንደ Mekonen ገለጻ ማኅበረሰቡ ከእብድ ውሻ በሽታ ለመፈወስ ከዘመናዊ ህክምና ይልቅ ባህላዊ ህክምናን እንደሚመርጥ በጥናታቸው አትተዋል። በባህላዊ ህክምና የሚሰጠው አገልግሎትና ፈውስ በባህል ሐኪሞቹና በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ሲሆን የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች በመስኩ ለሚካሄደውን ህክምና አሉታዊ አመለካከት ያላቸው መሆኑን አረጋግጠዋል። ማኅበረሰቡ ባህላዊ ህክምናን ተመራጭ ያደረገው፤ የባህል ሐኪሞች በየቦታው መገኘታቸው፣ ለእብድ ውሻ በሽታ የሚሰጡት መድኃኒት ፍቱን በመሆኑ፣ በዝቅተኛ ዋጋ አገልግሎት መስጠታቸው የህክምና ዘርፉን ተመራጭ አድርጎታል። በተቃራኒው የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች በባህላዊ መንገድ በሚሰጠውን አገልግሎት ከመድኃኒት ምጣኔያቸው፣ ከንጽሕና አጠባበቃቸው እና ከአሰጣጣቸው ጋር በተገናኘ ለመስኩ ለሚካሄደው ህክምና ዝቅተኛ አመለካከት እንዳላቸው ገልጸዋል።

Mekonen በባህላዊ ህክምና ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ለእብድ ውሻ በሽታ የሚሰጠውን ህክምና ለይተው ማጥናታቸው፣ ማህበረሰቡ ከእብድ ውሻ በሽታ ለመፈወስ የትኛውን የህክምና አገልግሎት እንደሚመርጥ በንፅፅር መመርመራቸው፣ ከዚህ በፊት ከተካሄዱት ጥናቶች በተለየ መልኩ አዲስ አቅጣጫን አመላክተዋል፤ ማለት ይቻላል።

Mekonene Meressa(2010) "Indigenous Medicine, Beliefs and Practices Among the Kunama in Sheraro, Tigray" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። በጥናታቸው በባህላዊ ህክምና የሚደረጉ እምልኮዎችን እና ተግባራትን አጥንተዋል። ማህበረሰቡ እና ባህላዊ ሃኪሞች ለበሽታ መንስኤዎች ያላቸውን አመለካከት፣ የባህል ሃኪሞች የህክምና እውቀቱን ከምን እንዳገኙት፣ ማኅበረሰቡ ለባህላዊና ለዘመናዊ ህክምና ያለውን አመለካከት፤ በዋናነት አጥንተዋል።

እንደ Mekonen ገለጻ አብዛኛውን የኩናማ ማኅበረሰብ በሽታን ለመከላከል ባህላዊ መድሃኒትን አዘውትረው እንደሚጠቀሙ በጥናታቸው አረጋግጠዋል። የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ በሽታን ለመከላከል፣ ህመምተኛን ለመፈወስ የተለያዩ እምልኮዎችን እና ተግባራትን እንደ አካባቢው ማህበረሰብ ልማድ የሚጠቀሙ በመሆናቸው በኩናማ ማኅበረሰብ ዘንድ ተመራጭ እንዳደረጋቸው አትተዋል። በኩናማ ማኅበረሰብ ለበሽታ መከሰቻ መንስኤ ናቸው የሚባሉት በተፈጥሯዊና በመለኮታዊ ሃይል የሚመጡ ሲሆን ተፈጥሯዊ የሚሏቸው በድንገተኛ አደጋ የሚደርሱ ጉዳቶችን፣ ከሰውነት ቁስል ጋር የተያያዙ በሽታዎች ያጠቃልላል። መለኮታዊ የሚሏቸው ከቅድመ አያቶቻቸው በሚላክ መንፈስ፣

ቡዳ፣ አጋንንት፣ ዛር እና በመሳሰሉት ቁጣ የሚመጡ በሽታዎች ናቸው፤ በማለት አብራርተዋል።

Mekonen ከባህል ህክምና ዘርፍ፤ የባህል ህክምና ባለሙያዎችን ሚና፤ ማህበረሰቡ ከዘመናዊና ከባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ፤ የትኛውን የህክምና አገልግሎት ተመራጭ እንደሚያደርጉ፣ ማህበረሰቡ ለጤና እና ለበሽታ መንስኤ ያላቸው አመለካት፤ የሚሉትን ነጥለው በማየት አጥንተዋል። አዲስ የጥናት አቅጣጫ ባይኖራቸውም የኩናማን ማህበረሰብ የባህል ህክምና አምልኮና ተግባር ማጥናታቸው፤ ከዚህ በፊት ከተካሄዱ ናቶች የተለዩ ያደርጋቸዋል።

### 3.2.4 ለታሪክ ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት

ከታሪክ ትምህርት ክፍል ባህላዊ ህክምናን ያጠኑ Assefa Balcha (1992 G.C) ናቸው። የጥናታቸው ርዕስ "Traditional Medicine in Wallo: Its Nature and History" በሚል አቅርበዋል። የጥናታቸው አቢይ አላማ የወሎን የባህል ህክምና ገጽታ (Nature) እና ታሪክ ማጥናት ነበር። ማህበረሰቡ ከአምልኮ ጋር በተያያዘ የሚፈፅማቸውን የባህል ህክምና ሥርዓት፣ ባህላዊ ሐኪሞች ለበሽታ መንስኤዎች እና ለመድኃኒት ያላቸውን አመለካከት፣ በዘመናዊና በባህላዊ ህክምና መካል ያለው ግንኙነት ቃኝተዋል።

የባህል ሐኪሞች የማኅበረሰብን ጤንነት በማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ሚና ከመጫወታቸውም በላይ እንደ ህመምተኛው ፍላጎት እና የህመም ዓይነት መድኃኒት መጥነው እንደሚሰጡ ጠቁመዋል። በዘመናዊ ህክምና የማይድኑ በሽታዎች በባህላዊው ህክምና ፈውስ እንደሚያገኙ አትተዋል። በጥናታቸው ማጠቃለያ ባህላዊ እና ዘመናዊ ህክምና በአንድነት ተቀራርበው ቢሰሩ፣ የባህል ህክምና ባለሙያዎችን በማደራጀት እና ህጋዊ እውቅና በመስጠት የሚጠናከሩበትን መንገድ መንግስት መቀየስ እና ማመቻቸት እንዳለበት በመጠቆም ጥናታቸውን ቋጭተዋል።

### 3.2.5 በውጭ አገር የታተሙ የፒ.ኤች.ዲ ጥናቶች

በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ የኢትዮጵያን ባህላዊ መድኃኒት ካጠኑ ባለሙያዎች መካከል Young(1970)፤ Fekadu(2001) እና Wondwosen (2006) ይገኙበታል። የጥናታቸው ርዕስ፣ ትኩረትና ያጠኑት ማኅበረሰብ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የYoung Allan ጥናት ርዕስ "Medical Beliefs and Practices of Begamder Amhara" የሚል ነው። የጥናታቸው ማእከላዊ ጉዳይ የአማራውን ማኅበረሰብ በተለይ የጎንደርን(በድሮው በጌምድር) ባህላዊ መድኃኒት አምልኮና ተግባር በመመርመር፤ ማኅበረሰቡ

ተፈጥሯዊና መለኮታዊ የበሽታ መንስኤዎችን እንዴት እንደሚከላከል፣ የባህል ሐኪሞች የህክምና አተገባበር ምን እንደሚመስል፣ በማኅበረሰቡ የበሽታ መንስኤ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ መግለጽ ነው።

አጥኚው ባህላዊውን መድኃኒት ከሃገረሰባዊ እምልኮ፣ ልማድና ተግባር አንፃር የመረመሩ ሲሆን ጥናቱን ባካሄዱበት አካባቢ የባህል የህክምና ባለሙያዎችን እንደ እውቀት ምንጫቸው በሁለት ምድብ ከፍለው አጥንተዋል። እነዚህም አለማዊ እና መንፈሳዊ በማለት ከፍለዋል። በአለማዊ ስር ያካተቷቸው የዕፅ መድኃኒት ባለሙያዎች፣ ወጌሻ፣ አዋላጆችና አጋሚዎችን ሲሆን መንፈሳዊ የሚባሉት ደግሞ ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ ደብተራዎችና ሼኮች ናቸው በማለት ያጠቃልላሉ። የባህል ህክምና አተገባበሩን እና የማህበረሰቡን አመለካከትና ተግባር አጥንተዋል።

Young የባህል ህክምና ባለሙያዎችን እንደእውቀት ምንጫቸው በሁለት ከፍለው ማየታቸው ተገቢ ቢሆንም በጥናታቸው ምድብ መጣረስ ይታያል። የኢትዮጵያ የባህል ህክምና ባለሙያዎች መታየትና መቃኘት ያለባቸው፤ ከተግባራቸው፣ ከእውቀት ምንጫቸው እና ማኅበረሰቡ ከሚሰጣቸው ስያሜ አንጻር እንጅ የእውቀት ምንጫቸውን ብቻ መሰረት በማድረግ መመደቡ ብዙም አያራምድ። አለማዊ በሚባሉት የህክምና ምድብ ደብተራዎች፣ ቄሶችና ሼኮች እፀ መድኃኒትን በመቀመም ህመምተኛን ይፈውሳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ተግባራትን ጎን ለጎን ያስኬዳሉ። እነዚህ ባለሙያዎች ከአንድ አቅጣጫ በማየት ለመመደብና ለመፈረጅ መሞከር ወደ ስህተት ያመራል። ከዚህ አንጻር በአለማዊና በመንፈሳዊ መካከል ያለውን ድንበር ድክመትና ጥንካሬ በመግለጽ፣ የህክምና ባለሙያዎቹ እውቀቱን ከየት እንዳገኙ፣ ተግባራቸውና አገልግሎታቸው በምን ላይ የተመሰረተ መሆኑን በመቃኘት መፈረጅ ይገባል።

ሌላው የኢትዮጵያን የባህል ህክምና በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ ያጠኑ ባለሙያ Fekadu Fullas ናቸው። Fekadu (2001) "Ethiopian Traditional Medicine: Common Medicinal Plants in Perspective" በሚል ርዕስ ያሳተሙት ጥናት ከሳይንስ ትምህርት ክፍል አንጻር የተቃኘ ነው። የጥናታቸው ይዘት በባህላዊ መድኃኒት ጉልህ ሚና ያላቸውን እፅዋት ከአገሪቱ ክፍሎች በመሰብሰብ በላብራቶሪ ምርመራ መርዛማነታቸውን፣ በሽታ የመከላከል አቅማቸውን የመረመሩበት ጥናት ነው። በጥናታቸው ሂደት 99(ዘጠና ዘጠኝ) እፅዋትን በመሰብሰብ የሚበቅሉበትን ቦታና የአየር ፀባይ፣ የአካባቢ ስያሜና ሳይንሳዊ ስም በመስጠት ሰንደዋል።

Fekadu ከቀደሙ ጥናታዊ ጽሑፎች የሚለዩት እፅዋትን፣ በዘመናዊና በባህላዊ ህክምና ዘርፍ ያላቸውን ሚና ማጥናታቸው፣ የእፅዋቱን የመድኃኒት አቅም በቤተ ሙከራ

ማረጋገጣቸው፣ በባህላዊና በዘመናዊ ህክምና የሚሰጡትን ጠቀሜታና አገልግሎት መጠቆማቸው፣ በሽታን የመፈወስ ሃይላቸውን፣ መርዛማነታቸውን፣ አካባቢያዊና ሳይንሳዊ መጠሪያቸውን፣ የሚበቅሉበትን ቦታና የአየር ፀባይ በመዳሰስ ሰፊ ትንታኔ ማቅረባቸው ከቀደሙ ጥናታዊ ጽሑፎች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡

የኢትዮጵያን የባህል ህክምና በፒ.ኤች ዲግሪ ደረጃ ካጠኑ ባለሙያዎች መካከል Wondwosen Teshome ይጠቀሳሉ፡፡ የጥናታቸው ርዕስ "Medical Pluralism in Ethiopia" የሚል ሲሆን በጀርመን ሻከር ቫርሌጅ ዩኒቨርሲቲ ስነ ሰብዕ ትምህርት ክፍል 2006 የታተመ ጥናት ነው፡፡ የጥናታቸው አቢይ ዓላማ ዘመናዊውን እና ባህላዊውን ህክምና ጥምረትን ማጥናት ነበር፡፡

ባህላዊ ህክምና ሲባል በውስጡ በርካታ ጉዳዮችን እንደሚያካትት ጠቁመዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በአለማዊና በመንፈሳዊ ኃይል በመታገዝ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ሁለት ንዑስ የህክምና ዘርፎች ናቸው፡፡ በአለማዊ ስር የሚመደቡት የባህል ህክምና ባለሙያዎች ከእጸዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት ንጥረ ነገሮችን በመቀመም መድኃኒት የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ መንፈሳዊ የሚባሉት በመንፈስ(በመለኮት) ኃይል በመታገዝ፣ ልዕለሰብ የሆነን ጉዳይ የሚፈፅሙ ተዓምር ሰሪዎች በጸበል፣ በመስቀል፣ በፆም፣ በፀሎት፣ በስግደት የሚፈውሱ የባህል ሐኪሞች ናቸው፤ በማለት ያብራራሉ፡፡

ዘመናዊ ህክምና የምዕራቡ አለም ስልጣኔ ውጤት ሲሆን ሳይንሳዊ ምርምሮች፣ ተጨባጭና ምክንያታዊ የህክምና ዘርፍ መሆኑን ያትታሉ፡፡ በባህላዊና በዘመናዊው መካከል ያለው ትልቁ ሽለቆ በሚከተሉት ፍልስፍና፣ በሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ምክንያታዊ መሆንና አለመሆን በሁለቱ መካከል ያለውን አመለካከት ያሰፋዋል፤ በማለት በመካከላቸው ያለውን ፍልስፍና እና ውዝግብ ዳሰዋል፡፡ በጥናታቸው ማጠቃለያ ዘመናዊውም ሆነ ባህላዊ ህክምና በሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ጠንካራና ደካማ ጎንእንዳላቸው በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

### 3.2.6 በአለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ የቀረቡ ጥናቶች ቅኝት

Alemayehu Moges (1984). "Traditional Ethiopian Medicine." በሚል ርዕስ ለ8ኛው አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ኮንፈረንስ ጥናት አቅርበው ነበር፡፡ የጥናታቸው ዓቢይ ዓላማ የኢትዮጵያ ባህላዊ መድኃኒት ነው፡፡ ጥናቱ የባህል መድኃኒት የሚማረው ማነው? እንዴት ይማሩታል? ከየት ይማሩታል? የባህል ህክምና ጥበቡ እንዴት ይተላለፋል? በባህላዊ መድኃኒት የሚድኑ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

እንደ Alemayehu ገለጻ በእምነት ተቋማት አካባቢ ያለ በተለይ በኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ለረጅም ዓመት መሪ ጌታ፣ ቄስ፣ ዲያቆን ሆኖ የሚያገለግል ባለሙያ፣ ከቤተ ክርስቲያን

የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥን ሊማር ይቻላል፡፡ የባህል መድኃኒት የሚያጠናው ተማሪ እፅዋትን፣ ማዕድናትን እንስሳትን በደንብ እንዲያስተውል፣ በአካባቢው የሚበቅሉ እፀ መድኃኒት በስም፣ በዓይነት፣ በባህሪ፣ በሚገኙበት ቦታና የአየር ፀባይ እንዲለይና እንዲማር ይደረጋል፡፡

Alemayehu ይዘውት የተነሱት ርዕስ ጥልቅና መሰረታዊ ጉዳይ ቢሆንም አጠቃላይ ይዘቱ ሲመረመር በአንድ አበይት ምክንያት ቀርነት ይታይበታል፡፡ ይህም ይዘውት የተነሱት ርዕስ የኢትዮጵያን የባህል ህክምና ስርዓት አገራዊ በሆነ ደረጃ ለመዳሰስ የሚሞከር ቢሆንም የሰሜኑን ክፍል ብቻ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ባህላዊ መድኃኒትን በተመለከተ ጥናት ካቀረቡት መካከል Richard Pankhurst (2004) ይገኙበታል፡፡ የጥናታቸው ርዕስ “The characteristics of Traditional Ethiopian Medicine and Its Traditional Pharmacopoeia” የሚል ነበር፡፡ የጥናታቸው ትኩረት የኢትዮጵያን የባህል ህክምና ፀባይ (መገለጫ) እና የባህላዊ መድኃኒት አውደ ጥበብን መመርመር ነበር፡፡

በጥናታቸው የኢትዮጵያን የባህል ህክምና ከእምነት፣ ከሐይማኖት እና ከመለኮት ኃይል ነጥሎ ማየት ያስቸግራል በማለት ያትታሉ፡፡ የተወሰነው ህክምና በልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል የሚታሰብ ሲሆን አምላክን በመለመንና በመማፀን፣ የመለኮት ሃይሉ በተሰጣቸው ሰዎች በመታገዝ በሽታን መከላከልና መፈወስ እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አስማታዊና ሃይማኖታዊ (Medico-magical/religious) መጻሕፍት እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ጥቂት ባህላዊ መድኃኒት አውደ ጥበብ ካላቸው አገሮች ጎራ ትመደባለች፡፡ ለዚህም የመልክዓ ምድሯ አቀማመጥ፣ የተለያዩ እፅዋት መገኛ መሆኗ እና አበው የጻፉት መረጃ ለዚህ ምስክር ነው፤ በማለት በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከ17ኛ ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው መ/ክዘመን መጀመሪያ ድረስ መድኃኒተ አውደ ጥበብ እንደተጻፈ በመግለጽ ጥናታቸውን ቋጭተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተዳሰሱ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ነጥብ ባህላዊ መድኃኒት(ህክምና)ን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ነው፡፡ የኔ ጥናት ከነዚህ የሚለየው በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች ያጠኑ እና በሰሜን ሸዋ ግሼ ወረዳ የሚካሄደውን የባህል ህክምና በቀጥታም ሆነ በተጓዳኝ የዳሰሱ ጥናቶች አለመኖራቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማኅበረሰቡን እምነት፣ ባህል፣ ልማድና መልክዓ ምድራዊ ገጽታ መነሻ በማድረግ የሚያዘጋጁቸውን መድኃኒቶች ከባህል ሐኪሞቹና ከማኅበረሰቡ ባህል አንፃር የሚመረምር ጥናት በመሆኑ ከሌሎች ጥናቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ

በዚህ ምዕራፍ ስር በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶች አሰባሰብ፤ ቅመማና አሰጣጥ፤ የጥበቡ መተላለፊያ መንገዶችና ምስጢራዊነት ትንታኔ ተሰጥቷል። ከዚህ በመቀጠል የባህል ሐኪሞች ከማኅበረሰቡ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ማኅበረሰብ ለባህላዊ ህክምና ያለው አመለካከት፤ በወረዳው ጎልተው የሚታዩ የበሽታ አይነቶች ተጠቁመዋል።

### 4.1 በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች

በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጅካዊና የህመምተኛውን ዳራ በማጤን እንደሆነ በምዕራፍ ሶስት ንዑስ ርዕስ 3.1.5 ተጠቅሷል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከመስክ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፤ በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በሽታን የመለያ ዘዴያቸው እንደግላዊ ልምዳቸው፣ እውቀታቸው፣ እምነታቸውና ተሰጥኦው የሚለያይ ቢሆንም በእይታዊ፣ በክሊኒካዊ፣ ባዮሎጅካዊና የህመምተኛውን ዳራ በመጠየቅ በሽታን እንደሚለዩ በጥናቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ ለውጫዊ የአካል ቁስለት፤ በእይታ የቁስሉን አይነትና ባህሪ መለየት እንደሚቻል ያስረዳሉ።

> የበሽታው ዓይነት የውጭ ቁስል ከሆነ በእይታ እለየዋለሁ። በሽተኛውን መጠየቅ አያስፈልገኝም። ለዚህም የቁስሉን ፈሳሽ፣ ዓይነትና መጠን፣ አቀማመጥና ቦታ በማየት በሽታውን እለያለሁ። የውስጥ ቁስል ከሆነ በሽተኛውን ምንክን ነው የሚሰማህ፣ መቼ ነው የጀመረህ፣ ስትንቀሳቀስ በመውደቅ ነው ወይስ በሾህ[15] ነው የጀመረህ በማለት እጠይቀዋለሁ። ተጥንት ሲጀምረኝ በመውደቅ፣ በሾህ፣ በንድፍት ወይም በላ በላ አድርጎኝ ታለ በዚያ በነገረኝ ፍርም [ሁኔታ ወይም መረጃ] መሰረት ቁስሉን እለይና መድኃኒት እሰጠዋለሁ (ሚያዝያ 19/2003 ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ በሰውነት ቆዳ ላይ የሚወጡ የቁስል ዓይነቶችን በአስረጅነት በመጥቀስ የቡድን ተወያዮች ገለፃና ማብራሪያ ሰጥተዋል። ከነዚህ የቡድን ተወያዮች መካከል የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ እንደሚከተለው አስረጂ በመጥቀስ ገልጸዋል።

---

[15] ከቡድን ተወያዮች መካከል የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ በእሾህ መንስኤ የሚመጡ የቁስል በሽታዎች እንዳሉ ጠቁመዋል። ደም የነካው እሾህ በተለያዩ ተሳቢና መርዛማ ነፍሳት ሊላስ ይችላል ። እነዚህ መርዛማ (እባብ፣ እንሽላሊት፣ ጊንጥ...) ነፍሳት በእሾሁ ላይ ያረፈውን ደም ሲልሱ መርዛቸውን ጥለው ይሄዳሉ። ይህ እሾህ ሰውን ከወጋ ለተለያዩ የቁስል በሽታዎች ይዳረጋል። በእንደዚህ ዓይነት እሾህ የተወጋ ሰው በቅርብ ጊዜ ውስጥ መድኃኒት መውሰድ እንዳለበት አስረድተው፤ ህመምተኛው ከቆየ ግን ወደ ሌላ በሽታ ሊቀየርበት እንደሚችል ገልጸዋል (የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ፤ሚያዚያ 29/2003ዓ.ም)።

የአጥንት ነቀርሳ ምልክቷ ምንድነው ፍንጫን ታጠባለች። ከዚያ ወዲያ ትልዝ እያለች፣ ትልዝ እያለች፣ ትልዝ እያለች [ቀስ እያለችና እየበሰለች] ደምና መግል እያበዛች ትመጣለች። አፏን ካጠበበች ተንኮል ያዘች ማለት ነው። ቶሎ አትደርቅም አንድ ጊዜ ጠፋሁ ትላለች፣ ትካክማለች [ትደክማለች]። እንደገና ስንዴና የአገዳ እህል የቀመሱ ጊዜ ቡፍ ብላ ትነሳለች፤ ከምግብም የሚቀሰቅሳት አለ። ሰውዬው በተጎዳ ጊዜ ትነሳለች። ምልክቷ ሁለት ሶስት አይነት ነው፤ ወፍራም መግል እንደ አጓት ዉሃ ያዘለ ታመጣለች፣ ወፍራም መግልና ደም የተቀላቀለበት ታመጣለች፣ አፏን ታጠባለች፣ ውስጥ ውስጡን አጥንት ትሰብራለች። ገስጋሽ[የቁስል ዓይነት ነው] የሚባለው ሰውነትን ቡትርፍ ነው የሚያደርገው፤ ጅብ የበላው ነው የሚያስመስለው። በተለይ ዘመናዊ ህክምና ከወሰደ ይብሳል፣ ይቆጣል። እንደእኸ ያመጣና ደም ብቻ ነው የሚያፈሰው። ውስጥ ውስጡን ይሄዳል፣ ይበላል። ቆንጣጭ የምትባለው በየክርክሩ ጣት ትቆረጣለች፤ አጥንት ትሰብራለች። ምልክቷ ታንገበግባለች፣ እሳተ ጋሞራ የሆነ ትኩሳት ታመጣለች፣ ታኃያለች። የሷ ዋና ምልክቷ ደም ብቻ ታፈስና እንደምላስ ቀይ የሆነ ሥጋ ከውስጥ ብቅ ትላለች፤ ፈሳሿ ደም እንጅ ሌላ አይቀላቅልም፤ በማለት በቡድን ውይይቱ እለት አስረድተዋል(ሚያዚያ 29/2003ዓ.ም)።



የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ በአጥንት ነቀርሳ የተያዘ ህመምተኛን በማከም ላይ እያሉ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው፤ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች በሰውነት ላይ ለሚወጡ ቁስል ነክ በሽታዎች መሰረታዊ ምልክታቸውንና መለያቸውን በማጤን የበሽታዎቹን ዓይነትና ባህሪ ይለያሉ ማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ መልኩ መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ በባህላዊ ህክምና ስርዓት ውስጥ በዋናነት በሽታን የመለያ ዘዴ እይታዊ እንደሆነ ገልጸው፤ ከዚህ የቀረውን የምርመራ ስልት ደግሞ የተለያዩ ተግባራትንና ሙከራዎችን በማድረግ መለየት የሚቻል መሆኑን እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> መጀመሪያ ታካሚዎች ሲመጡ፤ ከየት እንደመጡ፣ በሽታው እንዴት እንደጀመራቸው እጠይቅና ወደ ምርመራና አስተያየቱ እገባለሁ። የማይናገሩ ህፃናትና አዋቂዎች ከሆኑ የሰውነት አካላቸውን በእጅ በመዳሰስና ሁኔታቸውን አትኩሮ በማየትና በማዳመጥ፤ በአተነፋፈሳቸው፣ በዓይናቸው፣ በጥፍራቸው ያሉትን ምልክቶች በማየት በሽታቸውን እለያለሁ። የበሽታቸው ዓይነት ቁስል ከሆነ እሱን በማየት እለየዋለሁ። ሌላ በሽታ ከሆነ ደግሞ ዓይናቸውንና ምላሳቸውን በማየት፣ ጥፍራቸውን ጫን ጫን በማድረግ፣ አክታቸውን በማየት የበሽታውን ዓይነት መለየት እችላለሁ፤ በማለት ይገልፃሉ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

በባህል ህክምናው ዘርፍ ተሰማርተው የአርባ ዓመት ልምድ ያላቸው የሰማኒያ አራት አመቱ አዛውንት መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ፤ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለየቱ ዘዴ ቅድሚያ ቢሆንም የበሽታዎችን ዓይነትና ጸባይ ለማወቅ የረጅም ዓመት ልምድና ተሞክሮ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ የበሽታውን ዓይነት፣ ምልክትና ፀባይ ለይቶ ለመፈረጅ ከልጅነት እስከ እውቀት በሙያ ዘርፉ ማሳለፍን፣ በየወቅቱ የሚከሰቱ የበሽታ ሁኔታዎችን መረዳትን፣ የተለያዩ ሙከራዎች ማካሄድን፣ የህመምተኛውን ሁኔታና ጤንነት መከታተልንና የተሰጠው መድኃኒት መስራትና አለመስራቱን ማረጋገጥን፤እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ (ሚያዝያ13/2003ዓ.ም)።

መሪ ጌታ ዲበኩሉ አማረ ደግሞ፤ በባህል ህክምና በሽታን ለመለየት የሚደረገው ጥረት ከበሽታ በሽታ፣ ከቦታ ቦታ፣ ከባለሙያ ባለሙያ በተወሰነ መልኩ እንደሚለያይ ይጠቁማሉ። አንድን በሽታ ለመመርመር ፈርጀ ብዙ [ባዮሎጅካዊ ምርመራን መሰረት ያደረገ] አማራጮች እንዳሉ የሚከተለውን ምሳሌ በማቅረብ ያስረዳሉ።

> ለምሳሌ የስኳር በሽተኛን ለመለየት የህመምተኛውን ሽንት በተለያየ ሁኔታ ትመረምራለህ። መጀመሪያ የሚሰማውን ስሜትና የምግብ ፍላጎቱን ትጠይቃለህ። ከዚያም የስኳር በሽታ መሆኑን ከጠረጠርክ ታማሚው የራሱን ክንድ እንዲጠባ ታደርጋለህ፤ በሽታው ካለበት ስኳር ስኳር ይለዋል፤ ጤነኛ ሰው ከሆነ ጨው ጨው ይለዋል፤ ስኳር ስኳር ካለው በሽታው አለበት ማለት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ሽንቱን እንዲቀምስ በማድረግ በሽታውን ትለያለህ፤ የስኳር በሽታ ካለበት ሽንቱ ስኳር ስኳር ይለዋል። ሌላው በሽታውን የመለያ ዘዴ በትንሽ እቃ ሽንቱን ትይዝና በሌላ እጅህ ደግሞ ንጹህ ውሃ ትይዝና ጭጫን ወይም ጉንዳን ያለበት አካባቢ ሄደህ ታፈሳለህ። ጉንዳኖቹ ውሃውን ይሸሹታል፤ የስኳር በሽታ ያለበትን ሽንት ወረው ይልሱታል፤ በዚህ መልኩ በሽታውን መለየት ትችላለህ። ከዚህም በተጨማሪ ሽንቱን በጥቁር ድንጋይ ላይ እንዲሸና ታደርግና ለተወሰነ ደቂቃ እስኪደርቅ ትጠብቃለህ። የስኳር በሽተኛ ከሆነ ሽንቱ ሲደርቅ ዝንቦች ወረው ይልሱታል፤ የተሸናበት ድንጋይ የስኳር ምልክት ይዞ ነጭ ይሆናል፤ በማለት ለዓንድ በሽታ የተለያዩ የመፈተኛ ዘዴዎች እንዳሉ ያስረዳሉ (ሚያዝያ 24/2003 ዓ.ም)።

የባህል ሐኪሞች አንድን በሽታ በተለያየ መልኩ መርምረውና ፈትነው የበሽታውን ዓይነት መለየት እንደሚችሉ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ምሳሌ ያስረዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ህመምተኛው የሚሰማውን ስሜት በማጤን፤ ከአካላዊ አቋሙ የበሽተኛውን ምልክት በመረዳት፣ ከህመምተኛው የሚወጣውን ፈሳሽና ሰገራ በመመርመር የበሽታውን ዓይነት ይፈርጃሉ ማለት ይቻላል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች ምንም ዓይነት ቴክኖሎጂን ሳይጠቀሙ የበሽታ ምልክቶችንና ዓይነቶችን ለመለየት የሚያደርጉት ጥረትና ተግባር የባህል ህክምና ጥበቡን ውስብስብ እና ፈርጀ ብዙ አማራጭ እንዲኖረው አድርገውታል፤ ማለት ይቻላል።

ከአውራ የቡድን ተወያዮች መካከል "የወፍ" (የጉበት) በሽታን እንዴት መለየት እንደሚቻል የባህል ሐኪም ታለእግዚር ይናዱ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

የወፍ ወይም በዘመናዊ ህክምና የጉበት በሽታ የሚባለው ምልክቱ ሰውነትን ያነጣል፣ ያገረጣል፣ ዓይንና ጥፍር አካባቢ ቢጫ ያደርጋል። የምግብ ፍላጎታቸውን ይቀንሳል፣ ያቅለሸልሻቸዋል፣ ወደ ላይ ይላቸዋል፣ ምግብ ይሸታቸዋል በዚህ ምክንያት በሽታውን መለየት እንደሚቻል በቡድን ውይይቱ እለት አስረድተዋል፤ (ሚያዝያ 29/2003ዓ.ም)።

በመሪ ጌታ ኃይሉ ፍስሐ የባህል ህክምና መስጫ ቦታ ያነጋገረኳቸው ታካሚ አቶ ሉሌ ዘገየ በወፍ በሽታ ተይዘው እንደነበር ነገሩኝ። የበሽታው ስሜት እንዴት እንደነበርና የባህል ሐኪሙ ምን ምን ነገሮችን አይተውና ጠይቀው መድኃኒት እንደሰጧችው እንደሚከተለው አጫውተውኛል።

ሲጀምረኝ ያቅለሸልሸኛል፣ እህል አያስበላኝም። ወፍ መሆኗን እኔ አላውቅም ነበር፤ እሳቸው ናቸው የነገሩኝ። መጀመሪያ እጄን ፣ ቀጥለው አይኔን አዩኝ፣ መልኬን [መልክህን] ቀይሮታል አሉኝ። ከትላንት ወዲያ ነበር የጀመረኝ ሽንት ይዘህና ብለው ይገፍ መጣሁ እሱን አይተው ይህንን መዳያኒት ሰጡኝ። በመለኪያ የሚጠጣ ነው የሰጡኝ በማለት የበሽታውን ሁኔታና የህክምናውን ሂደት አስረድተዋል (ሚያዝያ 27/2003ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ የቀረቡ ሁለት መረጃዎች እንደሚያስረዱት ከሆነ ስለወፍ በሽታ ምልክት፣ ባህሪና የምርመራ ዘዴ በውይይቱ የቀረበው ሃሳብና ከታካሚው የተገኘው መልስ ተዛማጅ መሆናቸውን የቀረቡት ማስረጃዎች ይጠቁማሉ።

የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ከሌሎች የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለየት ባለ መልኩ የምርመራ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ የውስጥ አካል በሽታዎችን ከእጅና እግር ነርቮች በመከታተል መለየት እንደሚችሉ በጥናቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። በህክምና መስጫ ቤታቸው ውስጥ የእጅ፣ የእግርና የሰውነት አጽሞች ሥዕል በግድግዳ ላይ ጎላ ባለ መልኩ ተሰቅለው ይታያሉ፤ የስዕሎቹን መግለጫ እና አገልግሎት ጠይቂያቸው እንደሚከተለው ገልጸውልኛል።

እነዚህ የምታያቸው የሰውነት ጡንቻና አጥንት፤ የእግርና የእጅ መዳፍ ምስሎች የውስጥ አካል በሽታዎችን ለመለየት የምጠቀምባቸው ስዕላዊ መግለጫዎቼ ናቸው። በሰውነታችን ጡንቻዎች፣ በውስጥ እጃችን መዳፍና እና እግራችን ነርቮች ላይ ምርመራ በማካሄድ ሰባ ስድስት በሽታዎችን የምለይ ሲሆን ከሰባ ስድስቱ የበሽታ ዓይነቶች መካከል ሰላሳ አራቱ በእጅ መዳፍና በእግር ነርቮች ላይ ይገኛሉ፤ በዚህ መልኩ በእጃችን፣ በእግራችን እና በሰውነታችን ስስ ብልቶች ዙሪያ የሚገኙ ነርቮችን በመመርመር የውስጥ በሽታዎችን እለያለሁ፤ በማለት አስረድተዋል (ሚያዝያ 25/2003ዓ.ም)።



የቀኝ መዳፍና የግራ እግር ነርቮችን በመመርመር በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ የባህል ሐኪሞች የውስጥ አካል በሽታዎችን ለመለየት የነርቭ መገኛ ቦታዎችን በመዳሰስ በሽታን ይለያሉ ማለት ይቻላል። የባህል ሐኪሞች የሰውነት ህዋሶቻቸውን (their own sensory organ) በማንቃት የተለያዩ በሽታዎችን ለመለየት ጥረት ከማድረጋቸውም በተጨማሪ በውጫዊ አካል፣ በሽንትና በሰገራ ለመለየት የሚያዳግቱ በሽታዎችን ከሰውነት ነርቮች ለመለየት ጥረት ሲያደርጉ፤ በጥናቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። እኚህ የባህል ሐኪም የእጅና የእግር ነርቮችን በመመርመር እንዴት በሽታን መለየት እንደሚቻል ምሳሌ በመጥቀስ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> አብዛኛውን ጊዜ በሽታን የምለየው በውስጥ እግራችንና በውስጥ እጃችን መዳፍ ላይ ነው። ለምሳሌ የጨጓራ ህመም፣ የሆድ ቁስል፣ የቶንሲልና የድምፅ መዘጋት በሽታዎች አሉ። እነዚህን በሽታዎች ለመለየት አብዛኛውን ጊዜ በእጅና በእግራችን ላይ የሚገኙ ነርቮችን እከታተላለሁ፤ ለምሳሌ የጉሮሮ ቶንሲል ሲያብጥ ወይም የድምፅ መዘጋት ሲያጋጥም በአውራ ጣቱና በጠቋሚ ጣቱ መካከል ያለውን ነጥብ ስነካው ከደደረና ካመመው የጉሮሮ ቶንሲል መሆኑን አረጋግጣለሁ። የአንጀት ድርቀት ከሆነ ሆዱ አካባቢ በመዳሰስ በትልቁ አንጀትና በትንሹ አንጀት መካከል በጣም ለስላሳ ቦታ አለች፤ እሷን በመንካትና የሚሰማውን ስሜት በመጠየቅ በሽታውን መለየት እችላለሁ፤ በማለት ገልጸዋል (ሚያዝያ 25//2003 ዓ.ም)።



የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ በህክምና ላይ እያሉ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

ከዚህ በላይ የቀረቡ መረጃዎች እንደሚያስረዱት፤ የባህል ሐኪሞች በሽታን የመለያ ዘዴያቸው[16] እንደበሽታው አይነት የተለያየ ቢሆንም በዋናነት እይታዊ የምርመራ ዘዴን በመጠቀም በሽታን ይለያሉ። በዚህ የምርመራ ዘዴም፤ የበሽታውን ዓይነት፣ ምልክት፣ ፀባይና ባህሪ ለመለየት ጥረት ሲያደርጉ በጥናቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል።

በራቤል ጤና ጣቢያ በዘመናዊ ህክምና በማዋለድና የህፃናት እንክብካቤ የቡድን መሪ የሆኑት ሐኪም ማሞ ተስፋዬ ስለባህላዊ ህክምና እና በሽታን የመለያ ዘዴ አስመልክተው የሚከተለውን ሃሳብ አቅርበዋል።

> በባህላዊ ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች በሽታን የመለያ ዘዴያቸው ከድርው ከእናት ከአባት የወረሱት ካልሆነ በስተቀር በዘመናዊ ህክምና የታገዘ አይደለም። ይሆናል በማለት ይመረምራሉ እንጅ የበሽታውን ጸባይ ይለያሉ ማለት ይከብዳል። አብዛኛውን ጊዜ የቁስልን በሽታ በተመለከተ እንደ ትቪ ያለውን በሽታ ካንሰር ነው፤ እየተባለ ችግር ያጋጥመናል። እግርና መገጣጠሚያን ስለሚያሳብጥ ባህላዊ ህክምና ተደርጓል እየተባለ ህሙማን ተጎድተው ይመጣሉ። ለምሳሌ የትቪ አይነቶች አሉ፤ የአጥንት፣ የሳንባ፣ የጭንቅላት ፣ የአንጀት ትቪ አሉ። አብዛኛውን ጊዜ የሳንባ ትቪ የሚባለውን የባህል ሐኪሞች አያውቁትም የአጥንት ትቪዎች ወደውጭ የማበጥ ባህሪ ስላላቸው፤ …በዚያ ቁስል ውስጥ የአይጥ አር የመሰለች ያስገቡላቸዋል። ህሙማን ዓመት ሁለት ዓመት ቆይተው አልድን ሲላቸው ወደኛ ይመጣሉ ። እነዚህን ነገሮች የመለየቱ ሁኔታ አስቸጋሪ ነው፤ በማለት ይገልፃሉ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

ከዚህ ሃሳብ ጋር በተዛመደ መልኩ በራቤል ጤና ጣቢያ የጤና መኮንን የሆኑት ሐኪም ዘላለም ግርማ የባህል ሐኪሞች በሽታን የመለያ ዘዴዎች በልምድ የሚያውቋቸው እና ኋላ ቀርነት የሚታይባቸው መሆኑን ያስረዳሉ።

> በሽታን የመለያ ዘዴያቸው እና የመድኃኒት ምጣኔያቸው፤…የምርመራ ስርዓታቸው በልማድ የሚያውቋቸው፣ ከአባቶች የወረሷቸው… ምልክት ያላቸውና ኋላ ቀር ዘዴን ተጠቅመው የሚመረምሩት፤ ከዘመናዊ ህክምና ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፤ በማለት በባህል ህክምና በኩል ያለውን ክፍተት ይተቻሉ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

ከነዚህ ሁለት የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ሃሳብ መረዳት የሚቻለው፤ የባህል ሐኪሞች የተለያዩ የበሽታ ባህሪዎችን፣ ምልክቶችንና አይነቶችን በሚጠቀሙት ባህላዊ የምርመራ ዘዴ

---

[16]በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በዋናነት በሽታን የመለያ ዘዴያቸው የሰውነት ቆዳን (መሸብሸብ፣ መቆርፈድ፣ መሰንጠቅ፣ መከርደድ፣ መለስለስ)፣ የምላስ መልክን (የምላስ መደብ ነጭ መሆን፣ መሰነጣጠቅ፣ የምላስ ስር መስመሮች መጥቆር፣ ቢጫና ጥቁር መሆን፣ የምላስ ትፍትፍ መብዛት… )፣ የዓይን ቀለምን (የመቅላት፣ የመደፍረስ፣ ቢጫ የመሆን፣ እንባ የማገፍት፣ጉም የመምሰል፣… ምልክት ያሳያል) የሽንት ቀለምን (ነጭ አረፋ መሰል ፣ ቢጫ መሰል ፣ የደፈረሰ ውሃ መሰል፣ አረፋ ያለውና የሌለው ሽንት)፣ የደም አይነትን (ቀይ ደም፣ ጉበት ወይም ጥቁር መሰል ደም) ፣ የዓይነ ምድር መልክን (አረፋ መሰል ተቅማጥ፣ ደምና ንፍጥ የተቀላቀለበት ተቅማጥ፣ እንደክብት የደረቀ ዓይነ ምድር፣ ጥገኛ ትላትሎች የሚታዩበት ዓይነምድር…) በማየት የበሽታዎችን ዓይነትና ምልክት እንደሚለዩ አጫውተውኛል (ከአውራና ከንዑስ መረጃ አቀባዮች የተጠናቀረ መረጃ፤ ከሚያዚያ 13 እስከ 29/2003ዓ.ም)።

በውል ይለያሉ ብሎ መናገር እንደሚያዳግት ያስረዳሉ። አንዳንድ በሽታዎችን "በይሆናል" የሚለዩ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ከዘመናዊ ህክምና ምርመራ ሥልት ጋር የተዛመዱ አለመሆናቸውንም አትተዋል። ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ በባህል ህክምና በሽታን ለመለየት የሚደረጉ የምርመራ ዘዴዎች በዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ተቀባይነት እንደሌላቸው ከጥናቱ መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

በአጠቃላይ ከመስክ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የባህል ሐኪሞች የተለያዩ በሽታዎችን ለመለየት ግላዊ እውቀታቸውን፣ ሙያቸውን፣ የረጅም ዓመት ልምዳቸውን ከግምት በማስገባት የበሽታ ምልክቶችን፣ አይነቶችንና ፀባዮችን ሲፈርጁ ይታያሉ። ከዚህ አንፃር በሽታን የመለያ ዘዴያቸው ከባለሙያ ባለሙያ የተለያየ ነው ማለት ይቻላል። ይህ በሽታን የመለያ ዘዴ በዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ተቀባይነት ባይኖረውም በባህሉ ህክምና ዘርፍ ተግባራዊ እንደሚሆን ለመገንዘብ ተችሏል።

## 4.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶችና አሰባሰብ

በዚህ ንዑስ ርእስ ስር ለባህላዊ መድኃኒት መቀመሚያ የሚውሉ ግብዓቶች፤ አሰባሰብ፤ ለባህላዊ መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ቀናት ትዕምርታዊነት (Symbolism) በተመለከተ ትንታኔ ቀርቧል

### 4.2.1 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶች

ለባህል መድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ግብዓቶች፤ ከእንስሳትና ከማዕድናት ውጤቶች የተገኙ መሆናቸውን በምዕራፍ ሶስት በንዑስ ንዑስ ርእስ 3.1.4.1 የተጠቀሰውን ሃሳብ ልብ ይሏል። ከነዚህ ግብዓቶች መካከል እፀዋት፣ እንስሳት እና ማዕድናት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን ከነፍሳት የሚገኙ ውጤቶችን ለመድኃኒትነት እንደሚጠቀሙ ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

የባህል ሐኪሞቹ በአብዛኛው ለመድኃኒት የሚውሉ ግብዓቶችን የሚቀምሙት ከእፀዋት መሆኑን ከመስክ ከተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። ለዓብነት ያህል፦ እፀ ሚሮን፣ መካን እንደድ፣ እፀ ኩሉ /ቁንዶ በርበሬ/፣ ስሚዛ /ሰንሰል/፣ የአሮጊት ፍቅር፣ እፀ ሳቤቅ /ሐረግ ሬሳ/፣ እፀ እየሱስ /የዓይጥ ሃረግ/፣ እፀ እንስታር /እሬት/፣ እፀ ዋዊ / ብሳና/ ፣ እፀ ድኅነት/ለንቋጣ/፣ እፀ ጎመር /እራስ ክምር/፣ እፀ መንስኤ /ሙት ዓንሳ/... እና የመሳሰሉትን እፅዋት አፅድቀው ለማየት ተችሏል። ከነዚህ እፀዋት ቅጠል፣ አበባ፣ ፍሬ፣ ግንድ፣ ተቀፅላ፣ ሙጫ፣ ልጣጭ ቀንበጥ፣ ቅርፊት ወዘተ ወስደው ለፈውስ የሚያገለግሉ መድኃኒቶችን እንደሚቀምሙ ታውቋል።



እፀ ሜሮን



መካን እንዶድ



እፀ ኩሉ/ቁንዶ በርበሬ/

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከእንስሳት የሚገኙ ግብዓቶችን በሁለት መልኩ አዘጋጅተው ለመድኃኒት ቅመማ አገልግሎት ያውሏቸዋል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች ከእንስሳትና ከነፍሳት የሚገኙ ውጤቶችን እንደ ማር (የንብና የጣዝማ ማር)[17]፣ ቅቤ[18]፣ ስጋ፣ ወተት፣ ቀንድ፣ ፀጉር፣ ደም፣ ኀሞት፣ ቆዳ፣ ጉበት፣… የመሳሰሉትን ለመድኃኒት መቀመሚያ ይጠቀሙባቸዋል። ለመድኃኒት አገልግሎት የሚውሉት ደግሞ የእማምሳይ ላም ቅቤ፣ የዓህያ ወተት፣ የፍየል ወተት፣ የጅብ /ቆዳ፣ ቅንድብ፣ ፀጉር፣ ጥፍር/፣ የሽኮኮ ስጋ፣ የእስስት ስጋ፣ የለሊት ወፍ፣ የነብር ደም፣ የቀበሮ ጉበት፣ የቆቅ፣ የሶረኔ ስጋ፣ እና የመሳሰሉት እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል። ከነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ ማርና ቅቤ በባህል ህክምናው ዘርፍ ጉልህ ሚና አላቸው። እንደ ባህል ሐኪሞቹ ገለፃ የተለያዩ የማር አይነቶች አሉ። ለዓብነት ያህል፤ ነጭ (ወለላ)፣ ቀይና ከዳ ማር ይጠቀሳሉ። እነዚህ የማር ዓይነቶች ሲሰበሰቡ የሚቆረጡበት ቦታ (ቆላ፣ ወይናደጋና ደጋ)፣ ወቅት፣ የማሩ ዓይነት ከግምት እንደሚገባ ከቡድን ተወያዮች መካከል የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰና መሪጌታ መስፍን ገብሬ አስረድተዋል። በጥንቃቄ የተቆረጠ ማር ለማንኛውም በሽታ ፈውስ መሆኑን ጠቁመው

---

[17]ጥቅምት፡- ወርሃ ፀደይ ይባላል። በዚህ ወር እፀዋት በየቦታው ያብባሉ፣ ይፈካሉ፤ ምድሪቷ አርንጓዴ ትለብሳለች። በዚህን ጊዜ ንቦች በየቦታው ይሰማራሉ፤ የተለያዩ አበቦችን ይቀስማሉ። እነዚህ ንቦች ከተለያዩ እፀዋትና ቦታዎች አሰባስበው የሚሰሩት ማር ለተለያዩ በሽታዎች ፈውስ ይሆናል። ማር በባህሪው ሙቀት የሚሰጥ በመሆኑ ለህመምተኛ ብርታትን ይሰጣል፤ ለጤነኛ ሰው ደግሞ ጧት ሁለት መንኪያ፤ ማታ ሁለት ማንኪያ ቢወስድ፤ በሽታን ይከላከልለታል፤ በውስጡ በሽታም ካለ ይፈውሰዋል፤ ማር የማይገባበት መድኃኒት ስለሌለ በጥንቃቄ ከሌሎች መድኃኒቶች ጋር ተቀምሞ ይሰጣል፤ በማለት ገልጸዋል። ከንብ ማር በተጨማሪ ጣዝማ ማር እና የትንኝ ማር ለመድኃኒት መቀመሚያ እንደሚያገለግሉ አውራ የመረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ። የጣዝማ ማር ከመሬት ተቆፍሮ የሚወጣ ሲሆን የትንኝ ማር ግን ከግንድ ውስጥ ተፈልፍሎ እንደሚወጣ ጠቁመዋል። የነዚህ ማር ንቦች ከሚያዘጋጁት በበለጠ በአካል ላይ ለሚወጣ ቁስልና ለሳል ፍቱን መድኃኒት እንደሆኑ አስረድተዋል (የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰና መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ ፤ ሚያዚያ 19-20/2003 ዓ.ም)።

[18] ላሞች ከንቦች ባለተናነሰ መልኩ የተለያዩ እፀዋትን፤ሣረጎችንና ቅጠላቅጠል ስለሚመገቡ ለመድኃኒት የሚውሉ እፀዋትን ይመገባሉ። በብዛት ለመድኃኒት የሚውሉ እፀዋት አረምና ሳር ነገር ናቸው። እነዚህን ተመግበው የሚሰጡት ወተትና ቅቤ በራሱ ተፈላጊ ነው፤ የላም፣ የፍየል ወተት አንዱ የመድኃኒት ዓይነትና ግብዓት እንደሆነ ገልጸዋል (የቡድን ተወያዮች ሚያዝያ 29/2000ዓ.ም)።

በተለይ ለሆድ ውስጥ ቁስለትና ለውጭ አካል ቁስሎች ተፈላጊ መድኃኒት እንደሆኑ ጠቁመዋል፡፡ ከማር ዓይነቶች ወለላ ማር በዋናነት እንደሚፈለግ አትተው፤ ይህ ማር ከቆላማ ቦታ ተፈልጎ እንደሚቀመጥ ገልጸዋል፡፡ ቆላማ አካባቢ የተመረጠበት ምክንያት በአካባቢው መርዛማ እፅዋት የሚያብቡበት፤ የምድርና የዛፍ አበቦች በብዛት የሚገኙበት ቦታነው፡፡ ለምሳሌ፡- እፀ ኤልያስ፣ አባሎ፣ ንብጥራ፣ እፀ እስራኤል፤ ከነዚህ አበቦች ቀስመው የሚጋግሩት ማር "እኛ ቀምመን ከምንሰጠው መድኃኒት አይተናነስም" በማለት ይገልፃሉ (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)፡፡



እፀ ኤልያስ



አባሎ



ንብጥራ

የባህል ህክምና ባለሙያዎች የተፈጥሮ ማዕድናትን ለመድኃኒትነት ይጠቀማሉ፡፡ ለአብነት ያህል፡- የድንጋይ ሽበት፣ ዲኝ፣ ወርቅ፣ ብር፣ መዳብ፣ መብረቅ የመታው ዓፈር፣ የምስጥ ኩይሳ፣ ጨው፣ መረሬ ዓፈርና የመሳሰሉትን ለመድኃኒት ቅመማ ይጠቀሙባቸዋል ፡፡

የባህል ሐኪሞች ነፍሳትን፤ አዘውትረው ባይሆንም አልፎ አልፎ ለመድኃኒት ግብዓት እንደሚጠቀሙባቸው ከመስክ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ ለዓብነት ያህል፡- አሙኝ፣ የውሃ እናት፣ ቢራቢሮ፣ ጉንዳን፣ ተርብ፣ እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 4.2.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፅዋት አሰባሰብ እና ስርዓተ ገቢር

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት አሰባሰብ እና ልማዳዊ ሥርዓተ ገቢራቸው ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

#### 4.2.2.1 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፅዋት አሰባሰብ

ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፅዋት በሁለት መልኩ እንደሚሰበሰቡ በምዕራፍ ሶስት ንዑስ ርእስ 3.1.6 ተገልጿል፡፡ ይህም የባህል ህክምና ባለሙያዎች በግቢያቸው ወይም በመስኖ ማሳቸው በማልማት ለመድኃኒት የሚጠቀሙባቸውን እፅዋት የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከዱር የሚሰበስቧቸውን እፅዋት ይመለከታል፡፡

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋትን በግቢያቸውና በመስኖ ማሳቸው (መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ፣ መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ፣ ደብተራ በየነ አበጋዝ) እስከ ሩብ ሄክታር አልምተው ሲንከባከቡ ተስተውሏል።

ከዚህ ውጪ ያሉትን ደግሞ ከበረሃ፣ ከአረሀ፣ ገደላማ ከሆኑ ክርክር ቦታዎች፣ ከቆላ፣ ከወይና ደጋ፣ ደጋና ወርጭ ከሆኑ ቦታዎች ይሰበስባሉ። ለዓብነት ያህል፡-የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ በግቢያቸው በማልማትና ከዱር /ከደን ቦታዎች/ በመሰብሰብ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፅዋትን እንደሚያሰባስቡ ገልጸዋል።

> እፅዋትን የምሰበስበው ከአካባቢያችን ከሚገኙ ቦታዎች ማለትም ከቆላ፣ ከወይና ደጋ፣ ከደጋና የተወሰኑትን በግቢዬ በማልማት ነው። በግቢዬ የማለማቸው ለመድኃኒት ይጠቅማሉ የምላቸውን ከሌላ ቦታ ተክላቸውን በማምጣት በግቢዬ አፅድቄያቸዋለሁ። ለምሳሌ በበጋ የማይገኙ መድኃኒቶች አሉ፣ በክረምት ወራት ዝናብ በሚዘንብ ጊዜ ከመሬት ውስጥ የሚበቅሉ እፀዋት አሉ።...በዚህ ጊዜ የምፈልጋቸው እፀዋት በቅርብ ቦታ የማይገኙ ከሆነ በግቢዬ አለማቸዋለሁ በማለት አስረድተዋል (ሚያዝያ24/2003ዓ.ም)።

መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ ደግሞ እፅዋትን ብቻ ሳይሆን እንስሳትንና ነፍሳትን ከዱር እንደሚሰበስቡ አስረድተዋል። እሩብ ሄክታር በሚሆን ቦታ እፅዋትን አልምተው ሲንከባከቡ በመስክ ስምሪቴ ወቅት ለማየት ችያለሁ። የመድኃኒት አሰባሰባቸውን ሂደት እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

> የባህል መድኃኒቶችን ከበረሃ ቦታ እሰበስባለሁ። አንዳንዶቹን ከግቢዬ አምጥቼ እተክላለሁ፤ የማይፀድቁትን ከቆላና ከደጋ እየሄድኩ እሰበስባለሁ። ከዚያም ከዓራዊት፣ ከነፍሳትና ከማዓድናት አሰባስባለሁ። ከማዕድናት የድንጋይ ሽበት፣ ከእንስሳት ሽኮኮ፣ ጅብና ነብርን እጠቀማለሁ። ከነዚህ ከደማቸው፣ ከአጥንታቸው፣ ከኩሳቸው፤ በአግባቡ ሰብስቤ እፀ ደብዳቤው ባዘዘኝ መሰረት እጠቀማለሁ፤በማለት ገልፀዋል (ሚያዚያ 19/2003ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው መሪጌታ መስፍን ገብሬ ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ከግቢያቸው በማልማት እና ከዱር በመሰብሰብ በየዓይነቱ ባህላዊ መድኃኒቶችን ያዘጋጃሉ። በመድኃኒት አሰባሰቡ ሂደት እፀዋትን ብቻ ሳይሆን እንስሳትን፣ ማዕድናትንና ነፍሣትን ከዱር እንደሚያሰባስቡ አስረድተዋል።

እነዚህ የባህል ሐኪሞች በእፀዋት አሰባሰቡ ሂደት ከጳጉሜን እስከ ህዳር መጀመሪያ ድረስ ባለው ወር ውስጥ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ይሰበስባሉ። እፀዋት በነዚህ ወራት የመሰብሰባቸውን ምክንያት መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> ...እፀዋት ከጳጉሜ ጀምረው እስከ ጥቅምት ሰላሳ ይሰበሰባሉ። በነዚህ ወቅት የሚሰበሰቡበት ምክነያት የእፀዋት አበባና ማዓዛ እንዳለ ከነስራችው ሳይደርቁ የሚገኙ በመሆናቸው ነው። ከዚያ ካለፈ መሬቱ እየሞቀ እና እየጋለ ወደስራቸው፣ ወደውጭ

አካላቸው ሲዛመት መድኃኒትነታቸውን ያጣሉ።...በግዜ የተለቀመ ግን ገና ለጋ ሳይሆኑ፤ ጎምራ በሆኑበት ሰዓት ከእነእሸታቸው በተገቢው ሰዓትና ጊዜ ከተለቀመ አመቱን ሙሉ ፈውስ ይሰጣሉ። በነዚህ ወቅት የሚፈለጉ እፀዋት አበባቸው፣ ስሮቻቸው፣ ፍሬያቸው፣ ቅርፊታቸው እና ቅጠላቸው ከነሙሉ ማዕዛቸው የምናገኛቸው በመሆኑ ለዓመት የሚበቃንን መድኃኒት አብዝተን እንሰበስባለን በማለት አስረድተዋል (ሚያዝያ18/ 2003ዓ.ም)።

በአጠቃላይ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለባህል መድኃኒት የሚያገለግሉ እፅዋትን ከግቢያቸው፣ ከመስኖ ማሳቸውና ከዱር የሚሰበስቡ ሲሆን እነዚህን ግብዓቶች ከጸጉሜን እስከ ጥቅምት መጨረሻ ድረስ ይሰበስባሉ። በዚህ ወቅት የሚሰበስቡበት ምክንያት እፅዋት በብዛት የሚገኙበት፣ የሚበቅሉበት፣ የሚያሸቱበትና የሚያፈሩበት ወቅት በመሆኑ ስሮቻቸውን፣ ቅጠላቸውን፣ አበባቸውን፣ ቅርፊታቸውን... እንደልብ ማግኘት ስለሚቻል ነው። ከዚህም በተጨማሪ በጣም ለጋና ጮርቃ ሳይሆኑ ወይም ሳይደርቁና ወዘናቸውን ሳያጡ ለመሰብሰብ አመቺ ወራቶች መሆናቸውን በመገንዘብ እንደሚሰበስቡ ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

#### 4.2.2.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ እፀዋት ሲሰበስቡ የተለያየ ልማዳዊ ሥርዓተ ገቢር [ሥርዓተ ገቢር ማለት፤ ያደራረጉን ሥርዓት የሚገልጽ ነው። ይህም እፅን ከመቁረጥ አንስቶ ለበሽተኛው እስከ መስጠት ድረስ ያለውን ሥርዓት ያጠቃልላል] ይፈጽማሉ። እነዚህ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋትን ሲሰበስቡ ከቀናት ማክሰኞን፣ ረቡዕና ዓርብን ይመርጣሉ። እነዚህ ቀናት የተመረጡበት ምስጢርም እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

በእለተ ማክሰኞ እፀዋት የመሰብሰባቸው ምስጢር እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ከፈጠረ በኋላ በእለተ ሰሉስ (ማክሰኞ) እፀዋትን የፈጠረበት ቀን በመሆኑ በዚህ ቀን የሚቆረጡ እፀዋት ፈውስ ያስገኛሉ ተብሎ ይታመናል። ረቡዕ፤ አይሁዶች ኢየሱስ ክርስቶስን ለመያዝ ሰኞና ማክሰኞ ተማክረው ከፈረሰባቸው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሃሳበቸው ሰምሮ ረቡዕ ተማከሩ። ሃሳባቸው የሰመረላቸው በመሆኑ በዚህ እለት የሚቆረጡ እፀዋት ይፈውሳሉ ከሚል አመኔታ የመጣ መሆኑን ይገልፃሉ። በዕለተ ዓርብ፤ እግዚአባሔር ሰውን የፈጠረበት እለት ዓርብ በመሆኑ በዚህ ቀን ተቆርጠው የሚሰጡ መድኃኒቶች ለሰው ልጅ ፈውስ ናቸው፤ በማለት እፅዋት በእለተ ዓርብ መቆረጥ እንዳለባቸው ይመክራሉ (መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ፣ መሪ ጌታ(የኔታ) ጌታቸር ሸዋንግዛው ሚያዚያ 19-20/2003 ዓ፣ም)።

መሪ ጌታ ዲበኩሉ አማረ በዕለተ ዓርብ ዓይሁዶች ሀሳባቸው ሞልቶ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ያፈሰሱበት ዕለት በመሆኑ ፤ ሌላው ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል እና ደሙ የፈሰሰበት እፅ ከእፀዋት የተገኘ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ አስረድተዋል። ይህም በመሆኑ የተሰቀለበት እፀ እፀ ፈውስ ሆኗል፤ መስቀሉ ራሱ ፈውስ ነው በማለት ገልጸዋል። በዚህ ዕለት የሚቀረጡ እፀዋት ፈውስን ያስገኛሉ፤ ፍቱን መድኃኒት ናቸው፤ ከሚል አመኔታ ዓርብን ታሳቢ በማድረግ እንደሚቀረጡ አትተዋል፤ (ሚያዝያ 24/2003ዓ.ም)።

የባህል መድኃኒቶች ሲሰበሰቡ ጸሎትና ሥርዓተ ገቢር እንደሚያስፈልጋቸው መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ ይጠቁማሉ። ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት ሲቀረጡ "እፅ አንግስ" የሚባለውን የእፀ ደብዳቤ ጸሎት በግዕዝ ሰባት ጊዜ በመድገም የሚፈጸም ሥርዓት እንዳለ ይገልፃሉ። እፀዋትን ለመቁረጥ ሲደግሙ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቃል በቃል ቀርቧል።

> አንቲ ውእቱ ዕፅ ብሩክ ዕፀ ሕይወት ዕፀ መድኃኒት ከመ ዕፀ ኮመል ይብሉኪ፤ ሰንተው ቀንተው ቀርነው ቀርነለው ቀርን ሳሙኤል፣ ኡራኤል፣ ኢዩኤል፣ ጉሁኤል፣ አማኑኤል፣ በከመ አንገስኮ ለአዳም በውስተ ገነት ከማሁ አንግሣ ለዛቲ ዕፅ በእደ ገብርክ እገሌ ተብሎ ፯ ጊዜ ይደገማል፤ በማለት ገልጸውልኛል፤ (ሚያዝያ 19/2003ዓ.ም)።

በተመሳሳይ መልኩ በመሪ ጌታ መስፍን ገብሬ የቀረበውን ሃሳብ በመደገፍ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት ሲቀረጡ ሥርዓተ ገቢር እንዳላቸው መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ያስረዳሉ ።

> አንቲ ዉእቱ ዕፅ ብሩክ እፀ ሕይወት ዕፀ መድኃኒት ከመ ዕፀ ሕይወት ዘውስተ ገነት ዘኮንኪ ዕፀ ሕይወት በዲበ ምድር ፍሬኪ ፍሬ ሕይወት ውእቱ ወዘበልዓ እምኔሁ ሕይወተ ዘለዓለም የሐዩ፤... በማለት እንደሚቀርጡ ጠቁመዋል (ተቀንጭቦ የተወሰደ ሚያዚያ 18/2003 ዓ.ም)።

ከግዕዝ በተጨማሪ በአማርኛ ቋንቋ እንደሚደገም መሪጌታ ጌታቸር ሙላቱና መሪጌታ ዲበኩሉ አማረ እንገሚከተለው አጫውተውኛል።

> አንቲ ውእቱ ዕፀ ጥበብ
> የዛር ጳጳሱን የጅን ንጉሱን
> የአጋንንት እራሱን፣ የዛር ሰራዊቱን
> የጅን መኳንንቱን፣ የቡዳ ማኅበራቱን
> ለእኔ ለእገሌ፣ ለእጀም ለእግሬም
> አስገድደሽ አሰግጅልኝ
> ግብርሽን ይገፍ መጥቻለሁ፤

በማለት ከደገሙ በኋላ እፅዋትን እንደሚቆርጡ ጠቁመዋል (ሚያዝያ18ና 24/2003 ዓ.ም)።

መሪ ጌታ ዲበኩሉ አማረ፤ ለመድኃኒት የሚገለግሉ እፀዋት ሲቆረጡ ሥርዓተ ገቢር፣ ደንብ፣ ህግ፣ ወግና ይትባህል እንዳላቸው ይገልፃሉ። ለምሳሌ አንድ መድኃኒት የሚሆን እፅ ሲቆረጥ የትኛው እፅ እንደሆነ መለየት፣ በየትኛው ጊዜና ቦታ እንደሚቆረጥና እንደሚገኝ ማጥናትን ይጠይቃል። ሌሊት ተቆፍሮ ጧት የሚቆረጥ አለ፣ ማታ ተቆፍሮ ሌሊት የሚቆረጥ አለ፣ ማክሰኞ የሚቆረጥ ረቡዕ የማይቆረጥ አለ፣ ዓርብ የሚቆረጥ ሐሙስ የማይቆረጥ አለ፤ ሳይሸኑ፣ ሳይኮሱ፣ ውሃ ሳይነኩ፣ በባዶ ሆድ [እህል ሳይቀምሱ] ተነስቶ ሄዶ የሚቆረጡ እፀዋት እንዳሉ ያስረዳሉ፤ (ሚያዝያ 24/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ታላሚ ያደረጋቸው የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት ሲሰበስቡ የተለያየ ሥርዓተ ገቢር እንደሚፈጽሙ ከአውራና ከንዑስ መረጃ አቀባዮቹ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች የተለያዩ የመድኃኒት እውደ ጥበብን (እፀ ደብዳቤ) መሰረት በማድረግ እና በመከተል ልማዳዊ፣ ባህላዊና እምነታዊ የሆኑ ተግባራትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሲፈጽሙ፤ ከመስክ ጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል።

### 4.2.3 ለባህላዊ መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እና ቀናት ትዕምርታዊነት

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለባህላዊ መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች እና ቀናት ያላቸው ትዕምርታዊ ፋይዳ ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ቀርቧል። ከመስክ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከመድኃኒት፣ አቆራረጥ፣ አቀማመምና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ለተለያየ ፋይዳና አላማ ሲባል ቁሳቁሶችን እና ቀናትን ይጠቀማሉ። ከነዚህም መካከል፤ የጌሾ እና የወይራ እንካሴ፣ የቀንድ ካራ፣ የወይራ ዛቢያ፣ ወፍ ያልቀመሰው ውሃ፣ መዳመጫና አለሎ (የድንጋይ)፣ የማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ፣ ሙቀጫና ወፍጮ ከቁሳቁስ የሚመረጡ ሲሆን ከቀናት ደግሞ ማክሰኞ፣ ረቡዕና ዓርብ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ቁሳቁሶች እና ቀናት በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለየ ሁኔታ የተመረጡበትን ምክንያት፣ ዓላማና አገልግሎት፣ ትዕምርታዊነት ምን እንደሆነ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

1. የጌሾ እና የወይራ እንካሴ፡- በግሼ ወረዳ የሚኖሩ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋትን ስር በጌሾ እንካሴ ወይም በወይራ እንካሴ ይቆፍራሉ። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት የጌሾ እንካሴ እፅ ከሌሎች እፆች በተለየ መልኩ "ፊውስን ያመጣል" ከሚል እምነት የመነጨ ሲሆን በጌሾ ዘንግ ጫፍ ላይ የሚገጠመው ጦር ሰው የተገደለበት ወይም ጦርነት ቦታ ደርሶ የመጣ እንካሴን ቢሆን ይመረጣል ይላሉ። የዚህ ፋይዳው አንዳንድ እፀዋት የደም ግብርን ስለሚፈልጉ የሰው ደም በነካው

ሲቆረጡ ፈውስን ያስገኛሉ ከሚል ልማድ የመጣ መሆኑን ይገልጻሉ። የወይራ እንካሴው ደግሞ ለቤተክርስቲያን ጣሪያና ግድግዳ መሥሪያ እና ለቅብዐ ቅዱስ ተፈላጊ እፅ በመሆኑ በሱ የሚቆረጥ እፅ ፈውስ እንደሚያስገኝ ያስረዳሉ።

2. የቀንድ ካራ፡- ይህ ጥናት ታላሚ ያደረጋቸው የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋትን ሲቆርጡ ሁለት ስለት ያለው የቀንድ ካራ ይጠቀማሉ። ከተራ ቢላዋ በተለየ መልኩ የቀንድ ቢላዋን የመጠቀማቸው ተምሳሌት፤ለመድኃኒትነት የሚውሉ እፀዋት በሚቆረጡበት ሰዓት የእፀዋት ጠባቂ አጋንንት (ወታደር) እና እርኩስ መንፈስ እንዳይጣላቸው፤ ለመድኃኒትነት የሚቆርጡዋቸውን እፅዋት እንዳያከሽፍባቸው ለመከላከል፤ ከሚል እምነት የመጣ መሆኑ ይነገራል።

3. የወይራ ዛቢያ፡- የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለተወሰኑ እፀዋት ባልተለበለበ የወይራ ዛቢያ እና አፈር ባልቀመሰው ማረሻ (አዲስ በሆነ) መቆፈር እንዳለባቸው ይገልፃሉ። ለምሳሌ፡- እንደ ሾተላይ፣ ልክፍት፣ እና አውድቅ ለመሳሰሉት በሽታዎች በወይራ ዛቢያ ተምሰው አፈር ሳይነካቸው መቀመም እንዳለባቸው ያስረዳሉ። የዚህ ዋናው ምክንያት የበሽታዎቹ ክርኩስ መንፈስ (ጋኔን) የሚነሱ ስለሆኑ፤ ለነዚህ በሽታዎች የሚቆረጡ እፆች አጋንንት የሰፈረባቸው እፆች ናቸው ተብሎ ይታሰባል። እነዚህን እፆች በጥንቃቄ ለመቁረጥና ከበዋቸው የነበሩ ርኩሳን መናፍስትን (ሰይጣናትን) ለማራቅ፤ መድኃኒት ቆራጩን አደጋላይ እንዳይጥሉት፣ የተቆረጡ መድኃኒቶቹ ፈውስ እንዲኖራቸው በማሰብ ከሚል የፀና እምነት በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለ መሆኑን ይገልፃሉ።

4. መዳመጫና አለሎ፡- የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒትነት የሚውሉ ግብዓቶችን ለመፍጨት፣ ለማድቀቅ እና ለመደቆስ የሚጠቀሙበት ድንጋይ መዳመጫና አለሎ ይባላል። "እናቱ" ድንጋይ ሲሆን ከላይ የሚቀጠቀጥበትና መዳመጫ ማለት ከስር የሚቀመጠው የሚደቆሥበት አለሎ [አለሎ፣ አልሎ፣ አሉሎና አሎሎ በመባል በተለያዩ ዘዬዎች ይጠራል] ይባላል። መዳመጫና አለሎ የሚመጣው ከትልቅ ወንዝ ወይም መልካ ተፈልጎ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ድንጋዩ በወንዝ አለት የተፈተነ፣ በወራጅ ውሃ የታጠበና የፀዳ በመሆኑ መድኃኒት በሚቀመምበት ሰዓት የማይፈረፈርና የማይሰበር ነው፤ ከሚል እምኔታ ለመድኃኒት መቀጥቀጫና መደቆሻ ይጠቀሙበታል። ከወንዝ አለት ውጭ የሆኑ መዳመጫና አለሎ ለመድኃኒት መቀመሚያነት አይመረጡም። ለዚህ ምክንያታቸው የተለያዩ እንስሳት ወይም ሰዎች የተቀመጡበት፣ የሸኑበትና የረገጡት ሊሆን ስለሚችል፤ የረከሰ ነው፤ ከሚል እምኔታ ለመድኃኒት መቀመሚያነት አይውልም።



*መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ ለባህል መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በማሳየት ላይ እያሉ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ*

5. ወፍ ያልቀመሰው ውሃ እና ሰው (ሴት) ያልነካው ውሃ፡- ባለመድኃኒተኞች ከእፀዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፍሳት የሰበሰቧቸውን መድኃኒቶች "ወፍ በአልቀመሰው ውሃ" ይቀምማሉ። "ወፍ ያልቀመሰው ውሃ"[ሌሊት ወፍ ሳይንጫጫና ከመስፈሪያቸው ሳይወርዱ፣ሰው ተነስቶ ውሃ ሳይቀዳ የሚቀዳውን ውሃ ነው] ማለት ወፎች ከመስፈሪያቸው ወርደው ያልታጠቡበት፣ ኩሳቸውን ያልጣሉበት፣ ላባቸውን ያላራገፉበት፤ በሰውም ሆነ በሌላ ነገር ያልተነካካ ንጹሕ ውሃ ማለት ነው። የዚህ አይነት ውሃ ለመድኃኒት መቀመሚያ የሚመረጥበት ምክንያት ባልተነካካ (ባልረከሰ) ውሃ ከተቀመመ መድኃኒቱ ይሰራል (ይሰምራል) ከሚል አመኔታ የመጣ ነው። ከዚሁ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ሴት ያልነካው ውሃ (ቀድማ ያልቀዳችው) ይባላል። ሴት ያልነካው ውሃ ሲባል ለመድኃኒት የሚሆን ውሃ ከመቀዳቱ በፊት ሴት ያልደረሰችበት ወይም ያልቀዳችው ማለት ነው። ሴቶች ቀድመው ውሃውን ከነኩት ይረክሳል፣ በዚህ የተቀመመ መድኃኒት አይሰራም፣ አይሰምርም በሚል አመኔታ ሴት ያልነካው ውሃን ይመርጣሉ። ለዚህ ዋናው ምክንያታቸው ሴት የወር አበባ ካየች ወይም ጾታዊ ግንኙነት ከፈጸመች ትጎድፋለች ስለሚባል ወደ ውሃው ከቀረበች እንደምታረክሰው ይታመናል። በአንጻሩ ደግሞ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች (ድንግል የሆነች) ሴት ለመድኃኒት መቀመሚያ የሚውል ውሃ ትቀዳለች። ወፎች ከመውረዳቸውና ሴቶች ከመቅዳታቸው በፊት በልጅ አገረድ በተቀዳ ውሃ መቀመሙ መድኃኒቶች ይሰምራሉ ተብሎ ይታመናል።

6. የማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ፡- በግሼ ወረዳ በባህል ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች እፀ መድኃኒቶችን ከመቁረጣቸው በፊት በማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ ላይ ሆነው ይደግማሉ። የጥቁሩ ድንጋይ ዋና ተምሳሌት የሚደግሙት ድግምት አየር ላይ እንዳይቀር፣ ድግምታቸው እንዲሰራ ለማድረግ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ርኩሳን መናፍስትን በማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ ላይ ሆነው ሲጠሯቸው፤ ሓይልና ስልጣናቸውን

ስለሚያጡ ታዛዥ ይሆናሉ፤ የተጠየቁትን ነገር ያቀርባሉ፣ ወይም ይፈጽማሉ፣ ተብሎ እንደሚታመን ይገልጻሉ።

7. ሙቀጫና ወፍጮ፡- መድኃኒተኞች ቀምመው ያስቀመጧቸውን መድኃኒቶች ለበሽተኛ ሲሰጡ እንደ ህመሙ አይነት የመድኃኒት መስጫ ቦታዎች ይመርጣሉ። ለአንዳንድ ህሙማን መድኃኒቶችን በሙቀጫና በወፍጮ ላይ ተቀምጠው እንዲወስዱ ያደርጋሉ። በሙቀጫ ላይ ተቀምጠው መድኃኒት እንዲወስዱ የሚያደርጉበት ምክንያት እፀ ደብዳቤው [የባህል መድኃኒት ጥበበ መዝገብ] "ሙቀጫ ላይ አድርገህ አጠጣ" የሚል በመሆኑ ሲሆን ከዚህ ውጭ ለማጠጣት ቢሞክሩ መቅሰፍት ያመጣል፤ መድኃኒቱም ይረክሳል ከሚል እምነታ ስርዓቱን ተከትለው ይፈፅማሉ። ለምሳሌ እንጥል ስትወርድ፣ ለህፃናት የሚተፋ መድኃኒት ሲሰጡ በሙቀጫ ላይ ሆነው መድኃኒቱን እንዲወስዱ ያደርጋሉ። በወፍጮ ላይ የሚወሰዱ መድኃኒቶች ከእድል እና እጣፈንታ ጋር የተያያዙ ናቸው። ትዳርና አፍቃሪ ያጣች ሴት፤ እድሏ እንዲሰምር፣ የቀና ትዳር እንድታገኝ፣ የሞቀ ኑሮ እንድትመሰርት የሚሰጣትን መድኃኒት በወፍጮ ላይ ሆና እንድትወስድ ይደረጋል። እንደዚህ አይነት መድኃኒት የሚወስዱ ሴቶች በልጅነታቸው እድላቸው እንዳይቃና፣ ትዳራቸው እንዳይሰምር፣ ቆመው እንዲቀሩ የተደገመባቸው ናቸው ተብሎ በማኅበረሰቡ ስለሚታሰብ መድኃኒቱን በተባለው ቦታ ላይ እንዲወስዱ ይደረጋል። ድግምቱም ይሰረያል፤ ወደፊትም የቀና ትዳር ያጋጥማቸዋል በሚል እምነት የሚፈፀም ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ።

8. የእማምሳይ ላም ቅቤ፡- በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከእፀዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፍሳት የቀመሟቸውን መድኃኒቶች በእማምሳይ ላም ቅቤ ለውሰው ለቁስል መድኃኒት ይሰጣሉ። የእማምሳይ ላም ቅቤ[እማ፡-እናት፤እምሳይ፡-አምሳያ፣ ተመሳሳይ፣ አንድ አይነት እንደማለት ነው] የሚባለው እናትና ልጅ በመልክ ተመሳሳይ የሆኑ ማለት ነው። ለምሳሌ፤ ላሟ ጥቁር ከሆነች ልጇም ጥቁር የሆነ ማለት ነው። የዚህ ከዚች ላም ታልቦና ተነጥሮ የሚቀመጥ ቅቤ የእማምሳይ ላም ቅቤ ይባላል። የዚህ ተምሳሌቱ ቅቤው ከሌሎች መድኃኒቶች ጋር ተቀላቅሎ ሲሰጥ እንደ አንድ መድኃኒት ግብዓት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን የእማምሳይ ቅቤ ተጨምሮ መሰጠቱ መድኃኒቱን ያነግሰዋል፣ ቁስሉን ያድነዋል፣ ከሌሎቹ መድኃኒቶች ጋር ይስምራል፤ በሚል እምነታ ደባልቀው ይሰጣሉ።

9. አፅቅ እና ጋት (የእጅ ትንሿ ጣት እና መዳፍ)፡- የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት የሚውሉ እፀዋቶችን በአፅቅና በጋት ለክተው ይቆርጣሉ። በአፅቅ ክርክር(የጣት መጋጠሚያ) ተለክቶ የሚቆረጥ መድኃኒት፤ በአንድ በኩል ልኬትን፣ መጠንን ለመወሰን

የሚያገለግል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሆድ ውስጥ ያለውን በሽታ በትንሽ በትንሹ ቆራርጦ እንዲያወጣው በመመኘት የሚፈፀም ተግባር ነው፡፡ ጋት (የእጅ መዳፍ) እፀዋትን ለክቶ ለመቁረጥ ያገለግላል፡፡ የዚህ ተምሳሌቱ በህመምተኛው ሰውነት ውስጥ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን በሽታ አንድ ላይ ሰብስቦና ከሰውነታችን እጥብጥብ አድርጎ እንዲያስወጣው በመመኘት እና በአንድ ጊዜ ፈውስን የማግኘት ተስፋን ታላሚ በማድረግ የሚፈፀም ተግባር ና ልማድ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

10. ማክሰኞ፣ ረብዕና አርብ፡- (በ4.2.2.2 ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋት አሰባሰብ ሥርዓተ ገቢር በሚለው ርዕስ የቀረበውን ህሳብ ልብ ይሏል)

11. የጥቅምት ማር (የአቡነ አረጋዊና የእስጢፋኖስ ማር)፡- ጥቅምት14 የገዳሙ መስራች የነበሩት የአቡነ አረጋዊ የእረፍት እለት ነው፡፡ ይህችን አለምን ዞረው ህሙማንን ፈውሰው፣ ለምጽ አንጽተው፣ እውራንን አብርተው ሲኖሩ ወደ ፈጣሪያቸው ለምነው የተለዩባት እለትና የእረፍት ቀናቸው ስለሆነች በዚች ቀን ታስቦ የሚቆረጥ ማር ፍቱን መድኃኒት ነው፡፡ እግዚአብሔርም እሳቸውን ለክብርና ለሞገስ ያበቃበት እለት በመሆኑ፤ በእረፍታቸው ቀን የተቆረጠው ማር ፈውስ ይሆናል፤ በማለት ጥቅምት 14ን ታሳቢ በማድረግ ለመድኃኒት የሚውል ማር እንደሚቆርጡ አስረድተውኛል፡፡ ጥቅምት 17 የሚቆረጠው ማር የእስጢፋኖስ ማር ይባላል፡፡ እስጢፋኖስ የተባለው ሰማዕት በድንጋይ ተወግሮ ያረፈበት፤ ከፈጣሪው ክብርና ጸጋን አግኝቶ ያረገበት እለት ስለሆነ በዚህ ቅዱስ ሰማእት እረፍትና እለት የተቆረጠ ማር ፈውስ ነው፤ በማለት ገልጸዋል (መሪጌታ ካሳ መንገሻ፣ መሪጌታ መስፍን ገብሬ፣ መሪጌታ ጌታቸር ሽዋንግዛው፤ ሚያዝያ/2003ዓ.ም)፡

፡

በአጠቃላይ ከባህል ህክምና ባለሙያዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ለመድኃኒት መቁረጫ፣ መቀመሚያና መስጫ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፤ የጌሾ አንካሴ እና የወይራ አንካሴ፣ ሁለት ሰይፍ ያለው የቀንድ ካራ፣ የወይራ ዛቢያ፣ መዳመጫ፣ አለሉ፣ የማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይ፣ ሙቀጫና ወፍጮ፣ ሲሆኑ ከሰውነት አካል አፅቅና ጋት (የትንሿ ጣትና የእጅ መዳፍ) ለመድኃኒት መለኪያ ያገለግላሉ፡፡ መድኃኒቶችን ለማዋሃድና ለመቀመም ደግሞ ወፍ ያልቀመሰው እና ሴት ያልቀዳው ውሃ ይፈለጋል፡፡ ለአንዳንድ በሽታዎች የእማምሳይ ላም ቅቤ ተለውሶ ለመድኃኒትነት ይውላል፡፡ ለመድኃኒት የሚውሉ እፀዋት እህል ሳይቀምሱ በራቁት ሆድ[በባዶ ሆድ]፣ ሳይኮሱ [ዓይነምድር ሳይወጡና ሳይጸዳዱ] ማክሰኞ፣ ረብዕ እና ዓርብ ዕለት እንደሚቆርጡ ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በእነዚህ እለታት እፀዋቱ የሚቆረጡበት ምክንያት ሐይማኖታዊ ይዘት ያለው መሆኑን ከመስክ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

## 4.3 የባህል መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ

### 4.3.1 የባህል መድኃኒት ቅመማ

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች እፀዋትን፣ እንስሳትን፣ ማእድናትን እና ነፍሳትን ለባህላዊ መድኃኒት መቀመሚያነት እንደሚጠቀሙባቸው በጥናቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡ ፡ለባህል መድኃኒት መቀመሚያ የሚውሉ ግብዓቶች፡- ከእፀዋት፤ ቅጠል፣ ሥር፣ ግንድ ፣ ቅርፊት፣ አበባ፣ ፍሬ፣ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከእንስሳት፤ ሞራቸው፣ ስጋቸው፣ ደማቸው፣ አጥንታቸው፣ ጉበታቸው፣ ወተታቸው ለባህል መድኃኒት መቀመሚያ እንደሚያገለግሉ ተጠቁሟል፡፡ ከማዕድናት፤ የድንጋይ ሽበት፣ መብረቅ የመታው አፈር፣ የጉንዳን ኩይሣ ይጠቀሳሉ፡፡ ከነፍሳት ደግሞ ሙሉ አካላቸውን በመውሰድ ለመድኃኒት መቀመሚያ እንደሚያገለግሉ ከመስክ ስምሪቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

"የባህል መድኃኒት ቅመማ የጀመረው አባታችን ኖህ ነው" በማለት ከቡድን ተወያዮች መካከል መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ ያስረዳሉ፡፡

> ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ኖህ በመርከብ ላይ ተንሳፎ እንዳለ አንድ ሺ አምስት መቶ እፅዋትን 'እፅ የሐዩ እፅ ይቀትል' በማለት ገልፆለታል፡፡ ይህ ማለት 'እፅ ያድናል እፅ ይገላል' ማለት ነው፡፡ ኖህ ግን አንድ ሺውን ፈጽሞ ተግባር ላይ ካዋለ በኋላ፤ አምስት መቶ ሲቀረው ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል፤ በማለት የመድኃኒት ቅመማ አጀማመርን ከሐይማኖት አንፃር ገልጸዋል፤ (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)፡፡

በባህላዊ መድኃኒት ቅመማ ሂደት ለፈውስ የሚውሉ ግብዓቶች በተናጥል ወይም በጥምረት ተቀምመው ይዘጋጃሉ፡፡ የባህል ሐኪሞች ለአንድ በሽታ ከሁለትና ሶስት በላይ ተጓዳኝ የሆኑ እፅዋትን በተናጠል በማዘጋጀትና በመቀመም አማራጭ የህክምና አገልግሎትን እንደሚጠቀሙ ከመስክ ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ "ለወፍ" በሽታ፤ የስሚዛ (ሰንሰል) ቅጠል፣ የአሮጊት ፍቅር ቅጠል፣ የድግጣ ቅጠል፣ የእፀ ሳቤቅ (ሃረግ ሬሳ) ቅጠል እና የመሳሰሉትን" በአማራጭነት መጠቀምና መስጠት እንደሚቻል ያስረዳሉ (መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ፣ የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ፣ መሪ ጌታ ኃይሉ ፍሰሃ እና ደብተራ በየነ አበጋዝ፤ ሚያዝያ 17-29/2003 ዓ.ም)፡፡



ስሚዛ/ሰንሰል/



የአሮጊት ፍቅር



ድግጣ

ከዚህ አንጻር የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለታካሚዎቻቸው አማራጭ መድኃኒትን ቀምመው እንደሚሰጡ በተካሄደው የቡድን ውይይት ለማወቅ ተችሏል (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)። በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች በሽታን የመለያ ዘዴዎቻቸው እና የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልታቸውን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ከዚህ በታች የቀረበ ሲሆን የበሽታው ዓይነት፤ በሽታውን የመለያ ዘዴዎች፣ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፅዋት፣ እንስሳት ፣ ማዕድናትና ነፍሳት፤ ለመድኃኒትነት የሚውለው ክፍላቸው እና አካላቸው፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደታቸው ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ቀርቧል።

በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የበሽታው ዓይነት | በሽታውን የመለያ ዘዴዎች | ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት እንስሳት፣ ማዕድናትና ነፍሳት | | ለመድኃኒት የሚውሰው የእፀዋት ክፍል፣የእንስሳት አካል፣የማዕድናት አይነት | የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ [19] በአዋቂ ሰው መጠን ልክ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የወፍ በሽታ | • የምግብ ፍላጎት ትቀንሳለች<br>• አይንና ጥፍር ቢጫ ታደርጋለች<br>• ምግብ ሲሸት ታቅለሸልሻለች<br>• አክታ ታበዛለች<br>• በእቃ ባደረ ሽንት ላይ አረንጓዴ ምልክት ታወጣለች/ትሰራለች<br>• ምላስ ታነጣለች | ሀ | የድግጣ | ቅጠል | የድግጣ ቅጠሉን አድርቆና ደቁሶ ግማሽ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ጣሳ ውሃ ላይ ጨምሮ ማጠጣት |
| | | | ለ | የአህያ ኮሸሽላ | ፍሬ | የአህያ ኮሸሻላ ፍሬን ወቅጦና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ብርጭቆ የፈላ ውሃ በጥብጦ ለሳምንት ማጠጣት |
| | | | ሐ | የብሣና | ቀንበጥ | የብሳና ቀንበጡን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከሁለት ስኒ ነጭ ማር ጋር ለውሶ ለአራት ቀን ጧት ጧት ማብላት |
| | | | መ | የእፀ ሣቤቅ/ሐረግ ሬሳ/ | ቅጠል | የእፀ ሳቤቅን ቅጠል ቀጥቅጦ በአንድ ብርጭቆ ውሃ አፍልቶ ጨው ጨምሮ ጧትና ማታ አንድ ስኒ ማጠጣት |
| | | | ሠ | የእንቧጮ | ስር፣ቅጠሉና እንጨቱ | የእንቧጮ ቅጠሉን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከሁለት ስኒ ማር ጋር ደባልቆ ለሶስት ቀን እንደሻይ ማጠጣት |
| | | | ረ | የእሬት | አበባ | የእሬት አበባን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርብ ማንኪያ ዱቄት ከሁለት ስኒ ማር ደባልቆ ለሶስት ቀን እንደሻይ ማጠጣት |
| | | | ሰ | የአሮጊት ፍቅር | ቅጠል | አድርቆና ሰልቆ አንድ ሾርባ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ብርጭቆ ውሃ በጥብጦ ማጠጣት ወይም ቅጠሉን ቀቅሎ አጥሎ አንድ ስኒ በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ሸ | የሰንሰል | ቅጠል | የሰንሰል ቅጠልን ጨቅጭቆ በአንድ ብርጭቆ ውሃ አፍልቶ፣ በአንድ ጣሳ ጠላ ደባልቆ ሁለት ቀን ምግብ ሳይበሉ ማጠጣት |

[19] በመስክ ቆይታዬ እንዳረጋገጥኩት የባህል ሐኪሞች በመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት ወጥ መለኪያን የላቸውም፤ የመድኃኒት አሰጣጡም ቢሆን የባህል ሐኪሙን እውቀትና የህመምተኛውን ወቅታዊ ሁኔታ በማገናዘብ የሚሰጡ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። በዚህ ሰንጠረዥ የተገለጹት መለኪያዎች አውራ የመረጃ አቀባዮች የሰጧቸውን ማዕከላዊ መስፈርት(የጋራ መለኪያ) መበመውሰድ የተዘጋጁ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የጭርት በሽታ | በፊት ገጽ ላይ ክብ በመስራት ነጣ ነጣ ያለ ምልክት ታወጣለች፤ | ሀ | የብሣና | ቀንበጥ | የብሳና ቀንበጡን ጨምቆ ከቀንበጡ የሚወጣውን ፈሳሽ አዘውትሮ መቀባት |
| | | | ለ | የፓፓያ | የፓፓዬ ልጣጭ | የፓፓዬ የልጣጩን የውስጥ ክፍል በመቀባት ፀሐይ ላይ መሞቅ |
| | | | ሐ | የፍየለ ፈጅ | ፍሬው | የፍየል ፈጅ ፍሬውን ደቁሶ በድኚ ለውሶ ጧትና ማታ መቀባት |
| | | | መ | የጅብ ሽንኩርት | አበባው | የጅብ ሽንኩርት አበባውን ደቁሶ ከማምሳይ ላም ቅቤ ጋር ለውሶ ማታ ማታ ቀብቶ ማሳደር |
| | | | ሠ | የቀጋ | አበባው | የቀጋ አበባውን ደቁሶ ከማምሳይ ላም ቅቤ ጋር ለውሶ ማታ ማታ ቀብቶ ማሳደር |
| | | | ረ | የዘንባባ | ፍሬው | የዘንባባ ፍሬውን ወቅጦና ደቁሶ ከማምሳይ ላም ቅቤ ጋር ለውሶ ማታ ማታ ቀብቶ ማሳደር |
| | | | ሰ | የችፍርግ | ሥርና አበባው | የችፍርግ ስርና አበባውን አድርቆና ወቅጦ ከማምሳይ ላም ቅቤ ጋር ለውሶ ማታ ማታ ቀብቶ ማሳደር |
| | | | ሸ | የወፌ ጎመን | ቅጠሉ | የወፍ ጎመን ቅጠሉን ጨምቆ መቀባትና መፈግፈግ |
| | | | ቀ | የአወጥ | ፍሬውና ቅጠሉ | የአውጥ ፍሬውን እያፈረጡና እየጨመቁ መቀባት |
| | | | በ | የወይናግፍት | ቅጠሉ | የወይና ግፍት ቅጠሉን ቀጥቅጦና ጨምቆ ማሰር |
| 3 | የኮሶ በሽታ | -ከንፈርን ያነጣል<br>-ከሰገራ / ከኩስ ጋር ነጫጭና ጠፍጣፋ .ትል አብሮ ይወጣል<br>ያቅለሸልሻል<br>ሆድ ይነፋል<br>ክብደት ይቀንሳል<br>ፊንጢጣን በማሳከክ ብቻውን ይወጣል | ሀ | የመተሬ | ፍሬው | የመተሬ ፍሬን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሾርባ ማንኪያ የመተሬ ዱቄት ከሁለት ስኒ ነጭ ማር ጋር በጥብጦ ማጠጣት |
| | | | ለ | የኮሶ ዛፍ | አበባው፣ቅርፍፊቱና ሥሩ | የኮሶ ዛፍ አበባ ቅርፊት ሥሩን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሾርባ ማንኪያ የኮሶ ዛፍ ዱቄት (ከሶስቱ ተቀምሞ) በሙዝ ወይም በጥቁር ጤፍ ቂጣ ማብላት |
| | | | ሐ | የእንዳሁላ | ቅጠሉ | የእንደሁላ ቅጠሉን አድርቆና ወቅጦ ግማሽ የሾርባ ማንኪያ እንደሆላ ቅጠል ዱቄት ከአንድ ብርጭቆ የሱፍ ውሃ ደባልቆ ማጠጣት |
| | | | መ | የወገርት | ሥሩ | የወገርት ስሩን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከኑግ ልጥልጥ እና ከቀይ ጤፍ ቂጣ ጋር ደባልቆ ማብላት |
| | | | ሠ | የደድሆ | ሥሩ | የደድሆ ሥሩን አድርቆና ወቅጦ ግማሽ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በግማሽ ስኒ ማር በጥብጦ ማጠጣት |
| | | | ረ | የጠንበለል | ቅጠሉ | የጠንበለል ቅጠሉን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በግማሽ ስኒ ውሃ በጥብጦ ከቀይ ጤፍ እንጀራ ጋር ደባልቆ ማብላት |
| | | | ሰ | የዱባ | ፍሬው | የዱባ ፍሬውን አድርቆ ሶስት ስኒ የዱባ ፍሬ መጠን በምጣድ አምሶ ማብላት |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የስኳር በሽታ | • በሽንት ውስጥ የስኳር መጠን ይበዛል<br>• ክብደት ይቀንሳል<br>• ያልባል ሰውነትን ያሳክካል<br>• ታካሚው ሽንቱን ሲቀምስ ስኳር ስኳር ይለዋል።<br>• ታካሚው ክንዱን ሲጠባ ስኳር ስኳር ይለዋል<br>• ታካሚው ሽንቱን ጥቁር ድንጋይ ላይ ሲሸና ነጭ ምልክት ያወጣል፤ዝንቦች ይወሩታል<br>• የታካሚውን ሽንት ጉንዳን ያለበት አካባቢ ሲያፌሱት ስኳር ከሆነ በሽታው ወረው ይልሱታል | ሀ | የእንጆሪ | ቅጠሉ | የእንጆሪ ቅጠል አድርቆና ሰልቆ ግማሽ ስኒ ዱቄት ከአንድ ብርጭቆ ወተት ጋር በማደባለቅ ጧት ጧት ማጠጣት |
| | | | ለ | የወርቅ በሜዳ | ስር | የወርቅ በሜዳ ስር በአንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ብርጭቆ ወተት ጋር በማደባለቅ ጧት ጧት በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ሐ | የዶቅማ | ፍሬ | የዶቅማ ፍሬን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሻይ ማንኪያ ከአንድ ብርጭቆ ወተት ጋር ደባልቆ በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | መ | የመቅመቆ | ስር | የመቅመቆውን ስር አድርቆና ወቅጦ አንድ ሻይ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ብርጭቆ አሬራ ጋር በመደባለቅ ጧት ጧት በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ሠ | የእንጆሪ፣ የፓፓያ፣ የጎርጠብ፣ የአጋም | ቅጠል | የእንጆሪ፣ የፓፓዬ፣የጎርጠብ እና የአጋም ቅጠላቸውን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከሁለት ስኒ ወለላ ማር ጋር ደባልቆ ጧት ጧት ባዶ ሆድ አንዳንድ ማንኪያ ማጠጣት፤ |
| 5 | የእብድ ውሻ በሽታ | • የተለከፈው ሰው ይንቀጠቀጣል<br>• የተነከሰበት ልሃጭ ይቀራል<br>• ከቆየ እራሱን ይስታል፣<br>• ወደ እብደት ይቀይረዋል<br>• ልቡን ይሰውረዋል | ሀ | የአሰርኩሽ ተበተብኩሽ | ስር | የአሰርኩሽ ተበተብኩሽ ስሩን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ ውሃ ጋር በጥብጦ ለሁለት ቀን ማጠጣት |
| | | | ለ | የመካን እንዶድ | ስር | የመካን እንዶድ ስሩን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከግማሽ ስኒ ማር ጋር በጥብጦ መጠጣት |
| | | | ሐ | የሰንሰል | ስር | የሰንሰል ስሩን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ ማር ጋር በመደባለቅ በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | መ | የመቅመቆ | ስር | የመቅመቆ ስሩን ወቅጦና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ ማር ጋር በመደባለቅ በባዶ ሆድ ማጠጣት |
| | | | ሠ | የአባሎ | ስር | የአባሎን ስሩን አድርቆና ሰልቆ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት በቀይ ጤፍ እንጀራ ፈትፍቶ ማብላት |
| 6 | የአልማዝ ባለጭራ በሽታ | • እንገት፣ ግንባር ደረት ጀርባ ላይ ችፍ በማለት ትጀምራለች<br>• አንድ መስመር በመያዝ ትሰፋለች<br>• ሰውነትን ትለበልባለች<br>• ታቃጥላለች(ውሃ ትቋጥራለች)<br>• አባራ ሲነካ ትገናለች | ሀ | የእሬት | ፈሳሽ | የእሬት ፈሳሽ ከጎርጠብ ቅጠል ዱቄት ጋር ደባልቆ መደምደም |
| | | | ለ | የጎርጠብ | ቅጠል | የጎርጠብ ቅጠሉን አድርቆና ሰልቆ ሁለት የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከግማሽ ብርጭቆ ወለላ ማር ጋር ደባልቆ በየቀኑ ቁስሉን መቀባት |
| | | | ሐ | የነጭ ሽንኩርት | ፍሬው | የነጭ ሽንኩርት ፍሬውን ከፌጦ፣ ከድንብላል ጋር አዋህዶ ወቅጦ በማምሳይ ላም ቅቤ ለውሶ መቀባት |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መ | የብሳና | ቀንበጥ | የብሳና ቀንበጡን አድርቆና ወቅጦ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ የተጨቀጨቀ ነጭ ሽንኩርት ጋር አዋህዶ በእማሆሳይ ላም ቅቤ ለውሶ መቀባት፡፡ |
| 7 | የቆረቆር በሽታ | • አልፎ አልፎ በራስ ላይ ልጥፍ ያለ ቁስል ይወጣል፡፡<br>• መግልና እኸ ያፈሳል<br>• እየባሰ ከሄደ ፀጉር ይመልጣል | ሀ | የአንፋር | ቅጠል | የአንፋር ቅጠሉን አድርቆና ወቅጦ አንድ የሾርባ ማንኪያ ዱቄት ከግማሽ ስኒ ቅቤ ጋር ለውሶ መቀባትና በየቀኑ መቀየር |
| | | | ለ | የተልባ | ፍሬ | የተልባ ፍሬው ወቅጦ በለጋ ቅቤ ለውሶ ማሰርና በየቀኑ መቀየር |
| | | | ሐ | የእፀ ፋርስ | ቅጠልና ፍሬ | የእፀ ፋርስ ቅጠሉንና ፍሬውን ፈጭቶ እና ደቁሶ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከግማሽ ስኒ ቅቤ ጋር ለውሶ መቀባት |
| | | | መ | የጧጧቴ | ፍሬ | የጧጧቴ ፍሬውን ፈጭቶና ደቁሶ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከለጋ ቅቤ ጋር ለውሶ መቀባት |
| | | | ሠ | የዶቅማ | ተቀፅላ | የዶቅማ ተቀፅላን አድርቆና ሰልቆ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ ቅቤ ጋር በማደባለቅ መቀባት |
| 8 | የብጉንጅ በሽታ | • ሲጀምር እንደ ብጉር ጫፉ ይቀላል<br>• ዙሪያው ይደድራል<br>• ብርድ ብርድ በማለት የአካል ሙቀት ይጨምራል<br>• በውስጡ መግል ይቋጥራል | ሀ | የቀይ ሽንኩርት | ቅርፊት | የቀይ ሽንኩርት ቅርፊቱን ጨቅጭቆ ሞቅ በማድረግ በለጋ ቅቤ ለውሶ ማሰር |
| | | | ለ | የእሬት | ሙርኝ | የእሬት ሙርኝን በእሳት እያሞቁ መተኮስ እና አስሮ ማሳደር፣ ከበሰለ በኋላ ማፍረጥና ሰንኮፉን ማውጣት |
| | | | ሐ | የእንዳሁላ | ቅጠል | የእንዳሁላ ቅጠሉን እያሞቁ መተኮስ እና በዶሮ ላባ እያጠቡ ማር መቀባት |
| 9 | ለሚከሳ ልጅ | • ሰውነቱን ለሚያመነምነውና ለሚከሳ ልጅ | ሀ | የሸኮኮ | ስጋ | የሸኮኮ ስጋን ዘልዝሎና አድርቆ በጨው አሽቶ ቋንጣውን ማብላት |
| 10 | የነቀርሳ በሽታ | • | ሀ | የቀበሮ | ጉበት | የቀበሮ ጉበት ከጥቁር ስንዴ ጋር በመቀላቀል አድርቆና በእንክብል መልክ አዘጋጅቶ በቆሰለው ቀዳዳ በኩል ማስገባት |
| 11 | የቆንጣጭ በሽታ | • በእጅ ጣት ላይ ክርክር ይሰራል<br>• ጣትን እያመነመነ ይቆርጣል<br>• ይነዘንዛል ድንገት ይደማል | ሀ | የአሙኝ | አካል በሙሉ | የአሙኝን ነፍሳት ከምሬንገ// ከተቀፅላ ጋር በመደቆስና በመቀመም ቁስሉ ላይ ማሰር |

ምንጭ፡- ከቡድን ውይይት፣ ከመስክ ጥናትና ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ (ሚያዝያ/ 2003 ዓ.ም)

### 4.3.2 የባህል መድኃኒት አሰጣጥ

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለፈውስ አገልግሎት ያዘጋጇቿውን መድኃኒቶች ከመስጠታቸው በፊት የታካሚዎቻቸውን አቅም እና የበሽታውን ዓይነት ይለያሉ። ለምሳሌ የታካሚው እድሜ፣ ፆታ፣ የህመምተኛውን ሁኔታ፣ በሽታው በህመምተኛው ላይ ያደረሰውን ጉዳት… ከግምት በማስገባት፤ የበሽታውን ዓይነት ያጤናሉ። ግላዊ ሙያቸውን እና እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ ለበሽታው ተገቢ ነው የሚሉትን መድኃኒት አዘጋጅተው ይሰጣሉ።

አዘጋጅተው የሚሰጧቸው መድኃኒቶች፤ በሚሸተት፣ በሚታጠን፣ በሚቀባ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታሰር፣ በሚታኝክ፣ በሚቆረጠም፣ በሚጠጣ፣ በሚበላ እና በመሳሰሉት ይሰጣሉ። እነዚህ የባህል ሐኪሞች ያዘጋጁትን መድኃኒት በመስጠት ብቻ የሚገደቡ ሳይሆን ስለ አወሳሰዱ እና አጠቃቀሙ መመሪያ ይሰጣሉ ። የመመሪያው ሂደትም ለታካሚው የተሰጠው መድኃኒት በስንት ሠዓት እንደሚወሰድ፣ ምን ምግብ መበላት እንዳለበት እንደሌለበት፣ ከምን ከምን ነገሮች መቆጠብ እንዳለበት፤ ምናልባት የተሰጠው መድኃኒት የሚጎዳውና የሚያዳክመው ከሆነ ማርከሻው ምን እንደሆነ በዝርዝር በማስረዳት ያዘጋጁትን መድኃኒት እንደሚሰጡ በመስክ ስምሪቱ ለመገንዘብ ተችሏል፤ (ሚያዝያ 13-29/2003 ዓ.ም)።

መሪ ጌታ ካሣ መንገሻ የባህል መድኃኒት አሰጣጡን ሂደት እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> ካነጋገሩ፣ ካለው ህመምተኛው መጀመሪያ ቁጭ ብሎ እንዲያጫውተን እናደርጋለን። ካነጋገሩ፣ ካለው ፈገግታ፣ ካለው ሁኔታ ሂደቱን በሚገባ ከተረዳን በኋላ፤ ጥፍሩን በመመልከት፣ አይኑን በመመልከት፤ የበሽታውን ሁኔታ በተለያየ መልኩ ለመረዳት እንሞክራለን። እኛ መድኃኒት መስጠት የምንችለው እንደሰውየው የእድሜ ክልል፣ መበርታትና መቀነስ የመሳሰሉትን ከሰውየው ሁኔታ ከተረዳን በኋላ በማንኪያ፣ በስኒ (በፍንጃል)፣ በብርጭቆ እየለካን እንሰጣለን። የሚወስደውን መድኃኒት ከምግብ በፊት፣ በኋላ የሚለውን እንደበሽታው አይነት እናዝዛለን ለምሳሌ ለረጅም ጊዜ ሆዱን ታሞ የሚመጣ ህመመተኛ፤ መድኃኒት ከመስጠታችን በፊት ያልበካ የቀይ ጤፍ እንጀራ እሩብ (አንድ አራተኛ) መጀመሪያ እንዲቀምስ እናደርጋለን። መድኃኒቱን ከአቦል ቡና አድርገን በስኒ እንዲጠጣ ይደረጋል። ሰውየው አንድ ጊዜ ኻው አድርጎ ይጠጣል። ያንን ከጠጣ በኋላ አራት ሰዓት ከምግብ ነጻ እንዲሆን ይደረጋል። አራት ሰዓት ከሞላው አስራ አራት ቀን የተጠመቀ ጠላ (የበሰለ ጠላ) እንዲጠጣ ይደረጋል። ከዚያ በተቅማጥና በሽንት ሆዱ ውስጥ ያለው ትላትል ሁሉ ውልቅ ብሎ ይወጣለታል። መድኃኒቱ የሚጣላው ከሆነ ማርከሻ የገብስ በሶ ወይም የዶሮ ጉበት እንዲበላ ይደረጋል፤ በማለት የአሰጣጥ ሂደቱን ያስረዳሉ (ሚያዝያ 17/2003 ዓ.ም)

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚገልጸው፤ የባህል ሐኪሞች ያዘጋጁትን መድኃኒት ለመስጠት መጀመሪያ የታካሚዎቻቸውን የበሽታ አይነትና አቅም ከተገነዘቡ በኋላ እንደ ህመምተኛው አቋም፤ የመድኃኒቱም አይነት እየታየ በማንኪያ፣ በስኒ (በፍንጃል)፣ በብርጭቆና በመሳሰሉት መለኪያዎች በመጠቀም ያዘጋጁትን መድኃኒት መጥነው ይሰጣሉ። የአወሳሰዱን

ሂደትና መመሪያ በቃል ይገልጻሉ። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተቀራረበ መልኩ የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ስለባህል ህክምና የመድኃኒት አሰጣጥ ሂደት እንደሚከተለው አስረድተዋል፡

> መድኃኒት ከመስጠቴ በፊት የበሽታውን ሁኔታ ከግምት አስገባለሁ። ከበሽታው አኳያ አይቼ ፣ ከህመሙ ዓይነት በመነሳት፣ የተቀመሙ እፅዋትን እሠጠዋለሁ። ስሰጠው የመድኃኒት መለኪያ መጠን አለኝ። ለምሳሌ፡- በዘመናዊ ህክምና መድኃኒቶችን በእንክብል መልክ እያዘጋጁ ይሠጣሉ። እኔም በዛ ታማሚ ላይ ቁስል ከሆነ በቀን ሶስት ጊዜ የሚቀባ አለ፣ አንድ ጊዜ የሚቀባ አለ። ቁስሉ ሲቀባ በሳሙና እያጠቡ በመቀባት ይታከማል። ለምሳሌ፡- በጆሮ ላይ ኢንፌክሽን ሲፈጥር፤ ከእፀዋት ሰብስቤ ቀምሜ በንጹህ ጨርቅ አጥልዬ ያበቀመጥኩትን ጠብታ ጧት፣ ቀን፣ ማታ እሰጣለሁ። እንደታካሚው ሁኔታ፣ አዋቂ፣ ህፃን፣ የመሳሰሉትን እለይና በደረጃው ይሄን ያህል ተጠቀሙ ብዬ፣ ለሶስት ቀን፣ ለአራት ቀን እንዲጠቀሙ እሰጣለሁ። ይህንን ያህል ተጠቀሙ፣ በዚህ አድርጋችሁ ላኩ[ስጡ] በማለትና ከዚያ በላይ ከተጠቀሙ ጉዳት እንደሚያደርስ በማስገንዘብ እሰጣለሁ። ምግብ ሳይበሉ በባዶ ሆድ ወይም በልተው የሚሰጡ አሉ። ለምሳሌ፡- የወስፋት ወይም የኮሶ መድኃኒት በባዶ ሆድ ይሰጣል። ለቁስል ነክ ነገሮች ደግሞ ምግብ ወስደው ቢቀቡ የሚያመጡት ችግር የለም፤ በማለት ይገልጻሉ (ሚያዝያ 25/2003 ዓ.ም)።

የባህል ሐኪሞች በተለያየ መልኩ ያዘጋጇቸውን መድኃኒቶች በመመጠን፤ ከምግብ በፊት የሚወሰዱና የማይወሰዱ መሆኑን፣ ያለአግባብ ከተወሰዱ የሚያስከትሉትን ጉዳት በማስገንዘብ ይሰጣሉ። ምግብ ተበልቶና ሳይበላ የሚወሰዱ መድኃኒቶች ለምን አይነት በሽታ እንደሆኑ የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ ይገልጻሉ።

> የበሽታው አይነት ቁስል ከሆነ ምግብ ወስደው መድኃኒት እንዲወስዱ ይደረጋል። እንደ ወስፋት እና ኮሶ ላሉት እንዲያውም እርቦት ሰውየውን የማቅለሽለሽና የመፋቅ ባህሪ ሲያመጣ ያንግዜ ሞቅ ሲለው ሰውየው መድኃኒቱን ሲቀምስ በውስጥ ያለው በሽታ እህል መጣልኝ ብሎ ሃው! ብሎ [በፍጥነት] ያንን መድኃኒት ሲቀምስ ይሞታል። ለውስጥ ትላትሎች በራቀት ሆድ ቢሆን ይመረጣል። ለዚህ ሶስት ሰዓት ከቆየ በኋላ ኩርጥ [ኮስተር] ያለ ወጥ ይሰራል። በዚህ ላይ ጠላ ቢጠጣ ውልቅልቅ አድርጎ ነው የሚጥለው። እንደነቀርሳ፣ ገስጋሽ፣ ሰፎ ለመሳሰሉት ቁስሎች አተር፣ ሽንብራ፣ ስንዴ ከበሉ ቁስሉ የመቆጣት ፀባይ ያመጣል። ገብስ፣ ባቄላ፣ መብላት አለበት፤ የአገዳ እህል ከበሉ ቁስሉ ጉዳት ያደርሳል። ስንዴም ከበሉበት የመቆጣትና የማቃጠል ባህሪ አለው እሳት ነው።
> በማለት ያስረዳሉ (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)።

የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ ከአሁን በፊት ከተጠቀሱ የባህል ሐኪሞች በተመሳሰለ መልኩ ከምግብ በፊት የሚሰጡ መድኃኒቶች ለሆድ ትላትል በሽታዎች መሆኑን ያስረዳሉ። እንደ ነቀርሳ፣ ገስጋሽ እና ሰፎ ለመሳሰሉ ቁስል ነክ በሽታዎች ምግብ ተወስዶ መድኃኒት የሚሰጥ ሲሆን ህሙማን ከምግብ የአገዳ እህሎች፣ ሽንብራና ስንዴን መጠቀም እንደሌለባቸው ይገልፃሉ። በአንጻሩ እንደ ገብስና ባቄላ የመሳሰሉት መብላት እንዳለባቸው ይመክራሉ። አውራ የመረጃ አቀባይ የሆኑት የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱም ተቀምመው የተቀመጡ መድኃኒቶች እንዴትና መቼ እንደሚሰጡ፤ ህሙማን መድኃኒት ከወሰዱ በኋላ ከምን ከምን ነገሮች መቆጠብ እንዳለባቸው ያስረዳሉ።

> ታካሚዎች የሚበሏቸውና የማይበሏቸው ምግቦች አሉ። ታካሚው መድኃኒት ሲወስድ የአገዳ እህሎች ሰውነትን ስለሚቀረጣጥፉ፤ የአገዳ ጠላ፣ እንጀራ እንዳትበሉ ብዬ እከለክላለሁ። እንደ ገብስ፣ ባቄላ፣ አጃ የመሳሰሉትን እንዲመገቡ አደርጋለሁ። ምክንያቱም ሰውነትን ገንቢ ምግቦች ስለሆኑ የአካል ጉዳትን፣ ሥብራትን፣ ወደ ውስጥ ደም መፍሰስን የመሳሰሉትንና የተጎዳ አካሉን ወዲያውኑ ይገነቡለታል። መድኃኒት ከወሰዱ በኋላ አጥብቄ የምከለክለው ጥላ ወይም ፆታዊ ግንኙነትን ነው። መድኃኒቶችን ያረክስብኛል። ቀብር ረግጦ የመጣ፣ ለቅሶ ውሎ የመጣ አልኮል፣ ዶሮ እንዳይገቡ እከለክላለሁ፤ በማለት አስረድተዋል (ሚያዝያ 24/2003 ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ህመምተኞች መድኃኒት ከወሰዱ በኋላ እስከሦስት ቀን ድረስ በሚተኙበት ክፍል ከምግብ አገዳ እህሎች፣ ሽንብራና ስንዴ ይከለከላሉ ። እንዳሉ ከዚህም በተጨማሪ ወደህመምተኛው ክፍል እንዳይገቡ የሚከለከሉ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል። በመስክ ቆይታዬ ወቅት አስራ አንዱም የባህል ሐኪሞች ህሙማን፤ ከጥላ (ከፆታዊ ግንኙነት)፣ ከአልኮል፣ ጉልበቱ ከሚጮህ ሰውና ከዶሮ አይነጥላ መታቀብ እንዳለባቸው ገልፀዋል። ለዚህ ምክንያታቸው ህመምተኛውን ያዳክማል፣ በሽታው እንዲጠነክር ያደርጋል፣ መድኃኒቱን ያረክሳል ከሚል ልማዳዊ አመለካከት የመጣ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

በራቤል ጤና ጣቢያ በዘመናዊ ህክምና የተሰማሩት ባለሙያ ሐኪም ማሞ ተስፋዬ ስለባህላዊ መድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ የሚከተለውን ሃሳብ አቅርበዋል።

> የመድኃኒት አሰጣጣቸው ከባለሙያ ባለሙያ ይለያያል። አንደኛው በጣቱ ለክቼ ነው የምሰጠው ይላል፤ ሌላኛው የራሴ መለኪያ አለኝ ይላል፤ ተቆጥሮ የሚሰጥ ነው ይላል። መጠናቸው አይታወቅም። የመድኃኒቱ አይነት አንድ ቢሆንም አሰጣጣቸው ይለያያል። የመድኃኒት መለኪያ ዘዴያቸው የተለያየ ነው። አንዳንዱ ቆጥሮ ይሰጣል፤ አንዳንዱ አብዝቶ ይሰጧል፤ አንዳንዱ ደግሞ ለታማሚው መድኃኒት ሰጥቶ እንደዚህ አድርገህ ተጠቀም ሲል ይችላል። የሚሰጧቸው መድኃኒቶች መጠናቸው ያልታወቀ በመሆኑ አሳንሰውም ሆነ አብዝተው ጉዳት ሊያደርሱ ይችልሉ፤በማለት ይተቻሉ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

እንደ ሐኪም ማሞ ተስፋዬ ገለፃ የባህል ሐኪሞች የመድኃኒት አሰጣጥ ሥርዓታቸው ከባለሙያ ባለሙያ የተለያየ መሆኑን ጠቁመው፤ የሚሰጡት መድኃኒት የተጠና እና የተለካ ባለመሆኑ ግላዊ ምርጫንና ፍላጎትን መሰረት ያደረገና መለኪያ የሌለው በመሆኑ በህሙማን ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል አስገንዝበዋል።

በአጠቃላይ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት የተቻለው የባህል ሐኪሞች መድኃኒት ሲሰጡ ግላዊ እውቀታቸውንና ሙያዊ ችሎታቸውን ተጠቅመው የህመምተኛውን ሁኔታ፣ አቅም፣ እድሜ እና የመሳሰሉትን ከግምት በማስገባት በሽታውን ይለያሉ። የበሽታውን አይነት ከለዩ በኋላ አስፈላጊውን መድኃኒት ቀምመው ይሰጣሉ። ተቀምሞ የተሰጠው መድኃኒት ምግብ ተበልቶና ሳይበላ የሚወሰድ መሆኑን መመሪያ በመስጠት ቃላዊ ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ። መረጃው እንደሚያመለክተው ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ምግብ ሳይበላ የሚወሰዱ መድኃኒቶች ለሆድ ትላትል

(ጥገኛ ትሎች) ሲሆን ለቁስል ነክ በሽታዎች ግን ምግብ ተበልቶ መወሰድ እንዳለባቸው ከዘርፍ ባለሙያዎች ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች፤ ለህሙማን መድኃኒት ከሰጡ በኋላ ምን ዓይነት ምግብ መብላት እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ያስረዳሉ። በመጨረሻም ታካሚዎች ከህመማቸው እስኪድኑ ድረስ ከጥላ፣ ከአልኮል፣ ከፆታዊ ግንኙነት፣ ከዶሮና ከመሳሰሉት ነገሮች ተቆጥበው ወይም ተገልለው መቀመጥ እንዳለባቸው ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

## 4.4 የባህል ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስለባህላዊ ህክምና ጥበብ መማሪያ ስልቶች፣ የጥበቡ መተላለፊያ መንገዶች እና ጥበቡን ስለሚማሩ ሰዎች ምንነት ቅኝት ይደረጋል። በምዕራፍ ሶስት ንዑስ ርዕስ 3.1.7 እንደተጠቀሰው የባህል ህክምና ጥበብ አንድም ከቤተሰብ፣ ሙያው ካላቸው ሰዎች፣ የመድኃኒት አውደ ጥበብን በመስረቅና ገዝቶ በማጥናት፣ ከአብነት መምህራን፣ ሙያው ካላቸው ሰዎች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ ሙያውን መማርና መልመድ እንደሚቻል ተጠቁሟል።

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የባህል ህክምና ጥበቡን በተለያየ አጋጣሚ መማር እንደሚቻል ጠቁመው ከራሳቸው ተሞክሮ በመነሳት ያስረዳሉ። ይህን ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ መሪጌታ ካሳ መንገሻ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> ያሁን ሙያዬን ያገኘሁት በአብነት ትምህርት ቤት ነው። ዋድላ ደላንታ በቆሎ ትምህርት ቤት የዜማ ተማሪ ሳለሁ አለቃ ቀለም ወርቅ የሚባሉ መምህር ነበሩ። መጀመሪያ እውቀቱን ከሳቸው አገኘሁ። ከዚህ የተወሰኑ መድኃኒቶችን ለምጄ ወሎ ክፍለ ሀገር አማራ ሳይንት ተድባበ ማርያም በምትባል ቦታ ላይ ሙያዬን የበለጠ ላሰፋ ቻልኩ። ከዚህ በኋላ ሙያው እየጣመኝ ስሄድ ጎጃም ሞጣ ቀራንዮ ውስጥ ዲማ ጊዮርጊስ የምትባል ቦታ ሄድኩ፣ የቅኔ መምህራችን ብዛት ያላቸውን መድኃኒቶች አስተማሩኝ፤ እፀ ደብዳቤ በብራና የተፃፉ መጻህፍ አገኘሁኝ፤ ከዚህ በኋላ በግዕዝና በአማርኛ የተፃፉ ጽሑፎችን ለይቼ በማጥናት ሙያውን አዳብሬ መተዳደሪያዬ አደርጌዋለሁ። በማለት ይገልጻሉ (ሚያዝያ 17/2003 ዓ.ም)።




መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ የባህል ህክምና ጥበብን ከየት እንደተማሩት ገለፃ ሲያደርጉ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

ይህ ጥናት የተካሄደበት አካባቢ በአብዛኛው ነዋሪ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ነው። የህም በመሆኑ በመሪጌታና በደብተራ ደረጃ ያሉት የባህል ሐኪሞች በአብዛኛው ሙያውን የወረሱት ከአብነት ትምህርት ቤት ሲሆን የባህል ሐኪሞቹ ደግሞ ከቤተሠቦቻቸውና በግል ጥረታቸው ያዳበሩት ሙያ መሆኑን ከመስክ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። መሪ ጌታ ዲበኩሉ ዓግረ የህክምና ጥበቡን ከየት እንደለመዱትና እንዳገኙት የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል።

> እውቀቱን ከቤተሰብ የወረስኩት አይደለም። ከቤተክርስቲያን አባቶች ነው ። አሁን በባህል ህክምናውም በአብነት መምህርነቱም እየሰራሁ ነው። እኔንም ያስተማሩኝ እንደነ ሊቀ ሊቃውንት መንክር ከዚህም በተጨማሪ ወደ ሱዳን በመሄድ ተምሬያለሁ። በይበልጥ በአብነት ትምህርት ነው የተማርኩት፤ ለምሳሌ፡- በትግራይ፣ በጎንደር ቦጎጃምና በሸዋ በመዘዋወር ከአባቶች ተምሬያለሁ፤(ሚያዝያ 26/2003 ዓ.ም)።

የአብነት ትምህርት ቤት ለባህላዊ ህክምና መሰረት መሆኑን የሚገልጹት መሪጌታ ዲበኩሉ፤ ከቅኔ መምህራን፤ በጎንደር፣ በትግራይ፣ በጎጃምና በሸዋ በመዘዋወር የህክምና ጥበቡን አዳብረዋል። አሁን ለሚተዳደሩበት የህክምና ሙያ የአብነት ትምህርት ቤት መሰረት እንደሆናቸው ይገልፃሉ። የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው የወረሱት ሙያ መሆኑን እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> ልምዱን ከዘር ወይም ከቤተሠብ የወረሥኩት ነው። ከቤተሰብ ጋር አብሬ ስሰራ በዚያው ልምዱን እየቀሰምኩ፣ በታማሚው ላይ የታዩ ምልክቶችን በማጤን፣ በልምድ ያዳበርኩትን ተሞክሮ በመጠቀም በሽታውን እለያለሁ። በፊት ህክምና ስሰጥ ከእፀዋት ቀምሜ ስሰጣቸው ቢድኑ ሳይ፣ ታካሚዎቹን በመከታተል ልምድ እያገኘሁ መጣሁ። የህክምና ሙያዬን በሳይንስ ዓለም በመቃኘት ለዘመናዊ ህክምና የተፃፉ መጽሐፎችን፣ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ቅመማ ቅመሞችን፣ ለዶክተሮች ማገገሚ የተፃፉ የሳይንስ መጽሐፍትን በማንበብ፤ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር የተፃፉ መጽሐፎችን በማንበብ በማጤን.... የሰው ነርቮች ደም የሰዎችን ተክለ ሰውነት ከመነሻው እስከ መድረሻው እያለሁ። ወደ ሳንባችን ደም እንዴት ከየት ተነስቶ የት ቦታ ይፈሳል የሚሉትን እያለሁ። ወደ ሳንባችን ደም እንዴት ከየት ተነስቶ የት ቦታ ይፈሳል የሚሉትን፣ በነርቮች ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣ ማየትና እንደሚፈስ፣...በዚህ ጊዜ የነርቮች ሥርዓት፣ በነርቮች ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣ ማየትና መለየትን እችላለሁ።.... በቅርብ ከሚገኘው በራቤል ጤና ጣቢያ በመሄድ ከጤና ባለሙያዎች ጋር እየተወያየሁ እና እየተመካከርኩ ሙያዬን አሳደግሁ። እኔም እየነገርኳቸው እነሱም እያስተማሩኝ በዚህ መልኩ ሙያዬን እያዳበርኩ ነው፤(ሚያዚያ 24/2003ዓ.ም)።

የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ሙያውን የወረሱት ከቤተሰብ ቢሆንም ለዘመናዊው ህክምና የተዘጋጁ መጻሕፍትን በማንበብ፣ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ የህክምና፣ ጥበቡን አዳብረዋል። የባህላዊውንና ዘመናዊውን የህክምና አገልግሎት በማጣመር በመስኩ የሚሰጠውን የህክምና ሥርዓት በመቃኘት ከዘመናዊ ሐኪሞች ልምድ በመቅሰም ግላዊ እውቀታቸውን ያዳበሩ መሆኑን ገልጸዋል።

መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ ደግሞ ከቤተሰብ እና ከአብነት ትምህርት ቤት ሙያውን እንደወረሱት ያስረዳሉ።

ከቤተሰቦቼ በውርስ ያገኘኋቸው የህክምና መጻሕፍት አሉኝ፡፡ እነዚህ ከቆዳ የተሰሩ የብራና መጻሕፍት እፀ ደብዳቤዎችን፣ የያዙ ናቸው፡፡ የተለያዩ የህክምና አይነቶች የያዙ በመሆናቸው፤ እነሱ በሚያዙት መሰረት ነው ሰውን ማከም የቻልኩት፡፡ ይህን ሙያ ለመማር አስራ አምስት አመት ይፈጃል ይላሉ አባቶች፤ እኔ ግን በአስራ ሁለት አመት በአብነት ትምህርት ቤት ውስጥ ቆይቼ ብዙ ነገሮችን ተምሬ ወጥቻለሁ፤ የአባቴንም ሙያ አዳብሬያለሁ፡፡ የአብነት ትምህርት ቤት የተማርኩበት ቦታ በስና አንባ ሚካኤል [በግሼ ወረዳ ደል ቀበሌ ውስጥ የገኛል] ይባላል፤ መምህሬም አለቃ ወረሬ ይባላሉ፡፡ ከ300 በላይ የምንሆን ከጎንደር፣ ከጎጃም፣ ከመንዝ እና ከብዙ ቦታዎች የተሰባሰብን ሁሉ አንዳንድ ሙያዎችን ተወራርሰን፣ የተለዋወጥንበት አጋጣሚ አለ፤ በማለት ገልፀዋል (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)





*መሪጌታ መስፍን ገብሬ ካያታውና ካባታቸው የተላለፈላቸውን አስራ ሶስት የባህል መድኃኒት አውደ ጥበብ የብራና መጻህፍትን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ*

ከዚህ በላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው የባህል ህክምና ጥበቡን ከቤተሰብ የወረሱት ቢሆንም በአብነት ትምህርት ቤት ሙያውን ያዳበሩት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ሲማሩ ከሌሎች የአብነት ተማሪዎች ጋር ሙያዊ ምክክርና ልውውጥ በማድረግ የዛሬውን የህክምና እውቀታቸውን ቀስመውበታል፡፡ ይህንን የህክምና እውቀት መሰረት በማድረግ እና ከቤተሰብ የወረሷቸውን የብራና መድኃኒት ዓውደ ጥበብ እንደ መረጃ ማጣቀሻነት በመጠቀም የህክምና አገልግሎት እንደሚሰጡ አትተዋል፡፡

በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች የሚቀምሟቸው ባህላዊ መድኃኒቶች መነሻቸውም ሆነ መተላለፊያ መንገዳቸው ከሐይማኖት ተቋማት በተለይ ከአብነት ትምህርት ቤት (ከቆሎ ትምህርት ቤት) በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የባህል ህክምና ሙያውን አንድም በቤተሰብ በውርስ፣ በመልካም ሥነ ምግባር፣ ከአብነት መምህር፣ ሙያው ካላቸው የባህል ሐኪሞች፣ ከመድኃኒት አውደ ጥበቦች፣ ከህክምናው ዘርፍ የተለያዩ መጽሐፍትን በማንበብ እውቀቱን ማግኘትና ማስተላለፍ እንደሚቻል ከመስክ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ይህ ጥናት ታላሚ በአደረገው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ባህላዊውን የህክምና ጥበብ ተምረው በስፋት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ባለሙያዎች ወንዶች ናቸው፡፡ ሴቶች በባህል

ህክምናው ዘርፍ እንደወንዶቹ ጉልህ ድርሻ ለምን እንደሌላቸው መሪጌታ መስፍን ገብሬ ሲገልጹ
"በአብነት ትምህርት ቤት እንደወንዶቹ ጎላ ብለው አይሳተፉም። እኔ በምማርበት የአብነት
ትምህርት ቤት ከ300 ተማሪ ውስጥ አንድም ሴት የለችም ነበር። ሌላው ደግሞ አቅማቸው
አናሳነው ከሚል ግምት የመጣ ነው" በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፤(ሚያዚያ 20/2003ዓ.ም)።

መሪ ጌታ ጌታቸር ሽዋንግዛው ደግሞ ሴቶች እንደወንዶቹ በስፋት ያልተሰማሩበት ምክንያት
የስራውን ክብደት ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ እንደሚከተለው ገልፀውታል።

> በመድኃኒት አሰጣጥና አቀማመም ላይ እምብዛም ሴቶች አይሳተፉም። እንደ ወንዶቹ በመድኃኒት አሰጣጥና አቀማመም ላይ እምብዛም ሴቶች አይሳተፉም። እንደ ወንዶቹ በረሃ ሄደው ለመሰብሰብ ይቸግራቸዋል። ከአበው በቆየን ስርዓት ሴቶች ቤተመቅደስ ገብተው እንዲቀድሱ አልተፈቀዳላቸውም፤ የባህል ህክምናውም ቢሆን ለወንዶቹ እንጂ ለሴት ልጆቻቸው አያወርሱም። እርግጥ አንዳንድ ሴቶች ቀለል ቀለል ያለውን እንደ የሳም፣ የአህያ ሾተላይ የመሳሰሉትን በትንሹ ያስጠኗቸዋል። ከበድ ያለውን የመድኃኒት ቅመማ አባቶች አያስተምሯቸውም። ለዚህም ምክንያቱ የቤት ስራ ይበዛባቸዋል፣ የወር አበባ ይመጣባቸዋል፣ በረሃ ሄደው መድኃኒት መፈለግ አይችሉም..... ስለሚባል በአትኩሮት የሚያስተምሯቸው አባቶች የሉም። እንዲያውም ለሴት ልጅ ማስተማር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል በማለት አያስተምሩም (ሚያዝያ 18/2003ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ የቀረበው ገለፃ እንደሚያስረዳው፤ በልማድ ለሴት ልጅ መድኃኒት ማውረስ እምብዛም
አልተለመደም፤ ምክንያቱም ሴቷ ሙያው የሚጠይቀውን ጥረትና ጉልበት እንደወንዱ
ልትወጣው አትችልም በሚል፣ አቅሟ አናሳ ነው ከሚል ግምት፣ ከወር አበባ ማየት፣ ከልጅ
ማሳደግ እና ከቤተሰብ ኃላፊነት ጋር በተያያዘ የባህል ህክምና ጥበቡን እንድትለምድ
አይደረግም። ከዚህ ሀሳብ ጋር በተቀራረበ መልኩ የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ "የህክምና
ዘርፉ ሴት ወንድ በማለት የሚለይ ሣይሆን ከባህል፣ ከልማድና ከአበው የወረስነው ስርዓት
ነው፤ ሴቶችን ተሳታፊ ያላደረጋቸው" በማለት ያስረዳሉ። ይህንን እንዲህ ያብራሩታል።

> የባህል ህክምናው ሴት ወንድ የሚል አይመስለኝም። ስራው ከባድና ትኩረትን የሚጠይቅ በመሆኑ እንደወንዶቹ ተከታትለው አይሰሩትም ከሚል እሳቤ ነው። ሌላው ደግሞ ከንጽህና ጋር በተያያዘ የወር አበባ አለ፣ አራስ መሆን አለ፣ ህፃናት ማሳደግ አለ ህፃናት መድኃኒት ቢቀምሱ ጉዳት ያመጣል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሙያውን ለሴት ልጅ ማስተማር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል እያሉ አባቶችም አያስተምሯቸውም። ሴቶቹም ቢሆኑ ችግር ይገጥመናል እያሉ ሙያውን አይከታተሉትም። አባትም ለወንድ ልጁ እንጂ ለሴት ልጁ ትምህርት መስጠቱ ይቀራል፤በማለት አጫውተውኛል (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ ከመስክ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ህክምና
ባለሙያዎች ወንዶች ናቸው። ሴቶቹ በህክምና ዘርፍ ያለመሳተፋቸው ምክንያት ከቤተሰብ
ኃላፊነት፣ ልጅ ከማሳደግ፣ በአብነት ትምህርት ቤት እንደወንዶቹ ካለመማር፣ የወር አበባ
ማየት፣ ከአቅም ማነስ፣ ከአበው በመጣ ልምድ፣ እምነትና ሥርዓት "ሴትን ልጅ ማስተማር

ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል" ተብሎ መታሰቡ፤ የሙያ መስኩ ትኩረትና ክትትልን፣ አቅምና ጉልበትን የሚጠይቅ በመሆኑ እንደወንዶቹ ይሰሩታል ተብሎ በማህበረሰቡ ስለማይታመን አባቶች ለሴት ልጆቻቸው ሙያውን እንደማያወርሱ ለመረዳት ተችሏል። ይህ ሲባል ግን ለተወሰኑ በሽታዎች እፀ መድኃኒት ቆርጠው አይሰጡም ማለት አይደለም። ከአባት ወይም ከእናት የወረሷትን ጥቂት ልምድ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤ እንደ ወንዶቹ መተዳደሪያ አድርገው በባህል ህክምና ሙያ የተሰማሩ ሴቶች አለመኖራቸውን ከመስክ ከተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 4.5 የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት

በክለሳ ድርሳን ንዑስ ርዕስ 3.1.8 እንደተገለጸው የባህል ህክምና ጥበብ ድብቅና ምስጢራዊ እንደሆነ ተገልጿል። ምስጢራዊ መሆኑ የሕክምና እውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍ በመገደብ ጉዳት አድርሷል የሚል አመለካከት መኖሩም ቀርቧል። ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊ መሆን እንዳለባቸው ይሞግታሉ። ምስጢራዊ መሆኑ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ እንደሚያመዝን የባህል ህክምና ባለሙያዎች ያስረዳሉ። የህክምና ዘርፉ ምስጢራዊ መሆኑ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፆች እንዳይጠፉ፣ የታካሚውን ስነልቡና ለመጠበቅ እና አንዳንድ ተንኮለኛ ሰዎች ጉዳት እንዳያደርሱ መሆኑን መሪጌታ መስፍን ገብሬ እንዲህ ይገልጻሉ።

> የባህል መድኃኒቶች የሚደበቁበት ትልቁ ነገር መድኃኒቶቹ በየቦታው፣ በየእርሻ ማሳው የሚገኙ በመሆናቸው ሰው እየነቀለ እንዳያጠፋቸው በሚል ስጋት ነው። ሁለተኛው ህመምተኛው ተቀምሞ የተሰጠውን መድኃኒት ቢያውቀው እንዳያራክሰው እና እንዳይንቀው [ለተጠቀመው መድኃኒት ዝቅተኛ ግምት እንዳይኖረው]በማለት ነው። አንዳንድ እፀዋት ደግሞ በቀላሉ የማይገኙ በመሆናቸው ከምድረ ገጽ እንዳይጠፉ ያግዛል። ለምሳሌ፡- እፀ የሀዩ እፅ ይቀትል የምትባል ዕፅ አለች። እፅ ይቀትል የምትባለው የምትገድል ፍሬ ናት። እፅ የሀዩ ደግሞ የምታድን እፅ ናት። ለአንድ ሰው ያቺ እፅ ሰው የምትገድል ናት ቢሉት ለባለጋራው ሰጥቶ ሊገድልበት ይችላል። ሌላው ደግሞ ሲበሳጭ ራሱን ሊያጠፋበት ይችላል ስለዚህ በጣም ጠንቃቃና ባለሙሉ ተስፈኛ የሆነ ሰው መልመድና መስራት አለበት፤ በማለት ገልፀዋል፤ (ሚያዝያ 20፣2003 ዓ.ም)።

የባህል ህክምና ጥበብ በባለሙያ እጅ ካልተያዘ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን በማሰብ መሆኑን ከዚህ ገለፃ ለመረዳት ይቻላል። በተጨማሪም በየቦታው እፅዋት ለማግኘት፣ የተወሰኑት ደግሞ ጭራሹኑ እንዳይጠፉ ለማድረግ ፣ የታካሚውን ሥነ-ልቡና ለመጠበቅ እና ለክፉ ነገር እንዳይውሉ በማሰብ የህክምና ጥበቡ ምስጢራዊ መሆን እንዳለበት ያስረዳል። የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ስለባህል ህክምና ጥበቡ ምስጢራዊነት እንደሚከተለው አስረድተዋል።

> የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊ መሆን አለበት። ምክንያቱም ከአባቶች የተወረሰው ልማድ አንድ መድኃኒት ሲዘጋጅ እና ሲቀመም በንፅህና ሆኖ ከሰው ተሰውሮ መዘጋጀት

አለበት፡፡ አለበለዚያ ማንም ሰው ካወቃቸው ይረክሳሉ፣ ዋጋ ያጣሉ፡፡ ሌላው ደግሞ እፅዋት ሲቆረጡ የራሳቸው ስርዓተ ገቢር አላቸው፣ የገቢ ምንጭ ናቸው፣ መተዳደሪያ ናቸው፡፡ በጥንቃቄ ካልተያዙ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ መድኃኒት እንደሆነ እንኳ ቢታወቅ ባለሙያው አዘጋጅቶ እንዲሰጥ ነው የምመክረው፤ የህክምና ባለሙያውም መተዳደሪያው ስለሆነ ጠንክሮ ይሰራል፤ ከማኅበረሰቡ ክብር ያገኛል፡፡ መድኃኒት ተጠቃሚው የወሰደውን መድኃኒት ቢያውቀው፤ ስለሚጠራጠር አያድነውም፡፡ ሰዎች መጠንን አሳስተው እንዳይጠቀሙ በማለትም ነው፤(ሚያዝያ 24/2003 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያስረዳው፤ የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊ መሆኑ የእፅዋቱን ሥርዓተ ገቢር በተገቢው ለመፈፀም፣ የገቢ ምንጭ እና መተዳደሪያ መሆናቸው፤ የህክምና ባለሙያው በማህበረሰቡ እንዲከበር፣ መድኃኒቶች በአግባቡ በባለሙያ ተመጥነው እንዲሠጡ ሲባል ምስጢራዊ መሆን እዳለባቸው ይመክራሉ፡፡ መሪጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ደግሞ ሙያው ለማንኛውም ሰው መነገር እንደሌለበት ገልፀው፤ ህክምናውን መልመድና መማር ለሚፈልጉ ባለሙያዎች መነገር እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡

የባህል መድኃኒት መነገር የለበትም፡፡ አባቶችም በምስጢር መቀመምና መሠጠት አለበት ይላሉ፡፡ ሙያውን የሚማር ሰው ካለ ከእኛ ከአዋቂዎቹ ካልተተፋለት፤ ካማማስ፣ ካሰላለቅ እና ከቅመማ ሊያጠፋው ይችላል፡፡ ከሥሩ መነቀል ያለበትን ሊጎርድ ይችላል፤ የሚጎረደውን ሊነቅል ይችላል፡፡ የአባቶች ደንብ አለ ያንን ደንብ ከፈፀመ በኋላ ወይ በጉልበቱ፣ በገንዘቡ፤ በቡና፣ በስኳር እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ መድኃኒቱ ስሙር እንዲሆንለት ለተሰጠው እውቀት እሬንሣ[20] ይከፍላል፡፡ አባቶችም አቅማቸው እየደከመ ከእንግዲህ ወዲያ ምን ያደርግልኛል በማት ይሰጣሉ፡፡ ያለአግባብ የሰው ገንዘብ እንዳይበላበት ቃል ኪዳን[21] ይገባል፡፡ ለማንም ከሰጠው መድኃኒቱ ይረክሳል፤ ክብሩን ያጣል፤ (ሚያዝያ 18/2003 ዓ.ም)፡፡

እንደ መሪጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ገለፃ፤ ስራዬ ብሎ ሙያውን ለመማር የሚፈልግ ሰው እንደ መሪጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ገለፃ፤ ስራዬ ብሎ ሙያውን ለመማር የሚፈልግ ሰው እውቀቱ ከአላቸው ሰዎች "ካልተተፋለት" (እውቀቱ ተመርቆ ካልተሰጠው) በግል ጥረቱ እፀ መድኃኒቶችን ቢቆርጥ ከአተገባበር እንደሚያበላሻቸው፣ የሚሰጣቸው መድኃኒቶች ፈውስ እንደማይሆኑ ከልማድና ከእምነት አኳያ ያስረዳሉ፡፡

---

[20] እሬንሳ ማለት የእውቀት ወይም የሙያ ክፍያ ማለት ነው፡፡ አንድ የባህል ህክምና ጥበብን ለመልመድና ለመማር የሚፈልግ ተማሪ ለባህል ህክምና አዋቂዎች ላብና ሙያ የሚፈጽመው ክፍያ እንደሆነ መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሙያ የሚማር ተማሪ ጠንቃቃ፣ በማኅበረሰቡ የተመሰገነ፣ ምስጢር ጠባቂ፣ እውቀትና ሙያ ያለው መሆን እናዳለበት መሪ ጌታ ካሳ መንገሻና መሪ ጌታ መበጥን ገብሬ ይገልፃሉ፡ ፡ እነዚህን መስፈርቶች የማያሟላ ልጅም፣ ዘመድም ሆነ ባዳ ሙያውን እንደማይወርስ ጠቁመዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አንድ ተማሪ ሰውን ጉዳት ላይ ቢጥል ተማሪውም፣ አስተማሪውም ተወቃሾች መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ ለባህል ህክምና አዋቂው የሚከፈለው ክፍያ በመምህሩና በተማሪው ሁኔታና ቀረቤታ የሚወሰን መሆኑን ገልጸው፤ በአገልግሎት፣ በመጠነኛ የብር ክፍያ የሚፈጸም እንደሆነ አትተዋል፡፡ ደንቡንና ወራሹ ልጅና ዘመድ ቢሆንም እንኳ ለአባቱ እንደባህሉና ልማዱ አነስተኛ ክፍያ ይፈጽማል፡፡ ደንቡንና ስርዓቱን በማክበር ፍቃድ (እራሱን የቻለ፣ ኀበዝና ጠንቃቃ የሆነ እንደ ማለት ነው) ያገኛል፣ የሚቀምመው መድኃኒት ፍቱን እንዲሆንለት፤ እንዲሰምርለት ይመረቃል፡፡ ከዚህ በኋላ የህክምና አገልግሎቱን በይፍ መስጠት ይችላል፤ (ሚያዝያ 17 እና 20/2003 ዓ.ም)፡፡

[21] ቃል ኪዳን በባህል ህክምናው ዘርፍ ያለውን ምስጢር ለሌሎች አሳልፎ እንዳይሰጥ የሚገባው ቃመ መሃላ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእውቀቱና በሙያው የሰው ገንዘብ ያለአግባብ እንዳይበላበት፣ ሰውን እንዳያጠቃበትና እንዳያጠፋበት (ለተንኮል ተግባራት እንዳያውለው) በማሰብ የሚገባ መሆኑን ይገልፃሉ፤(መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው፣መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ፣ የባህል ሐኪም ታላእግዜር ይናዱ ሚያዝያ/2003 ዓ.ም)፡፡

በባለሙያዎቹ ሙያውን ተምሮ፣ አስፈላጊውን "አሬንሣ" (ክፍያ) ፈፅሞ እፅዋቱ ከየት ፣ እንዴት፣ መቼ እንደሚሰበሰቡ፤ የትኛው አካላቸው ለመድኃኒትነት እንደሚያገለግል፣ ለምን አይነት በሽታ እንደሚውል፣ በምን አይነት መለኪያ ተመጥነው እንደሚሰጡ እና የመሳሰሉትን ምስጢሮች ከባለሙያ ቀስሞ፤ ቃል ኪዳን (ቃለ መሃላ ፈፅሞ ) ገብቶ እንደሚሰጠው ይገልፃሉ።

በአጠቃላይ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊ መሆን እንዳለበት ይስማማሉ። የህክምን ጥበቡ ምስጢራዊ ካልሆነ መድኃኒቱ ይረክሳል፣ የመተዳደሪያ ምንጭ መሆኑ ይቀራል፣ እፅዋት ያለአግባብ ስለሚቀረጡ ይጠፋሉ፣ ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ ጉዳት ያደርሳሉ። ከባለሙያው ውጭ ከተሰጠ ከአመጣጠን ጋር በተያያዘ ግድፈት ይፈጠራል፤ ሙያው ዝቅተኛና ኋላ ቀር ተደርጎ ይቆጠራል። ስለዚህ በባለሙያ መሰጠቱ፤ የህክምና ባለሙያው በማህበረሰቡ ዘንድ ክብርን ያገኙበታል፤ መድኃኒት ተጠቃሚው ለመድኃኒቱ ዝቅተኛ አመለካከት እና ግምት እንዳይኖረው ያግዛል፤ የማህበረሰቡንም ጤንነት በማስጠበቅ ረገድ ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው ከመስክ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል።

እነዚህ የባህል የህክምና ባለሙያዎች ጥበቡን ለጤና ተቋማት እና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ማስፈተሽ፣ ማስተማርና ማስረዳት እንደሚችሉ በምእራፍ ሶስት ንዑስ ርእስ 3.1.8 ተጠቁሟል። ከመስክ የተገኘው መረጃም እንደሚያሳየው ባለሙያዎቹ መንግስታዊ በሆኑ ድርጅቶች፣ ጤና ኬላዎች የህክምና እውቀታቸውን በመግለጽ ማስተማርና ማስረዳት እንደሚችሉ፤ ከመንግስት ጤና ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለመስራት ፍቃደኛ እንደሆኑ በቡድን ውይይቱ ዕለት ጠቁመዋል፤ (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ የባህል ህክምና ባለሙያዎች የህክምና ጥበቡ በምስጢር ይያዝ ሲሉ፤ ሃላፊነት በማይሰማቸው ሰዎች እጅ ገብተው እንዳይረክሱና ጉዳት እንዳያደርሱ ከማለት እንጂ በድርጅት ለሚካሄድ ጥናት ይፋ ቢደረጉ ጉዳት እንደሌላቸው በቡድን ውይይቱ እለት አስረድተዋል። ሁሉም ተጠኚ አካላት ለሚመለከተው የጤና ዘርፍና ድርጅት የሙያ እውቀታቸውን ቀርበው ለማስረዳት ፍቃደኛ መሆናቸውን ከመስክ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

## 4.6 የባህል ሐኪሞች ከማኅበረሰቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት

በዚህ ንዑስ ርዕስ፤ የባህል ሐኪሞች ከባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች፣ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች እና እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ተቃኝቷል።

### 4.6.1 የባህል ሐኪሞች ከባህል መድኃኒት ተጠቃሚዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት

የባህል ሐኪሙና በባህላዊ ህክምና አገልግሎት ሁለት መሰረታዊ ነገሮች ይጠቀሳሉ። የባህል ሐኪሙና የታካሚው ግንኙነት። በእነዚህ ሁለት አካሎች መካከል የሚደረገው የህክምና አገልግሎት

የሁለቱንም የጋራ ስምምነትና ተግባቦት መሰረት ያደረገ ሁነት እንደሆነ ይታሰባል። በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከታካሚዎቻቸው ጋር ያላቸው ቀረቤታና ግንኙነት እንደሚከተለው ተቃኝቷል።

የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ ከታካሚዎቻቸው ጋር ያላቸውን ቀረቤታ ሲገልጹ፣ "ታካሚዎቼ ድነው፤ 'ምን እናድርግልህ፤ የሰው ህይወት በሺ ብር አይገዛ' እያሉ ያመሰግናሉ፤ ያዳንኳቸው ልጆች 'ጡት እናጣባህ ዝምድና እንፍጠር፣ ቤተሰብ እንሁን' የሚሉኝ አሉ። የኔ ዋጋና ፀጋ የነሱ መዳን ጤንነታቸው መመለሱ ይበቃኛል" በማለት በነ ፍቃዳቸውን ተቀብለው ከጎረቤትም ሆነ ከሩቅ አካባቢ ከሚመጡ ታካሚዎች ጋር የጠነከረ ግንኙነትና ወዳጅነት እንዳላቸው አጫውተውኛል። ማኅበረሰቡም በመልካም ስራቸውና አገልግሎታቸው እንደሚያከብራቸው፣ እስካሁን ድረስ በሰጡት ህክምና የተጎዳ ታካሚ እንደሌለ ጠቅሰው፤ "በምትኖርበት አገር ቂል [መጥፎና የሚያስወቅስ] ስራ አትስራ እንጅ መልካም ከሰራህ ትከበራለህ" በማለት ከታካሚዎች ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት ይገልፃሉ (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)።

በፅለተ ሐሙስ ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም በህክምና ቤታቸው ተገኝቼ ያነጋገርኳቸው ታካሚ[22] ወ/ሮ ታደለች አያሌው ስላገኙት ህክምና እንደገለጹልኝ ከሆነ፤ ለሁለት ሳምንት ያህል በጡት ካንሰር ሲሰቃዩ ቆይታው፤ ወደ ወረዳው ራቤል ጤና ጣቢያ በማምራት ሲታከሙ ቢቆዩም እየባሰባቸው እንደሄደ ያስረዳሉ። በዘመናዊው ህክምና እድናለሁ ብለው ሁለት መቶ ብር አውጥተው እንደነበርና ህመሙም እየባሰባቸውና የጤንነታቸው ሁኔታ እያሳሰባቸው ስለሄደ ወደ ባህላዊው ህክምና እንደሄዱ አስረድተዋል። በባህል ህክምናው ያገኙትን አገልግሎት በማመስገን "ይኸው ሰመዳን ችያለሁ! እርጥብ ልጅ [ከተወለዱ ወር እስከሚሞላቸው ድረስ እርጥብ (እንደተወለዱ ሰሞን)ና እራስ ልጅ በማለት ይጠራሉ] ይገኔ በጤና ጣቢያ ስዞር፤ እራሷንም ለማጥባት በቅቻለሁ ፈጣሪ ምስጋና ይግባዉና፤ የባህል ሐኪሞቼንም እጃቸውን ይባርክላቸው..." በማለት ይገልፃሉ። ለህክምናው ምንያህል እንደከፈሉ ስጠይቃቸው "በነፃ እንደማለት ነው፣ ከዛኛው [ከዘመናዊ ህክምና] ጋር ሲታይ የሚነገር አይደለም፣ አንተ ከፈለከው ሃያ አምስት ብር ነው፤ እሱንም ከዳንሽ በኋላ ተብዬ፤ እምቢ ብዬ ነው የሰጠሁት፤ ፈጣሪ ምስክሬ ነው፤ ከዚህም በላይ ብከፍል ደስባለኝ፤ ለሳቸው ነበር ሁለት መቶ መክፈል ያለበት..." በማለት አስረድተዋል።

ገብሬ በባህል ህክምና ዘርፍ የስልሳ አምስት አመቱ አዛውንት መሪ ጌታ መስፍን ከታካሚዎቻቸው ጋር ያላቸው ቀረቤታ የአባትና የልጅ ያህል መሆኑን ጠቁመው፤ "ህሙማን

---

[22] መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ፤ ታካሚዎቻቸው በብዛት የገጠር ኗሪዎች ሲሆኑ ከከተማ የሚመጡት ዘመናዊውን ህክምና ሞክረው ያልዳኑ ታካሚዎች እንደሆኑ ገልፀዋል ። ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ህሙማን የሚሄዱበት ሲያጡና የሚገቡበት ሲጨንቃቸው ደጃቸው መጥተው ሲወድቁ፤ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ረድተውና አስተናግደው እንደሚሸኙ ተናግረዋል (ሚያዝያ 17/2003 ዓ.ም)።

ወደኔ ሲመጡ ተሽቆጥቁጨ፦ እቀበላቸዋለሁ፦ እነሱም ተሽቆጥቁጠው ይቀበሉኛል" በማለት ይገልፃሉ። በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ቀረቤታ በህክምናው ዘርፍ ብቻ አለመሆኑን ጠቅሰው "የአገር አባትና አስታራቂም ያደርጉኛል"፣ በማለት ይናገራሉ። ከገቢ አንፃር፣ "በህክምና ሙያው ከማገኘው ጥቅም ይልቅ ለማህበረሰቡ የምሰጠው አገልግሎት ያረካኛል" በማለት ያስረዳሉ። ገንዘብ የሌላቸው ህሙማን ወደ ህክምና ቦታቸው ደርሰው አገልግሎት ሳያገኙ የተመለሱበት እለትና ወቅት እንደሌለ ያትታሉ። በዚህ ሙያ ዘመድና ቤተሰብ እንዳፈሩበት ከተሞክሯቸው በመነሳት ሲገልፁ "በአንድ ወቅት አንድ ልጅ በጠና ታማ አዳንኳት፣ ትዳር ይዛ ስምንት ልጅ ወለደች፣ የሁሉም የክርስትና አባት አድርጋኝ፣ ይኸው ቤተሰብ ሆነናል" በሚለት ከታካሚዎቻቸው ጋር ያላቸውን ቀረቤታ ያስረዳሉ ።

አንዳንድ ህሙማን ወደህክምና ቤታቸው መጥተው በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎቱን አግኝተው ሲመለሱ ከጠየቁት በላይ እንደሚከፍሏቸው ይገልፃሉ። በህክምናው ረክተው ሲድኑ የአቅማቸውን ያህል ተመጣጣኝ ዋጋ ከፍለው ይሄዳሉ እንጂ አስገድደው "ይህን ያህል ነው"፣ ብለው እንደማይወስኑ ያስረዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ በህክምና ዘመናቸው ከምስጋና በቀር፣ ጉዳት ደርሶባቸው የከሰሱም ሆነ የወቀሱ እንደሌሉ፣ እሳቸውም ተጨንቀውና ተጠበው ታካሚዎቻቸውን አክብረው እንደሚያስተናግዱ ያትታሉ።

የባህል ሐኪም ታለእግዚር ይናዱ ከታካሚዎቻቸው ጋር የአላቸውን ግንኙነት ሲያስረዱ፣ ህሙማን ወደ ህክምና ቦታቸው ከመጡ በኋላ "በሚገባቸው ቋንቋ ፣ በሚያስደስት ፈገግታ አቀበላቸዋለሁ" በማለት ገልፀዋል። በተለይ ስብራትና ውልቃት የደረሰባቸውን ታካሚዎች "በማሳሳቅ፣ አይምሯቸውን ዘና በማድረግ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚድኑ በመግለጽ ተስፋ በመስጠት፣ ሙሉ ፈገግታ በመለገስ" እንደሚንከባከቧቸው አትተዋል። "እግዚአብሔር እውቀቱን በመስጠት፣ ስጦታውን አውቄ በማገልገሌ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። የሚሰጡኝ ጤና ምጽዋቱን ልጉሙን ተቀብለው እንደሚመርቁኝ አረዱኝ" ብለዋል። [...] ስጦታውን ... "በማለት የሚሰጡት ህክምና ስጥቶኛል፣ ይባርክልኝ እያልኩ ስለምሰራቸው ስራዎች እፀልያለሁ" በማለት የሚሰጡት ህክምና ፈውስን እንዲያስገኝላቸው በማሰብ በእግዚአብሔር ስም እንደሚሰጡ ገልፀዋል ።

አቅምና ጉልበት የሌላቸው አዛውንቶች፣ ወደ ህክምና ጣቢያቸው ከመጡ በነፃ አክመው ምርቃታቸውን ተቀብለው እንደሚሸኟቸው አስረድተዋል። በህክምና አገልግሎት ዘመናቸው በተለየ ሁኔታ የሚያስታውሱትን ታሪክ እንደሚከተለው ገልፀዋል።

> በወረዳችን አንድ የእንስሳት ዶክተር ነበር። ሞተር ሲያሽከረክር ወደቀና ቀኝ እጁ ውልቅም አለ፣ ስብርም አለ። ትውልዱ አዲስ አበባ ነው። በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ሂድ ብለውት አልሄድም ብሎ፣ በእኔ ችሎታና እውቀት ተማምኖ፣ እዚሁ ህክምናውን ተከታትሎ፣ በአራት ወር ውስጥ ዳነ፣ እኔ ይሄን ያህል ስጠኝ ሳላልኩትም በራሱ ፍቃድ ስድስት መቶ ብር ሰጥቶኛል፤(ሚያዝያ 25/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ በሚሰጡት የህክምና አገልግሎት በብዛት የገጠር ኗሪዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን አትተው ከአጎራባች ወረዳዎች "አንፃኪያ፣ ከደጋጋና፣ ከመንዝ" ድረስ የሚመጡ ታካሚዎች እንዳሉ አስረድተዋል፤(ሚያዝያ25/2003 ዓ.ም)።

መሪጌታ ሐይሉ ፍሰሃ፣ በባህላዊ ህክምና የሚሰጠው አገልግሎት እንደ አካሚው ጥረትና ታካሚው ቀረቤታ የሚሰጥ መሆኑን ያስረዳሉ።

> ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጠንክሮ መስራት ያስመሰግናል፤ እንደዚህ አይነት ጎበዝ ሰው አለ እየተባባሉ ይመጣሉ። ስራህ በማኅበረሰቡ ይታወቃል፣ ትከበራለህ፣ አንዱ ታክሞ ሲሄድ ሁለት ሶስት ይጠቁማል፤ እኔም በጥንቃቄ እሰራለሁ፣ ታካሚዎቼን እንከባከባለሁ" በማለት አስረድተዋል። ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት የተሰጡትን ስጦታ በማስታወስ የነበረውን ሁኔታ ሲገልጹ፤አቶ አማረ ሃይሌ ይባላል። ሚስቱ ጡት ላይ ነቀርሳ ወጥቶባት፤ በዘመናዊ ህክምና ሳይሻላት ይቀራል። ሰውነቷ ይበላሻል፤ ይሂት ሲመጣ ፣ እንደማትድን ተስፋ ቆርጦ ነበር፤ ሚስቱን አዳንኩለት እንዲህ ሆናማ ከዳነች ብሎ፤ ተደስቶ አንዲት ጊደር ሰጥቶኛል፤በማለት ገልጸዋል (ሚያዝያ 27/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከታካሚዎች ጋር መልካም ቀረቤታና ግንኙነት ያላቸው መሆኑን በጥናቱ ሂደት ለማወቅ ተችሏል። የሚሰጡትም የህክምና አገልግሎት ከማህበረሰቡ ክብሬታንና እድናቆትን እንዳስገኘላቸው ገልጸዋል። ታካሚዎቻቸውም ከከተማው ማኅበረሰቡ ይልቅ የገጠሩ ኗሪ እንደሚበዛ ጠቀመው፤ አብዛኛዎቹ ከከተማ የሚመጡ ታካሚዎች ዘመናዊውን ህክምና ሞክረው አልድን ሲላቸው ወደ ባህል ህክምና እንደሚመጡ ከባህል ሐኪሞቹ ለመረዳት ተችሏል።

### 4.6.2 የባህል ሐኪሞች ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት

የባህል ሐኪሞች ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተጨማሪ ሕዝብና የመረጃ አቀባዮቼንና ሁለት የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችን በማወያየት ያላቸው ቀረቤታ እንደሚከተለው ተቃኝቷል።

መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው፤ አድማሱ ከሚባ የዘመናዊ ህክምና ባለሙያ ጋር ቀረቤታ እንዳላቸው ገልፀው፤ ቁስል ነክ በሽታዎችን አክመው ካልተሳካላቸው ወደ እሳቸው እንሚልኳቸው አስረድተዋል። ነገር ግን በመንግስት ወይም ከወረዳው ጤና ጣቢያ ጋር ምንም አይነት ግንኙነትና ቀረቤታ እንደሌላቸው ተናግረዋል። ላለመገናኘታቸው ዋናው ምክንያት በሁለቱ ባለሙያዎች መካከል መናናቅ ያለ መሆኑን ገልጸዋል።

> በሁለታችን መካከል መናናቅ አለ፣ እኛም እነሱን እነሱም እኛን ይንቃሉ፣ በየራሳችን ተገናኝተን ምስጢር አንገላለጥም፤ በተለይ አንዳንድ የዘመናዊ ሐኪሞች ባህላዊውን ኋላ ቀር አድርገው የሚመለከቱ አሉ። ሁላችንም በያለንበት ውስጥ ውስጡን በሙያችን እንተዋወቃለን፣ እንደምናድን ያውቃሉ፣ ባህል እንደሚሰራ ያምናሉ፣ ይፋ የማያወጡት የነሱ ህክምና እንዳይናቅባቸው ሊሆን ይችላል፤(ሚያዝያ 18/2003 ዓ.ም)።



መሪ ጌታ(የኔታ) ጌታቸር ሽዋንግዛው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

ከዚህ በላይ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያስረዳው፡ የባህል ሐኪሞች ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር መልካም ቀረቤታ የላቸውም፡፡ የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር በግለሰብ ደረጃ መልካም ቀረቤታ እንዳላቸው አጫውተውኛል፡፡

> ከዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለኝ፡፡ በጤና ጣቢያ በኩል የተሰጠኝ ስልጠና የለም፡፡ ነገር ግን በግለሰብ ደረጃ ስለሰው ልጅ አጥንት ሁኔታ ውይይት በማቅረብ ሰዓት ይቀበሉኛል፤ ገለፃም ይሰጡኛል፡፡ ከነሱ የቀሰምኩትን ተግባር ላይ ሳውለው እውቀት አገኝበታለሁ፡፡ ለወረዳው ከዘመናዊ ህክምና ስልጠና ይሰጠኝ ብዬ ደብዳቤ አስገብቻለሁ፡፡ እስካሁን ምላሽ አላገኘሁም እንጂ፤ በማለት ገልፀዋል (ሚያዝያ 25/2003 ዓ.ም

እኚህ የባህል ሐኪም ከዘመናዊው ህክምና ባለሙያዎች ጋር ቀረቤታ ቢኖቸውም፤ የባህልና የዘመናዊ መድኃኒት ውጤቶችን በማቀላቀል ህክምና እንደማይሰጡ አስረድተውኛል፡፡ ከዘመናዊው ህክምና መድኃኒቶችን ሳይሆን ቁሳቁሶችን በመጠቀም ባህላዊውን ህክምና አደራጅተው፣ ቁሳቁሶቹን ገዝተው ህክምና እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ የደም ግፊት መለኪያ መሳሪያ እስቴትስኮፕ፣ ጓንት፣ ፋሻ፣ የተለያዩ የመቀስ አይነቶችና አልኮሆል በመግዛት የህክምና አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን አትተዋል፡፡ እኔም በህክምና መስጫ ቦታቸው በመገኘት የመሳሪያዎቹን አይነትና ብዛት ለማየት ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም ባህላዊውን መድኃኒት ቀምመው የሚያስቀምጡባቸውና የሚሰጡባቸው ቁሳቁስና አንዳንድ መድኃኒቶችንም በጠብታ መልክ ማዘጋጀትን ከዘመናዊው ህክምና ልምድ በመውሰድ እንደሚጠቀሙ አጫውተውኛል፤ ለምሳሌ፡- ለጆሮ ህክምና የሚሰጥ ጠብታ ከእፀዋት ቀምመው በጠብታ መልክ እንደሚያዘጋጁ አስረድተዋል (ሚያዚያ 25/2003 ዓ.ም)፡፡

በባህል ሐኪም ታለእግዜር የተገለጸውን ሐሳብ በሚያጠናክር መልኩ በዘመናዊ ህክምና የራቤል ጤና ጣቢያ የጤና መኮንን የሆኑት ሐኪም ዘላለም ግርማ፤ በሁለቱ መካከል ያለውን ወቅታዊ ሁኔታና ቀረቤታ ሲገልጹ፤ "እንደተቋም ቀረቤታ የለንም፣ በግለሰብ ደረጃ ግን ከአንዳንድ የባህል ሐኪም ቀረቤታ አለኝ" በማለት ገልጸዋል፡፡ የወረዳው ጤና ጣቢያ ከባሕል ሕክምና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ባያደረግም አብዛኞቹ የባህል ሐኪሞች የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችን

እንደማይቀበሉ አስረድተዋል። በተጨማሪ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጣቸው ግምታዊ እንጂ ጥናትን መሰረት ያላደረገ መሆኑን አስረድተዋል። በባህል ህክምና ጉዳት ደርሶባቸው በጤና ጣቢያው የታከሙ ህሙማን እንደነበሩ አስረድተዋል። በዚህ ጉዳይ ያስታወሱትን እንደሚከተለው አጫውተውኛል።

> አንድ ልጅ የቆዳ ቁስል እግሩ ላይ ወጣቸበት። በየቀኑ ስትበላው ስትበላው እያከካት እየሰፋች መጣች። በባህላዊ ህክምና የሚቀባ ነገር ተሰጥቶት አራት ወር ሙሉ ሳይድንለት ይቆያል። እኛ ጋር ሲመጣ ጉዳቱ እስከ ሶስተኛው የቆዳ ክፍል ዘልቆ ነበር። ቁስሉ እየተጠና አይነቱ ተለይቶ በመርፌ ኤሌክትሮኒክስ ድራግ እየተሰጠው የዳነበት ሁኔታ አስታውሳለሁ፤ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

እንደ ጤና መኮንንኑ ገለጻ የባህል ሐኪሞች ባልተመረመረና ባልተረጋገጠ መድኃኒት የሚሰጡት አገልግሎት ህብረተሰቡን እየጎዳው ነው። በተለይ የምርመራ ዘዴያቸው ኋላ ቀርነት፣ የመድኃኒት ቅመማቸው፣ አሰጣጣቸውና የመጠን መለኪያቸው ግምታዊ በመሆኑ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው እንደሚያመዝን ይገልፃሉ። በዓመት በባህል ህክምና ጉዳት ደርሶባቸው የመጡ ታካሚዎች ብዛት ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለህልፈተ ሕይወት የተዳረጉ ታካሚዎች ሲያስረዱ "የጉዳቱ መጠን ይለያይ እንጂ በዓመት ቢያንስ ከአምስት ያላነሱ ይመጣሉ። ለሕልፈተ ሕይወት የተጋለጡ ታካሚዎች አሉ;ጋጠሙ'ንም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ ደግሞ ከመሪጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ጋር የተቀራረበ ሃሳብ ሰጥተዋል። የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች የባህል መድኃኒቶችን እንደሚንቁ፣ ተቀራርበውና ተወያይተው እንደማያውቁ ያስረዳሉ። በጤና ጣቢያው ባሉ የተሰጠ ስልጠና እንደሌለ ጠቁመው "እንዲያውም ቤት በሬት ከጎጂ ልማድ ቆጥረውን ነበር" በማለት ገልጸዋል። ለዚህ ክፍተት ትልቁ ምክንያት ተቀራርበው አለመነጋገራቸው እና ሙያውን በሞግተው መያዛቸው ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አስረድተዋል (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)።

የቡድን መሪ የሆኑት የቡድን መሪ የሆኑት በዘመናዊ ህክምና ዘርፍ በእናቶች ማዋለድና የሕፃናት ጤና እንክብካቤ የቡድን መሪ የሆኑት ሐኪም ማሞ ተስፋዬ ከባህል ሐኪሞች ጋር ያለውን ግንኙነት በሁለት መልኩ ያዩታል። አንደኛ የባህል ሐኪሞችን በተመለከተ በወረዳው ጤና ጣቢያ የተሰራ ስራና የተሰጠ ስልጠና እንደሌለ፤ ሁለተኛ ግንኙነታቸው በተቋማት ደረጃ ሳይሆን በግለሰብ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን አጫውተውኛል። እሳቸውም ከተወሰኑ የባህል ሐኪሞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የባህል ሐኪሞች በሚሰጡት ህክምና ዙሪያ የበኩላቸውን ልምድ እንደሚያካፍሏቸው አስረድተውኛል።

አንድም የባሕል ህክምና ባለሙያዎችን የቀረቤታቸውንም ሁኔታ በሁለት መልኩ ይገልጹታል። አንድም የባሕል ህክምና ባለሙያዎችን ብንርቃቸው ማህበረሰቡ በብዛት የሚጠቀምባቸው በመሆኑ ጉዳት እንዳይደርስ ከማለት፣ ሌላው ደግሞ በባህል ህክምናው የሚሰጠው አገልግሎት ምን እንደሚመስል በሂደት ለመቃኘት እንደሆነ

ነግረውኛል። ምናልባት እነዚህ የባህል ሐኪሞች ቢደራጁ ፍቀድ ቢሰጣቸው ጥሩ እንደነበረ ገልጸው፤ እነዚህን የህክምና ባለሙያዎች አደራጅቶ መስመር የሚያሲዝ አካል እስካልተፈጠረ ድረስ የችግሩ ሁኔታ ቀጣይ እንደሚሆን አትተዋል። "የህክምና ዘርፉ በአንዳንድ ነገሮች ውጤታማ መሆኑ ባያጠራጥርም ሁሉም በየቤቱ እንደ ፈቀደ የሚሰጠው ህክምና መሆኑ" ተገቢ እንዳልሆነ አስረድተዋል፤ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር ያላቸውን ቀረቤታ አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ይህን ጉዳይ በሁለት መልክ ለማየት ይቻላል። ይኸውም አንደኛ በወረዳው ጤና ተቋማት የሙያም ሆነ፣ የውይይት መድረክ ተከፍቶ ያልተወያዩና ያልተዋወቁ መሆናቸው ሲሆን በሌላ በኩል የተወሰኑ የባህል ሐኪሞች በግለሰብ ደረጃ ከዘመናዊ ሐኪሞች ጋር በመገናኘት ውይይትና ምክክር እንደሚያካሂዱ ለመገንዘብ ተችሏል። የተወሰኑ የባህል ሐኪሞች ደግሞ ከዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ከመሆኑም ባሻገር ዘመናዊ ሐኪሞችን በአይነ ቁራኛ እንደሚያዩዋቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል። የባህል ሐኪሞቹ ሙያ በዘመናዊዎቹ እምብዛም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ሲገልጹ የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ደግሞ የባህል ባለሙያዎች ያላቸውን እውቀት ለማካፈል ፍቃደኞች አለመሆናቸውን ያትታሉ።

### 4.6.3 የባህል ሐኪሞች የእርስ በርስ ግንኙነት

በባህላዊ ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት እንደሌላቸው መሪ ጌታ ሃይሉ ፍስሃ ይገልጻሉ። በአጠቃላይ ግንኙነት የለም ማለት እንደማይቻል አስረድተዋል። ለዚህ ዋናው ምክንያት በሙያው "እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ" የሚል የውድድር መንፈስ ስላለ፤ አንዱ ከአንዱ በአንድ ነገሩ በልጦ እንዲታወቅ" ከመፈለግ አንጻር እንደሆነ ይጠቅሳሉ። በሁለተኛ ደረጃ ከገቢ ምንጭ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እውቀቱን አሳልፈው ቢሰጡ የገቢ ምንጭ ያጥራል በሚል ፍራቻ እንደማይነጋገሩ አስረድተዋል። በመካከላቸው የውድድር መንፈስ መኖሩን በበጎ መልኩ ያዩታል። ምክንያቱም በሁለቱ መካከል የውድድር መንፈስ ካለ አንዱ አንዱን ለመብለጥ ሲወዳደሩ ስራቸው በጥራት የሚታይ መሆኑን ያትታሉ። ከዚህ ውጣ ባለ መልኩ ደግሞ፤ "ሙያው በልፋትና በጥረት የሚመጣ ነው፤ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ብዙ ጥረትና መስዋዕትነት ይጠይቃል። ቃል ኪዳን አለው፣ ደጅ ተጠንቶ፣ እግር አጥቦ እና አገልግሎ የሚገኝ እውቀት ነው" በማለት ያስረዳሉ። ብዙ ውጣ ውረድ ተለፍቶበት የሚገኝ ሙያ እንደሆነና በዚህ ምክንያት እንደማይቀራረቡ አስገንዝበዋል፤ (ሚያዝያ 27/2003 ዓ.ም)።

መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ተቀራርበው የሰሩበትም ሆነ የተወያዩበት አጋጣሚ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ሁለቱም ሙያተኞች የየራሳቸውን እውቀት ስለሚያጋንኑ ቅርርብ አለመኖሩን ያትታሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም በተንኮል፣ በክፋትና በአይነ ቁራኛ ስለሚተያዩ የህክምና ሙያው እንደተዳከመ ይናገራሉ፡፡ ተባብረው ቢሰሩ፣ አንዱ የሚያውቀውን ለአንዱ በቅንነት ቢያሳውቅና ቢያስረዳ ለማኅበረሰቡም ሆነ ለባህል ሐኪሙ እንደሚጠቅም ያስረዳሉ (ሚያዚያ 20/2003 ዓ.ም)፡፡

የባህል ሐኪሞች የርስ በርስ ግንኙነት አለመኖር ዋናው ምክንያት እውቀታቸውን በቅንነት ያለማካፈላቸው እንደሆነ በባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ ተጠቁሟል፡፡ አንዳንድ ጉዳዮችን ለመመካከር እንኳ ካስፈለገ የልብ ጓደኛ የሚሉትን፣ይነግረኛል ብለው የሚያምኑትን ሰው እንጂ ሌላ ባለሙያ በማወያየት መረጃ እንደማይቀበሉና እንደማይሰጡ አጫውተውኛል (ሚያዚያ 25/2003 ዓ.ም)፡፡

የባህል ሐኪሞች የማይገናኙበት ዋናው ምክንያት "አንዱ የሰጠውን መድኃኒት አንዱ 'አይሰራም፣ አይረባም' ስለሚለው መወቃቀስና መተዛዘብ ይመጣል" ከሚል ፍራቻ ቀርበው እንደማይወያዩ መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው ተናግረዋል፡፡ ሌላው ምስጢር የማይገላለጽቡት ምክንያት ከአባቶች የተወረሰው ባህልና እምነት መወያየትንና ምስጢር ማውጣትን የማይፈቅድ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ መሰረቱ መድኃኒቶቹ ገሃድ ከወጡ ይረክሳሉ፣ የፈዋሽነት ኃይላቸውን ያጣሉ የሚል እምነት ነው፡፡ በነዚህ አበይት ምክንያቶች የባህል ህክምና ባለሙያዎች ግንኙነት እንደሌላቸው አትተዋል (ሚያዝያ 18/2003 ዓ.ም)፡፡

መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ የባህላዊ መድኃኒት አዋቂዎችን ግንኙነት አስመልክቶ ሲገልጹ "ጌታችንን የሰቀሉት የተማሩ ናቸው፡፡ ቤተ ክህነት ሲባል ምቀኛ ነው፡፡ የአንዱን ምስጢር ለአንዱ ለመግለጽ " እኔ ደስተኛ አይደሉም" በማለት ያስረዳሉ፡፡ የራሳቸውን የሕይወት ልምድና ተሞክሮ በመጥቀስ " እኔ ደስተኛ አይደለሁም" በማለት ያስረዳሉ፡፡

ሰሜን ሸዋ ነው ያለሁት፤ የግድ ጎንደር ወይም ጎጃም ሄጄ ተምሬ መምጣት አለብኝ፣ ከሌላ ቦታ ያለው ደግሞ እዚህ መጥቶ መልመድ አለበት" እዚህ ያለው የባህል ሐኪም እውቀቱን ለሌሎች የአካባቢ ሰዎች ቢያካፍል የህክምና ገቢው ይቀንሳል በሚል ፍራቻ እንደማይቀራረቡ አስረድተዋል (ሚያዝያ 17/2003 ዓ.ም)፡፡

በአጠቃላይ በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ሙያዊ ውይይትና ቀረቤታ እንደሌላቸው፣ ምስጢር እንደማይገላለጹ፣ እንደማይተማመኑ፣ በመካከላቸው የትብብርና በጋራ የመስራት መንፈስ እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለዚህ ዋናው ምክንያት በባህል ሐኪሞች መካከል የውድድር መንፈስ ፣ የገቢ ምንጭ በመሆኑ፣ በባለሙያዎች መካከል የእውቀትና የሙያ ክፍተት መኖሩ፣ አንድ ሞያተኛ በአንደኛው ስራ አለመተማመኑ፣ ለግንኙነታቸው አሉታዊ አመለካከት

እንዲኖር ምክንያት መሆኑ ይጠቁማሉ፡፡ ይህን ልምድና ተሞክሮ በመቅረፍ ሙያዊ ክህሎታቸውን በውይይትና በምክክር ቢያሳድጉ፣ የህክምና ልምድና እውቀታቸውን ቢያዳብሩ፣ ለማኅበረሰቡ ጥሩ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ይገመታል፡፡

## 4.7 የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብ ለባህል ሐኪሞች ያላቸው አመለካከት

የግሼ ወረዳ ማኅበረሰብ ለባህላዊ የህክምና ባለሙያዎች ያላቸውን አመለካከት ለመቃኘት ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን፣ ታካሚዎችንና የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችን በማነጋገር ቅኝታዊ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡

መሪ ጌታ ጌታቸር ሸዋንግዛው አሁን ያለው ማኅበረሰብ ለባህል ህክምና ቀና አመለካከት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ በፊት በነበረው መንግስት የባህል ሐኪም እየተባሉ ችግር የደረሰባቸውን ሰዎች እያስታወሱ በዚህ ሙያ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ለእስራትና እንግልት ተዳርገው እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ "አሁን ያለው ማኅበረሰብ አምኖብን ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ ባህላዊውን አዘውትሮ ይጠቀማል" በማለት ያስረዳሉ (ሚያዝያ 18/2003 ዓ.ም)፡፡

በራቤል ጤና ጣቢያ የጤና መኮንን የሆኑት ሐኪም ዘላለም ግርማ የአካባቢው ማኅበረሰብ የባህል ህክምናን በብዛት እንደሚመርጥ ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ ለዘመናዊ ህክምና ያለው ግንዛቤ እና አመለካከት አናሳ መሆን አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ ሌላው በሚኖሩበት አካባቢ የባህል ህክምና መገኘቱ፣ በቀላል ወጪ ህክምናው መሰጠቱ፣ በተደጋጋሚ በሽታዎችን ሲያድን ማየታቸው፤ "ለምሳሌ እንደ ወፍ፣ ኪንታሮት፣ ችፌ፣ ቋቁቻና የቆዳ ላይ ቁስሎችን በተመለከተ ከዘመናዊ ይልቅ ባህላዊውን ምርጫቸው እንሚያደርጉ" አትተዋል፡፡ እነዚህን በሽታዎች "በዘመናዊ ህክምና ማዳን ቢቻልም አብዛኛው በገጠር የሚኖረው ማህበረሰብ እምብዛም ግንዛቤው ላይኖረው ይችላል" የሚል ሃሳብ እንዳላቸው ገልጸውልኛል፡፡ በባህል ህክምናው ዘርፍ የሚሰጠው አገልግሎት ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ፣ በሽታን የመለያ ዘዴዎች ልማድን የተከተሉ በመሆናቸው የሚሰጠው ህክምና አግባብነት አለው ብሎ ለመወሰን እንደሚያዳግት አስረድተዋል (ሚያዚያ 21/2003 ዓ.ም)፡፡

ሌላው በመሪ ጌታ ኃይሉ ፍስሃ የህክምና መስጫ ቤት ያነጋገርኳቸው አቶ ሞገስ አብይ ለባህላዊ ህክምና አዎንታዊ አስተያየት እንዳላቸው ገልጸውልኛል፡፡ አቶ ሞገስ አብይ የአርባ ሶስት ዓመት ጎልማሳ ናቸው፡፡ በሚጥል በሽታ ከተለከፉ ሰባት አመት አልፏቸዋል፡፡ በነዚህ አመታት ዘመናዊ ህክምና ሞክረው ከህመማቸው እንዳልተፈወሱ ገልጸዋል፡፡ በአንጻሩ ወደ ባህል ህክምናው በመሄድ "መድኃኒት አገኘሁ ይኸው የሚጠጣና በአፍንጫ የሚሸተት መድኃኒት እየወሰድኩ ለውጥ አግኝቻለሁ፡፡ አሁን አርባ ቀን ሞላኝ የባህል ህክምና ጥሩ ነው፡፡ መድኃኒት ነው" በማለት

ያስረዳሉ፡፡ በዘመናዊ ህክምና እንደተንገላቱ ገልጸው፤ የባህል ህክምናው ፈውስ ስለሰጣቸው ሐኪሙን በማመስገን በህክምናቸው እንደረኩ አስረድተዋል (ሚያዝያ 27/2003 ዓ.ም)፡፡

የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ በባህል ህክምናው ዘርፍ በማኅበረሰቡ ተቀባይነትና እውቅና ያላቸው መሆኑን ይገልጻሉ፡ አሁን የባህል ሐኪም መባል ክብር እንደሆነ፣ ማኅበረሰቡም እንደሚያበረታታቸው ያስረዳሉ፡፡ ድሮ ተብታቢ፣ ስር በጣሽ፣ መተተኛ እና የመሳሰሉትን ስያሜዎች ሲሰጡ እንደነበር አስታውሰው አሁን ከዘመናዊ ህክምና ጎን እንደሚታዩ አስረድተዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በእጃቸው እየዳሰሱ፣ በአይናቸው እያዩ፣ በሽታዎችን የሚለዩ በመሆናቸው ማኅበረሰቡም በቂ ግንዛቤ እያገኘ መምጣቱና በግልጽ የባህል ህክምናን መጠቀሙ ዘርፉን ተመራጭ እንዳደረገው ይናገራሉ፤ (ሚያዝያ 25/2003 ዓ.ም)፡፡

ቁልፍ የመረጃ አቀባይ የሆኑት መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ የአርባ ዓመት ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ የግሼ ወረዳ ማህበረሰብ ለባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ያላቸውን አመለካከት ከኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት እስከ አለንበት መንግስት[23] (ኢ.ፌ.ድ.ሪ) ድረስ ያለውን ሁኔታ አስረድተዋል፡፡ በፊት የነበረው ማኅበረሰብ ከባእድ አምልኮ ጋር እያጣመረ ይጠራቸው እንደነበር በማስታወስ አሁን ያለው ትውልድ ወደ ባህል ህክምና በግልጽ የመሄድና የመጠቀም ልማድ እንዳለው አትተዋል፡፡ በዚህ ዘመነ መንግስት አገልግሎቱን በስፋት እየሰጡ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በመስክ ስምሪቴ ወቅት ከመሪ ጌታ መስፍን ገብሬ የህክምና አገልግሎት ያገኙ ታካሚ ለበሽታቸው አይነትና ስላገኙት የህክምና አገልግሎት አጫውተውኛል፡፡ ታካሚ አቶ በየነ ተገኝ የሃምሳ ሶስት ዓመት ጎልማሳ ናቸው፡፡ በፊንጢጣቸው የኪንታሮት በሽታ ወጥቶባቸው ሲሰቃዩ እንደነበር፤ የህመሙ አይነት እንደማይሻላቸው ሲረዱ ወደ መሪጌታ መስፍን ገብሬ በመሄድ የህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን አስረድተውኛል፡፡ "ዘመናዊ ህክምና ኪንታሮትን አያድንም

---

[23] በኃይለስላሴ ዘመን ህክምናውን ጀምሬዋለሁ፡፡ በደርግ ዘመን በባህል ህክምና ከፍተኛ ጉዳትና እንግልት ደርሶብኛል፡፡ መጽሐፎች ተሰብስበው እንዲቃጠሉ፣የባህል ህክምና እናውቃለን የሚሉ እንዲታሰሩ ፣ጎጂ ልማድ ህዝብን ያለአግባብ የሚበዘብዙ ተብሎ በዚያ ጭፍጨፋ አብሬ ተደገፍ ነበር፡፡ መጽሐፎቹ እንዲቃጠሉና ወደ ውሃ እንዲጣሉ ተደርገዋል፡፡ ቅጠል በጣሾች፣ ስር መዛገሮች፣ ሕዝቡን አቆርቁዘዋል ተብሎ መመሪያ መጣ፡፡ በዚህ ግዜ ወደመነከሙ እና እውቀትን ወደ መደበቁ ተደረሰ፡፡ እስከአሁን ያደረሱኒቸው መጽሐፎች በመሬት ውስጥና በዋሻ ውስጥ ቀብሬ በማስቀመጥ፤ ላቆያቸው ችያለሁ፡፡ ይኸው አሁን ለክብርና ለደረጃ በቅተዋል፡፡ ያን ግፍና መከራ ተቀብለን አሁን እውቀቱን በአደባባይ እየተጠቀምንበት ነው፡፡ በደርግ የህክምና ቤቱን እንድዘጋ ያለኝን እውቀት እንድደብቅ ተገድጃለሁ፡፡ ማህበረሰቡ ደግሞ በድብቅ ጨሊማ ለብሶ፣ "መድኃኒት ስጠን" ሲሉኝ ችግር ነውና በድብቅ እሰጣቸው ነበር፡፡ አሁን ግን የሁላችንም መብት ተጠብቆ በሙያችን እንድናገለግል መደረጉ ጥሩ ነው ፡፡ በፊት የባህል ህክምና ሲባል ከጠንቋዮች፣ ከባለዛሮች… ጋር በመደባለቅ ያዩን ነበር፡፡ አሁን ያለው ህብረተሰብ ወደ ባህል ህክምና በይፋ የመሄድ ጤንነቱን በግልጽ የማስረዳት ልማድ አለው፤ በማለት ገልጸዋል (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)፡፡

የሚባል ነገር ስለምሰማ" በማለት ወደ ዘመናዊ ህክምና ጣቢያ አለመሄዳቸውን ጠቁመው፤ ለህመማቸው መፍትሄ የሆናል ወዳሉት የባህል ህክምና አገልግሎት እንደሄዱ ይናገራሉ። አሁን ከህመማቸው እየተፈወሱ በመሆናቸው "እግዚያብሔርን አመስግኘዋለሁ በቅርቡ በመታከሜ" ይላሉ። ከዚህ በተጨማሪ በዝቅተኛ ወጪና በቅርቡ መታከማቸውን፣ በትራንስፖርት አለመንገላታታቸውን እየጠቀሱ የባህል ህክምና ፈዋሽ መሆኑን ያስረዳሉ፤ (ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ በግሼ ወረዳ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ለባህል ህክምና ባለሙያዎች አዎንታዊ ምላሽ እንዳላቸው ከባህል ሐኪሞች እና ከታካሚዎች ለመገንዘብ ተችሏል። በፊት ማኅበረሰቡ ለባህል ህክምና ባለሙያዎች እንደ ጠንቋይ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ስርማሽ፣ አስማተኛ የሚሉ የተለያዩ ስያሜዎችን ይሰጥ እንደነበር መረዳት ይቻላል። በአሁኑ ሰዓት ማኅበረሰቡ ለሚያጋጥመው የጤና ችግር ባህላዊው ህክምናን በግልጽ ሄዶ እንደሚጠቀም ከአውራና ከንዑስ መረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ተችሏል።

የዘመናዊ ህክምና ባለሙያና የጤና መኮንን የሆኑት ሐኪም ዘላለም ግርማ እና ሐኪም ማሞ ተስፋዬ፤ የህክምና ዘርፉ በማኅበረሰቡ የተመረጠ ቢሆንም የሚሰጠው አገልግሎት የተመጠነ፣ የተመረመረ እና የተረጋገጠ ነው ማለት እንደማይቻል አስገንዝበዋል። ከዚህ አንጻር ማኅበረሰቡ ለባህል ሐኪሞች ያለው አመለካከት ቀና መሆኑን የባህል ሐኪሞችና ታካሚዎች የገለጹ ሲሆን የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ደግሞ የህክምና ዘርፉ እስካልተፈተሸ እና እስካልተረጋገጠ ድረስ ተገቢ ነው ማለት እንደማይቻል አስገንዝበዋል፡

## 4.8 በግሼ ወረዳ ጎልተው የሚታዩ የበሽታ ዓይነቶች

በግሼ ወረዳ ጎልተው የሚታዩ የበሽታ ዓይነቶችን ለማጤን በዘመናዊና በባህላዊ ህክምና የሚሰጠውን አገልግሎት በመቃኘት፣ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዘመናዊ ህክምና ጎልተው የሚታዩ በሽታዎችን ለማወቅ በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት የተዘጋጁ መረጃዎችን በመፈተሽ በ2001 እና በ2002 ዓ.ም ጎልተው የታዩ በሽታዎችን መረጃ ለማቀናበር ተችሏል። የሌላቸው በአንጻሩ በባህላዊ ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች የተጠናከረና የተደራጀ መረጃ የሌላቸው በመሆኑ ጎልተው የሚታዩ በሽታዎችን ለማወቅ የሰነድ ምርመራ አልተደረገም። ስለዚህ ጉዳይ እንደ መፍትሔ የተወሰደው የባህል ህክምና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ የሚፈውሷቸውን በሽታዎች በቅደም ተከተል ከአንድ እስከ አስር እንዲጠቅሱ በማድረግ፤ በዘርፉ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ተችሏል። ይህም በመሆኑ አውራና ንዑስ መረጃ ሰጭ የሆኑ የባህል

ህክምና ባሙያዎችን መረጃ መሰረት በማድረግ በግሼ ወረዳ ጎልተው የሚታዩ በሽታዎችን ከአንድ እስከ አስር ዝርዝራቸውን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተችሏል።

የግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት በ2001 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም[24] በወረዳው ጎልተው የሚታዩ አስራ አራት ዋና ዋና የበሽታ አይነቶችን መረጃ ዝርዝር አስቀምጧል (በአባሪ-6 የቀረበውን መረጃ ልብ ይሏል)። በነዚህ ተከታታይ ሁለት አመታት አስር ዋና ዋና በሽታዎችን (Top Ten Disease) ዝርዝር በመውሰድ በወረዳው ጎልተው የታዩ በሽታዎች ተጠቁመዋል።

በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት በ2001 ዓ.ም ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶች በቅደም ተከተል ስናይ፤ "ተለይቶ ያልታወቀ ትኩሳ፣ አሜባ፣ የላይኛው መተንፈሻ አካል ለሽታ፣ ቁርጥማት፣ የጨጓራ ህመም፣ የቆዳ ላይ ቁስል፣ በአደጋ የደረሰ ጉዳ፣ ቶንሲል፣ ሌሎች የመተንፈሻ አካላትና የሆድ ውስጥ ትላትል" የሚሉት ናቸው፤(በአባሪ-6 የቀረበውን መረጃ ልብ ይሏል)። ይህ አሃዝና የበሽታ ዝርዝር በ2002 ዓ.ም መጠነኛ የደረጃ ለውጥ በማሳየት ከዚህ በፊት የተገለጹ በሽታዎች በድጋሚ ቀርበዋል። እነርሱም፤ "ተለይቶ ያልታወቀ ትኩሳት፣ የላይኛው የመተንፈሻ አካል በሽታ፣ የጨጓራ ህመም፣ ሌሎች የሆድ ትላትሎች፣ ቁርጥማት፣ አሜባ፣ የአይን ህመም፣ የሳንባ ምች፣ የጥርስና የድድ ህመምና የቆዳ ቁስል" የሚሉት ከአንድ እስከ አስር ያለውን ቦታ በቅደም ተከተል ይዘዋል።

በነዚህ ሁለት ዓመታት የተከሰቱ በሽታዎችን በንጽጽር ስናይ፤ ቀድሞ የነበረ ደረጃቸውን ሳይለቁ ባሉበት ሁኔታ የቀጠሉ በሽታዎች አሉ። ለምሳሌ፤ ተለይቶ ያልታወቀ ትኩሳት በሁለቱም ተከታታይ አመታት የአንደኛነት ደረጃ በመያዝ ይመራል። ሌሎቹ ደግሞ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ በፊት ከነበሩበት ደረጃ ከፍና ዝቅ ያሉ የበሽታ አይነቶች አሉ። ለዓብነት ያህል፤ የአሜባ በሽታ በ2001 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃነት በመያዝ ዋና የበሽታ አይነት ሆኖ ተመዝግቧል። ይህ በሽታ በ2002 ዓ.ም የስድስተኛ ደረጃን በመያዝ የበሽታው ስርጭትና ጉዳት ከበፊቱ እየቀነሰ መምጣቱን መረጃው ይጠቁማል።

በአንጻሩ ደግሞ በ2001 ዓ.ም ዝቅተኛ ደረጃ የነበራቸው በሽታዎች በ2002 ዓ.ም ከፍተኛ ደረጃን በመያዝ የበሽታዎቹ ስርጭት እንደጨመረ ለመገንዘብ ተችሏል። ለምሳሌ በ2001 ዓ.ም የሆድ ጥገኛ ትላትሎች አስረኛ ደረጃን የያዙ ሲሆኑ በ2002 ዓ.ም የአራተኛን ደረጃን በመያዝ ከበፊቱ የበለጠ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል። በሌላ የበሽታ ስርጭትና ስፋት በበለጠ ሁኔታ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ዓመት ተከስቶ የነበረ በሽታ በሌላኛው አመት ያልታየበት አጋጣሚና

[24] በግሼ ወረዳ በአምስት አመት ውስጥ ጎልተው የታዩ በሽታዎችን ለመቃኘት ጥረት ቢደረግም የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ከሁለት ዓመት ውጭ የተጠናከረ መረጃ እንደሌለው እና የተወሰኑ ጤና ኬላዎች በቅርቡ የተከፈቱ በመሆኑ የአምስት አመት ዝርዝር እንደሌለ አቶ ተከላ ደበበ ገልጸዋል፤ (ሚያዚያ 12/2003ዓ.ም)።

ሁኔታ እንዳ ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት የወጣው መረጃ ያስረዳል፡፡ ለአብነት ያህል፤ በ2002 ዓ.ም የሳንባ ምች የስምንተኛነት ደረጃ በመያዝ የተጠቀሰ በሽታ ሲሆን በ2001 ዓ.ም በሽታው አልተከሰተም፤ ቢከሰትም እንኳ ዋና ዋና ከተባሉት የበሽታ ዝርዝሮች ውስጥ አልተካተተም፡፡

በአጠቃላይ የግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት በ2001 እና በ2002ዓ.ም ያወጣውን መረጃ መሰረት በማድረግ ጎልተው የታዩ በሽታዎችን ሁኔታና ደረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በነዚህ ሁለት አመታት የተከሰቱ በሽታዎችን ደረጃ ስናጤን የተወሰኑ በሽታዎች ባሉበት ደረጃ የቀጠሉበት ግሚሶቹ ደግሞ ከደረጃቸው ከፍና ዝቅ በማለት ለውጥ ያሳዩበት፣ ቀሪዎቹ ደግሞ በፊት ተከስተው በሁለተኛው አመት ያልተከሰቱ ወይም ቢከሰቱም ጎልተው የታዩ በሽታዎች እንዳልሆኑ ከቀረበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከዚህ በፊት እንደተገለጸው፤ በባህላዊ ህክምና ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ ዓይነቶችን ለመጠቆም የባህል ሐኪሞቹን ምላሽ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በ2003 ዓ.ም በግሼ ወረዳ በባላዊ ህክምና ዘርፍ ጎልተው የታዩ በሽታዎች ለማት ባያስደፍርም አጠቃላይ መረጃን ከመጠቆም አንፃር ጉልህ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ በዘርፉ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት የባህል ሐኪሞች የሰጡትን ወቅታዊና ግላዊ ምላሽ እንደመፍትሔ በመውሰድ የበሽታዎችን ደረጃ በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡ ለዚህም በሁሉም የባህል ህክምና ባለሙያዎች የተመረጡ የበሽታ ዝርዝር በመውሰድ በባህል ህክምናው ጎልተው የሚታዩ በሽታዎችን ለመጠቆም ተሞክሯል ፡፡

በግሼ ወረዳ በሚገኙ የባህል ሐኪሞች የቀረበውን መረጃ (በአባሪ-5 የቀረበውን መረጃ ልብ ይሏል) መሰረት በማድረግ፤ ከአስራ አንዱ የባህል ሐኪሞች ውስጥ፤ የወፍ በሽታ(ስምንት)፣ የኮሶ በሽታ (ሰባት)፣ የጭረት በሽታን (አምስት)፣ የእንጥል መውረድ (አምስት)፣ የስኳር በሽታን (አምስት)፣ አልማዝ ባለጭራ (አራት)፣የእብድ ውሻ በሽታን (አራት)፣ ነቀርሳ(ሶስት)፣ የጨጓራ በሽታን (ሶስት) እና የሚጥል በሽታን(ሶስት) መርጠዋል፡፡ ከዚህ መረጃ በመነሳት አስር የበሽታ አይነቶችን ለመጠቆም ተችሏል፡፡ የተወሰኑ በሽታዎቸ ተመሳሳይ አሃዝ ያላቸው ቢሆንም በዚያው ይዘታቸው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ከዚህ መረጃ በመነሳት የወፍ (የጉበት)[25]፣ የኮሶ፣ የጭርት፣

[25] እንደ አካባቢው ማኅበረሰብ ገለፃ፤ **ወፍ (ጉበት)** ለሚባለው በሽታ መንሥኤ የሌሊት ወፍ እንደሆነች ከቡድን ተወያዮች አውራ የመረጃ አቀባይ የሆኑት የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ ያስረዳሉ፡፡ የበሽታውን መነሻ መንስኤ እና ሂደቱን ሲያስረዱ፤ የሌሊት ወፎች በመኖሪያ ቤት ውስጥ ገብተው ሲበሩ በመመገቢያ ገበታችን፣ በመጠጫ እቃዎቻችን፣ በመተኛና በመቀመጫ ቦታዎቻችን ላይ ሽንታቸውን ረጭተው ይሄዳሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ምግብ ስንበላ፣ ውሃ ስንጠጣ፣ የሽንብትን (የረጩበትን) ቁሳቁስ በእጃችን ነክተን ወይም ከምግብ እና ከመጠጥ ጋር ወደ ሆዳችን ሲገባ የወፍ በሽታ እንደሚይዝ አስረድተዋል (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)፡፡

የእንጥል መውረድ፣ የስኳር፣ የአልማዝ ባለጭራ፣ የእብድ ውሻ በሽታ፣ ነቀርሳ፣ ጨጓራና የሚጥል በሽታ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ማለት ይቻላል።

በጥናቱ ታላሚ በሆኑ የባህል ሐኪሞች የተገኘውን መረጃ ከዘመናዊ ህክምና ጎልተው ከታዩ በሽታዎች ጋር ለማነጻጸር ተሞክሯል። ይህ ንጽጽር ተጨባጭ መረጃዎችን ባያመለክትም፤ የተገኙት መረጃዎች ሲመሳከሩ እንደሚጠቁሙት ከሆነ በባህላዊ ህክምና በዋናነት የተጠቆሙ በሽታዎች በዘመናዊ ህክምና ውስጥ አልተጠቀሱም። በአንጻሩ ደግሞ በዘመናዊ ህክምና ጎልተው የታዩና የተመዘገቡ በሽታዎች በባህላዊ ህክምና አልተጠቆሙም ።

ስለዚህ ከነዚህ መረጃዎች ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ሆኗል። አንድም ማኅበረሰቡ በዘመናዊና በባህላዊ ህክምና የሚፈወሱ በሽታዎች ለይቶ አውቆ ይሆን? ለምን ለተወሰኑ በሽታዎች ከዘመናዊ ህክምና ይልቅ ባህላዊውን ምርጫቸው አደረጉ የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል። ለነዚህ ጥያቄዎች ከመስክ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክቱት ከሆነ ማኅበረተሰቡ ለቁስል ነክ፣ ለኪንታሮት፣ ለወፍ፣ ለሆድ ውስጥ ጥገኛ ትላትል፣ ለእብድ ውሻ በሽታ፣ ለሚጥልና ለልክፍት በሽታዎች ከዘመናዊ ይልቅ ባህላዊውን እንደሚመርጡ የዘመናዊ ህክምና ባለሙያ የሆኑት ሐኪም ማሞ ተስፋዬ እና የጤና መኮንን ሐኪም ዘላለም ግርማ ይጠቁማሉ (ሚያዝያ 21/2003 ዓ.ም)።

ከአውራ የመረጃ አቀባዮቼ እና ከታላሚ ቡድናዊ ውይይት የተገኘው መረጃም እንደሚጠቁመው ከሆነ ማኅበረሰቡ፤ ለወፍ፣ ለተለያዩ የሰውነት ቁስሎች፣ ለሚጥል በሽታ፣ ለሞኝ ባገኝ፣ ለእንጥልና ለኪንታሮት በሽታዎች ከዘመናዊ ይልቅ ባህላዊ ህክምና ምርጫቸው እንደሆነ አስረድተዋል (ሚያዝያ 29/2003 ዓ.ም)።

በአጠቃለይ ከነዚህ መረጃዎችና ጥቆማዎች በመነሳት፤ ማኅበረሰቡ ለተወሰኑ በሽታዎች ባህላዊ ህክምናን ምርጫው ያደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። በዘመናዊ ህክምና ዋና ዋና ተብለው የተመዘገቡ በሽታዎች፣ በባህላዊው ጎልተው ያልታዩ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ በባህላዊ ጉልተው የታዩ በሽታዎች በዘመናዊ ህክምና አልተመዘገቡም። ከዚህ አንጻር በግሼ ወረዳ በባህላዊና በዘመናዊ ህክምና ጎልተው የሚታዩ የበሽታ አይነቶች ልዩነት እንዳላቸው ከመረጃዎቹ ለማረጋገጥ ተችሏል።

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ" በሚል ርዕስ ላይ ያተኮረ ሲሆን ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በግሼ ወረዳ ከሚኖሩ አውራና ንዑስ መረጃ ሰጭዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በታላሚ የቡድን ውይይት ዘዴ ተሰብስበዋል። መረጃዎቹም ትንታኔ ተደርጎባቸዋል። በትንታኔው መሰረት ከሚከተሉት የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ለመድረስ ተችሏል።

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች የበሽታን ምልክትና ፀባይ ለመለየት የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ። በአብዛኛው የባህል ሐኪሞቹ እይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባዮሎጅካዊ እና የህሙማንን ማኅበራዊ ሁኔታ በመቃኘት በሽታዎቹን በመለየት ህክምና እንደሚሰጡ ጥናቱ አሳይቷል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ህክምና ባለሙያዎች እይታዊ የምርመራ ዘዴን በመጠቀም፤ በሰውነት ውጫዊ አካል ላይ የሚወጡ ቁስሎችን፤ በአክታ፣ በዓይነ ምድርና በፈሳሽ መልክ የሚወገዱ ቆሻሻዎችን በማየት... በሽታን ለመለየት ጥረት ያደርጋሉ። በክሊኒካዊ ምርመራ ደግሞ የሰውነት ትኩሳትን፣ የአጥንት መሰንጠቅን፣ የጅማት መሸማቀቅን፣ የልብ ምትን እና የግንባር ስሮችን... በመዳበስ በሽታን ይለያሉ። በባዮሎጅካዊ ምርመራ ዘዴ፤ ከሰውነት የሚወገዱ ቆሻሻዎችን በተለያዩ ሙከራዎች በመፈተን፣ የህመምተኛውን ስስ ብልትና የነርቭ መገኛ ቦታዎችን በመፈተሽ፣ የህመሙን ስሜትና ምልክት በማጤን የበሽታውን አይነት እንደሚለዩ ለመገንዘብ ተችሏል። ከነዚህ የምርመራ ዘዴዎች በተጨማሪ የህመምተኛውን ማኅበራዊ ሁኔታ (የስራ ዓይነት፣ የቤተሰብ ግንኙነት፣ የገቢ ምንጭ...) ጠይቀው በመረዳትና በማወያየት የበሽታን መንስኤ ና ምክንያት ለመለየት ሙከራ እንደሚያደርጉ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን ከአቅማቸው በላይ ከሆነ ወደ ዘመናዊ ህክምና እንደሚልኩ ጥናቱ አረጋግጧል። በባህል ህክምና ተግባራዊ ከሚሆኑ የምርመራ ዘዴዎች መካከል እይታዊ ምርመራ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚሸፍን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

በዘመናዊ ህክምና ዘርፍ የተሰማሩ ሐኪሞች በባህላዊ ህክምና በሽታን ለመለየትና ለመመርመር የሚካሄደውን ተግባር አጥብቀው ይቃወማሉ። ባህላዊ ሐኪሞቹ የተለያዩ የውስጥና የውጭ ደዌ በሽታዎችን ባህሪ፣ ምልክት እና ዓይነት በውል መለየትና መፈረጅ እንደማይችሉ፣ "በይሆናል" በሽታን እንደሚለዩ፣ ከዘመናዊው የህክምና ምርመራ ስርዓት ጋር በማይገናኝ መንገድ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል። በተለምዶ በወረሱት ዘዴ በማከማቸውም ጉዳት እንደሚያደርሱ ጠቁመዋል። በዚህም በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች ውጤታማነትን አስመልክቶ ሁለት አመለካከቶች መኖራቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች ለመድኃኒት መቀመሚያ የሚውሉ ግብዓቶችን ከእፅዋት፣ ከእንስሳት፣ ከማዕድናትና ከነፍሳት ውጤቶች የሚያገኙ ሲሆን ከመጠንና ከዓይነት አንፃር ሲታይ ከእፀዋት የሚቀመሙ መድኃኒቶች ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ለመለየት ተችሏል። ሐኪሞቹ ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀ መድኃኒቶችን ከግቢያቸው፣ ከመስኖ ማሳቸውና ከዱር የሚሰበስቡ ሲሆን እነዚህን ግብዓቶች ከጳጉሜ እስከ ህዳር ባሉት ወራት በብዛት ተሰብስበው ለቅመማ ይውላሉ። በነዚህ ወራት የመሰብሰባቸው ምክንያት እፀዋት በብዛት የሚገኙበት፣ የሚያብቡበት፣ የሚያሸቱበት፣ የሚያፈሩበት ... ወራት በመሆናቸው፤ በጣም ለጋ (ጮርቃ) ሳይሆኑ ወይም ሳይደርቁ (ሳይገነትሩ) እና ወዘናቸውን ሳያጡ በአፍላ ጊዜያቸው ለመሰብሰብ የታለመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በግሼ ወረዳ የሚኖሩ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ እፀዋት ሲሰበስቡ የተለያየ ልማዳዊ ሥርዓተ ገቢር ይፈጽማሉ። ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት ሲቆረጡ በዋናነት "እፅ አንግስ" የሚባለውን የእፀ ደብዳቤ ጸሎት በግዕዝ ሰባት ጊዜ በመድገም የሚፈጸም ሥርዓት-ገቢር እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህ የባህል ሐኪሞች የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ ለመድኃኒት ቅመማ የሚውሉ እፀዋትን ሲሰበስቡ፤ ከመድገሚያ ቦታ የማይነቃነቅ ጥቁር ድንጋይን፤ ከቀናት ማክሰኞ፣ ረቡዕና ዓርብን፤ ከመቆፈሪያና መቁረጫ መሳሪያ፤ የጌሾና የወይራ አንካሴ፣ ሁለት ሰይፍ ያለው የቀንድ ካራና የወይራ ዛቢያን እንደሚመርጡ ታውቋል። መድኃኒቶችን ለመሰለቅና ለማዋሃድ፤ መዳመጫና አለሎ፣ ወፍ ያልቀመሰው ውሃን ይመርጣሉ። ለመድኃኒት መለኪያ (ከቁሳቁስ ውጭ) እና ማጠጫ ቦታ ደግሞ በአዕቅ እና በጋት (የእጅ ትንሿ ጣት እና መዳፍ) በመለካት፣ ሙቀጫና ወፍጮ ላይ በማስቀመጥ እንደሚያጠጡ ለመገንዘብ የተቻለ ቢሆንም ይህን ለተወሰኑ በሽታዎች ካልሆነ በስተቀር አዘውትረው እንደማይተገብሩት ለመረዳት ተችሏል። ለመድኃኒት መውሰጃ፤ የእማምሳይ ላም (እናትና ልጅ በመልክ ከሚመሳሰሉ) ቅቤ እና ማር (የንብና የጣዝማ) በዋናነት ተመራጭ ናቸው። እነዚህ ለመድኃኒት መሰብበቢያና መስጫ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችንና ቀናት የራሳቸው የሆነ ትዕምርታዊ ፋይዳና ትርጓሜ እንዳላቸው ጥናቱ አመልክቷል።

የባህል ህክምና ባለሙያዎች ያዘጋጇቸውን መድኃኒቶች ለህሙማን ሲሰጡ የህመምተኛውን አቋም፤ የመድኃኒቱን እና የበሽታውን አይነት በማጤን፤ በማንኪያ፣ በእፊያ (በሃይላንድ ክዳን)፣ በስኒ (በፍንጃል)፣ በብርጭቆና በመሳሰሉት ለክተው እንደሚሰጡ በመስክ ጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል። ለህመምተኛ የሚሰጠው መድኃኒት በስንት ሠዓት እንደሚወሰድ፣ ከምግብ ምን መበላት እንዳለበትና እንደሌለበት፣ ከምን ከምን ነገሮች መቆጠብ (ከግብረስጋ ግንኙነት፣ ከአልኮል፣ ከዶሮ)፤ የተሰጠው መድኃኒት የሚጎዳውና የሚያዳክመው ከሆነ ማርከሻው ምን እንደሆነ በዝርዝር በማስረዳት ያዘጋጁትን መድኃኒት እንደሚሰጡ በጥናቱ ተጠቁሟል። ከዚህ

ጋር በተያያዘ የአካባቢው ማኅበረሰብ የባህል ህክምና አገልግሎትን በስፋት የሚጠቀም ሲሆን አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት አርሶ አደሮች፤ ዘመናዊ ህክምና ሞክረው ፈውስ ያላገኙ የከተማ ኗሪዎች መሆናቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡

በዘመናዊ ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች በአካባቢው ለሚተገበረው የባህል ህክምና ከመድኃኒት ምጣኔና አሰጣጥ ሥርዓት፣ ግብዓት፣ መቀመሚያና መስጫ ቁሳቁስ ንፅህና ጋር በተያያዘ በዘርፍ የሚሰጠውን አገልግሎት አጥብቀው እንደሚተቹ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለዚህም ዐበይት ምክንያታቸው፤ የባህል ሐኪሞች የሚሰጡት መድኃኒት መጠኑ ያልታወቀ፣ የመፈወስ ኃይሉና ደረጃው በቤተ-ሙከራ ያልተረጋገጠ፣ ለመድኃኒት የሚውሉ ግብዓቶች በውል ያልተለዩ መሆናቸው፣ የሚቀምሙባቸውና የሚሰጡባቸው ቁሰሳቁሶች ንፅህና የጎደላቸው እንደሆኑ፤ ከጥንቃቄና ከአሰጣጥ ግድፈት በህሙማን ላይ ጉዳት እንደሚያደርሱ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ደብተራዎች፣ መሪጌታዎች፣ ቄሶችና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ የባህል ሐኪሞች ሲሆኑ የባህል ህክምና ጥበቡን የተማሩት ከሃይማኖት ተቋማት (ከአብነት ትምህርት ቤት)፣ ከቤተሰብ በልምድ፣ የባህል መድኃኒት የሚያውቁ የአብነት መምህራንን በመቅረብና በማገልገል፣ ሙያው ካላቸው የባህል ሐኪሞች መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ ከመድኃኒት አውደ ጥበቦች፣...የህክምና ጥበቡን እንደተማሩት በጥናቱ ተገልጿል፡፡ ለባህል ህክምና መነሻና መተላለፊያ የሃይማኖት ተቋማት (የአብነት ትምህርት ቤት) ጉልህ ሚና እንዳላቸው ጥናቱ አትቷል፡፡

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በጥናቱ ታላሚ ማኅበረሰብ ውስጥ እንደወንዶቹ እራሳቸውን ችለው በባህል ህክምና የተሰማሩ ሴቶች አለመኖራቸውን በዚህ ጥናት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሴቶች በባህል ህክምና ያለመሳተፋቸው ምክንያት፤ የህክምና ዘርፉ ብርቱ ጥረትን፣ ክትትልንና ጥንቃቄን የሚሻ መሆኑ፣ ከቤተሰብ ኃላፊነት፣ ልጅ ከማሳደግ፣ በአብነት ትምህርት ቤት እንደወንዶቹ ካለመማር፣ ከአቅም ማነስ፣ ከአበው በመጣ ልምድ፣ እምነትና ሥርዓት "ሴትን ልጅ ማስተማር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል" ተብሎ መታሰቡና አባቶች ለሴት ልጆቻቸው ሙያውን አለማውረሳቸው ምክንያት እንደሆኑ ጥናቱ ገልጿል፡፡

ከመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በግሼ ወረዳ የሚካሄደው የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊ ካልሆነ ጥበቅና ምስጢራዊ እንደሆነ በጥናቱ ተብራርቷል፡፡ ለዚህም የህክምና ጥበቡ ምስጢራዊ ካልሆነ መድኃኒቱ ይረክሳል ተብሎ መታሰቡ፣ የመተዳደሪያ ምንጭ መሆኑ፣ እፅዋት ያለአግባብ እንዳይቆረጡ፣ ለእኩይ ተግባራት እንዳይውሉ፣ ከአያያዝና ከአሰጣጥ ግድፈት ጉዳት እንዳያደርሱ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ክብር ለማድኘት፣ ህሙማን ሙያው ዝቅተኛና ኋላ ቀር ተደርጎ እንዳይታሰብ፣ ለመድኃኒቱ ዝቅተኛ አመለካከት እና ግምት እንዳይኖራቸውያ የሚሉት ዐበይት ምክንያት መሆናቸው በጥናቱ ውጤት ታይቷል፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ ማኅበረሰብ አካባቢ የሚገኙ የባህል ሐኪሞች እርስ በርሳቸውም ሆነ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር ያላቸው ቀረቤታና ግንኙነት የጠነከረ አለመሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ለእርስ በርስ ግንኙነት መሻከር ዋናው ምክንያት የመቀናናት፣ የመናናቅ፣ የውድድር መንፈስና ያለመተማመን መኖር፤ በባለሙያዎች መካከል የእውቀትና የሙያ ክፍተት ያለመሆኑ ለግንኙነታቸው አሉታዊ አመለካከት እንዲኖር ምክንያት መሆናቸው ታይቷል፡፡ ከዘመናዊ ሐኪሞች ጋር ያለመገናኘታቸው ምክንያቱ የህክምና ጥበቡ ኋላቀርና ዝቅተኛ ተደርጎ ይታሰባል መባሉ፣ በወረዳው ጤና አስተዳደር የውይይት፣ የምክክርና የስልጠና መድረክ አለመሰጠቱ፣ ሙያችንን በዘመናዊ ሐኪሞች እንነጠቃለን ተብሎ መታሰቡ የሚሉት ተጠቃሽ ምክንያት እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ የባህል ሐኪሞች ከታካሚዎች ጋር መልካም ቀረቤታና ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሚሰጡትም የህክምና አገልግሎት ከማኅበረሰቡ ከበሬታንና አድናቆትን እንዳስገኘላቸው በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡

በግሼ ወረዳ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ለባህል ህክምና ባለሙያዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ከባህል ሐኪሞች እና ከታካሚዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በፊት ለባህል ህክምና ባለሙያዎች እንደ ጠንቋይ፣ ቅጠል በጣሽ፣ ስርማሽ፣ አስማተኛ የሚሉ የተለያዩ ስያሜዎችን ይሰጡ እንደነበር ተገልጿል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ማኅበረሰቡ ለሚያጋጥሙት የጤና እክሎች ባህላዊው ህክምናን በግልጽ ሄዶ እንደሚጠቀም በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ደግሞ የባህል ህክምና ዘርፉ በማኅበረሰቡ የተመረጠ ቢሆንም የሚሰጠው አገልግሎት የተመጠነ፣ የተመረመረ እና የተረጋገጠ ነው ማለት እንደማይቻል አስገንዝበዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በማኅበረሰቡና በባህል ሐኪሞች የህክምና ዘርፉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን በዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ደግሞ ተቀባይነት እንደሌለው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በግሼ ወረዳ በባህላዊ ህክምና ጎልተው የሚታዩና የሚፈወሱ በሽታዎች የወፍ (የጉበት)፣ የሆድ ውስጥ ጥገኛ ትላትል፣ የጭርት፣ የእንጥልና የቶንሲል፣ የስኳር፣ የአልማዝ ባለጭራ፣ የእብድ ውሻ በሽታ፣ የነቀርሳ፣ የጨጓራ፣ የኪንታሮት፣ የቋቁቻ፣ የሚጥል በሽታ መሆናቸው ታይቷል፡፡ አብዛኞቹ የባህል ሐኪሞች ከእምነት ተቋም የወጡ መሆናቸው፣ ለህሙማን ስነልቡናዊ ድጋፍ ማድረጋቸው፤ በዝቅተኛና በመጠነኛ ክፍያ የህክምና አገልግሎት መስጠታቸው፤ ከማኅበረሰቡ ሃይማኖት፣ እምነት፣ ባህልና ልማድን የፈለቁ መሆናቸው እና ህሙማን በህክምናው እንፈወሳለን የሚል ጥብቅ እምነት መያዛቸው የህክምና ዘርፉን ተመራጭና ተፈላጊ እንዳደረገው የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡

## የተጠቀሱ ጽሑፋዊ ምንጮች


ሐዲስ ገብረመስቀል፤ *መጽሐፈ መድኃኒት* ፣ አዲስ አበባ፣......፣ሚያዚያ 3፣ 1998 ዓ.ም።

መሪራስ አማን በላይ፤ *መጽሐፈ ፈውስ-መዝገበ ጥበብ ወፈለገ ጠቢብ ዘስርወ ዕፅዋት*፣ አዲስ አበባ፣------፣2000 ዓ.ም።

መስፍን ፍቃዱ፤ "የሃገረሰባዊ መድኃኒቶች ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002 ዓ.ም።

ምህረት ዳኘው፤ "በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድኃኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ሰብስቤ ደምሰው (አርታኢ)፤ *ዕፀ ደብዳቤ* ፣ በገላሁን አባተ የተዘጋጀ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1987 ዓ.ም።

ተክለፃድቅ መኩሪያ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*፣ 5ኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1965 ዓ.ም።

________፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣የመጀመሪያ እትም 5ኛ መጽሐፍ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1936 ዓ.ም።

ቴቶ ላጺሳ እና ሌሎችም፤ *የአማርኛ የሕክምና መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ መ.ት.መ.ማ.ማ. ድርጅት ታተመ፣ 1978 ዓ.ም።

አለማየሁ ዘሪሁን፤ "የኑዌር ማኅበረሰብ የባህል ህክምና እውቀት አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም።

አብደላ ሙሃመድ አሊ፤ *ተአምራዊ ፈውስ*፣ አዲስ አበባ፣ ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ ድርጅት፣ 1996 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፤ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ*፣አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል፤ *የመዓዛማ እና መድኃኒት ዕፅዋት ጠቀሜታ*፣ ሻሸመኔ፣ ኤ. ዋይ. ማተሚያ ቤት፣ 2003 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም::

የግሼና አካባቢው ተወላጆች ማኅበር፤ <u>የግሼ መነፅር</u>፣ መፅሔት፣ቅፅ1፣ቁጥር.1፣........... ::

የግሼ ወረዳ ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት በየስድስት ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት፤ <u>ነፀብራቅ</u> ፣ 2ኛ ዓመት ቅ.2፣ ቁ.3፣ ነሐሴ፣ 2002 ዓ.ም::

የግሼ ወረዳ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳይ ጽህፈት ቤት የ2003ዓ.ም ከግማሽ ዓመት ሪፖርት ተሻሽሎ የተወሰደ (ያልታተመ)::

የግሼ ወረዳ ግብርና እና ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት የ2003 ዓ.ም ከግማሽ ዓመት ሪፖርት ተሻሽሎ የተወሰደ (ያልታተመ)::

የግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት የ2003 ዓ.ም ከግማሽ ዓመት ሪፖርት ተሻሽሎ የተወሰደ (ያልታተመ) ::

ደስታ ተክለወልድ፤ <u>ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም::

ጳውሎስ ኞኞ፤ <u>ዳግማዊ አጤ ምኒልክ</u>፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም::

ፈቃደ አዘዘ፤ "የመስክ ስራ ስነቃል አሰባሰብ፣ አከለሳሰፍ፣ አተናተን እና አሰናነድ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ለባህልና የባህል አመራር ለልማት፣ ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ" የቀረበ ጽሑፍ ሚያዚያ 3-5፣ 1999 ዓ.ም (ያልታተመ)::

___________ ፤ <u>የስነቃል መምሪያ</u>፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም::

Abraraw Tesfaye. "Traditional Medicine in an Urban Center, Belief and Practices (The Case of Dessie Town, N. Ethiopia)" M.A Thesis, Department of Social Anthropology; Addis Ababa University, 1993.

Ademuwagun, Z.A, and et al (eds). <u>African Therapeutic Systems</u>. Waltham: Crossroads Press, 1979.

Agonafir.E. "Vision and Mission of Traditional Health Practitioners in Ethiopia." In Urga. K, Assefa. A, and Guta. M, (eds). <u>Traditional Medicine in Ethiopia</u>. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, (2004):PP. 48-51.

Alemayehu Moges. "Traditional Ethiopian Medicines." Institute of Ethiopian Studies; Eight International Conferences of Ethiopian Studies: Addis Ababa University, 1984.

Assefa Balcha. "Traditional Medicine in Wollo Nature and history." M.A Thesis, Department of History: Addis Ababa University, 1992.

Baquar, S. "The Role of Traditional medicine in a Rural Environment". In Isaac Sindiga, and et al (ed). Traditional Medicine in Africa. Nairobi; East African Educational Publishers Ltd, (1995).PP.134-152.

Chavunduka, Gordon. Traditional medicine in modern Zimbabwe. Zimbabwe: University of Zimbabwe Publications, 1994.

Dawit Abebe (ed). Development and Utilization of Herbal Remedies in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, 1996.

______. "The Role of Medicinal Plants in Health Care Coverage of Ethiopia: The Possible Benefits of Integration" In Medhin Zewdu and Abebe Demissie (eds). Conservation and Sustainable Use of Medicinal Plants in Ethiopia . Institute of Biodiversity Conservation and Research. Addis Ababa May, (2001): PP.6-19.

Dawit Abebe and Ahadu Ayehu. Medical Plants and Enigmatic Health Practices of Northern Ethiopia. Addis Ababa: Berhanenna Selam Printing press,1993.

Desta B. "Review of Traditional Medicine Research in Ethiopia" Proceedings of a National Workshop: Addis Ababa, 30 June-2July, 2004.

Fekadu Fullas. Ethiopian Traditional Medicine: Common Medicinal Plants in Perspective. Sioux City Lowa: St. Luke's Regional Medical Center, 2001.

Goldstein, Kenneth. A Guide For Field Workers in Folklore. USA: Folklore Association Inc, 1964.

Good, Charles. Ethno-Medical System in Africa: Patterns of Traditional Medicine in Rural and Urban Kenya. New York: The Guilford Press, 1987.

Gumede, M.V. Traditional Healers: A Medical Practitioner's Perspective. Jahannesbarg: Skotaville Publisher, 1990.

Hufford, J. David. "Folk Healers" In Richard Dorson M (ed). Handbook of American Folklore. India: Indian University Press, (1986): P306-313.

Hurreize, Sayyid. Studies in African Applied Folklore. Khartoum: The Occasions of African Universities Congress, 2006.

Kannon, B. "Integration of Traditional Medicine with Modern Medicine." In Urga. K, Assefa. A, and Guta. M (eds). Traditional Medicine in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, (2004): PP.32-38.

Kokawaro, J.O. Medicinal Plants of East Africa. Kampala: General Printers Ltd, 1976.

Konadu, Kwasi. Indigenous Medicine and Knowledge in African Society. New York and London: Taylore and Francis Group PLC, 2007.

Medhin Zewdu and Abebe Demissie (eds). Conservation and Sustainable use of Medicinal Plants in Ethiopia. Institute of Biodiversity Conservation and Research: Addis Ababa May, 2001.

Mekonen Meressa. "Indigenous Medicine, Beliefs and Practices Among The Kunama In Sheraro, Tigray" M.A. Thesis; Department of Ethiopian Study: A.A.U, 2010.

Mekonen Workineh. "The Attitude of Traditional Practitioners, Biomedical Workers and the Public to Wards Traditional Medicines with Particular Reference to Rabies Healers in West Gojjam." MA Thesis, Department of Ethiopian Studies: A.A.U, 2008.

Mekkonen Bishaw. "Integrating Indigenous and Cosmopolitan Medicine in Ethiopia." PhD dissertation; Southern Illinois University: Carbondale, USA, 1988.

Mesfin Kassaye. "Integration of Traditional Medicine with Modern Care Services." In Dawit Abebe (ed). Development and Utilization of Herbal Remedies in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research institute: Addis Ababa, (1996):PP.10-14.

Messeret Shiferaw. "The Role of Health Professionals in the development of Traditional Medicine in Ethiopia." In Dawit Abebe (ed). Development and Utilization of Herbal Remedies in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, (1996): PP. 15-19.

Mirgissa Kaba. "Indigenous Medical Beliefs and Practices Among the Oromo of Illubabor" M.A Thesis, Department of Social Anthropology: A.A.U, 1993.

Molvaer, Reidulf. Medical Anthropology: Topics of Relevance for Health Workers and Students of Health in Ethiopia. Addis Ababa: UNICEF/Ministry of Health in Ethiopia, 1987.

Murdock, George Peter. Theories of Illness: A World Survey. Pittsburgh; University of Pittsburgh Press, 1980.

Pankhurst, Richard. "An Historical Examination of Traditional Ethiopian Medicine and Surgery." Ethiopian Medical Journal 3, (1965): PP.157-172.

_________. An Introduction to the Medical History of Ethiopia. With a postscript by Asrat W. Trenton: The Red Sea Press Inc, 1990.

_________. "Historical Reflection of Traditional Ethiopian Pharmacopeia." Ethiopian Pharmacy Journals, 2(1976):PP.29-32.

_________. "The Characteristics of Traditional Ethipian Medicine and its Traditional Pharmacopeia." In Urga. K, Assefa. A, and Guta M (eds). Traditional Medicine in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, (2004): PP.26-29.

Press, Irwin. "Urban Folk Medicine: A Functional Overview." American Anthropologist; Blackwell Publishing on Behalf of the American Anthropological Association: New Series, Vol. 80, No1 (Mar, 1978):PP. 71-84. Available in:http://www.jstor.org/stable/673512. Accessed: 05/03/2011 18:25

Read, Margaret. Culture, Health, and Disease. London: Lavistock Publications Limited, 1966.

Richter, Marlise. Traditional Medicines and Traditional Healers in South Africa. Discussion Paper Prepared for the Treatment Action Campaign and AIDS Law Project: South Africa, 27 Nov, 2003.

Sindiga, Isaac and et al (ed). Traditional Medicine in Africa. Nairobi; East African Educational Publishers Ltd, 1995.

Sofowora, Abayomi. Medicinal Plants and Traditional Medicine in Africa New York: John Wiley and Sons Ltd, 1982.

Steiner, Richard (ed). Folk Medicine: The Art and the Science. Washington DC: Maple Press Company, 1986.

Taye Bekele. "Inidiginoue Knowledge of Medicinal Plants: Perspectives of the Ethiopian Orthodox Church." In Mersha Alhegne, and et al (eds). The EthiopianChurch Yesterday, Today and Tomorrow. EOTC-Mahibere Kidusan: Proceeding of the Workshop, April18-11,2002.

Urga K, Assefa. A, and Guta M. (eds). Traditional Medicine in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa, 2004.

Waldram, B. James. "The Efficacy of Traditional Medicine: Current Theoretical and Methodological issues." Medical Anthropology Quarterly: Blackwell Publishing on Behalf of the American Anthropological Association; New series, Vol.14, No 4 (2000): pp 603-625.

Watson, Wilbur (ed). Black folk Medicine: The Therapeutic Significance of Faith and Trust. USA: transaction Books, 1984.

WHO. Traditional Medicine Strategy 2002-2005. Geneva; Renata Kerr: Printed in France, May 2002.

________. Tools for Institutionalizing Traditional Medicine in Health Systems in the WHO African Region. WHO Regional Office for Africa Brazzaville: Brazzaville Ltd, 2004.

Wondwoson Teshome. "Indigenous Medicinal Plants Used in Ethiopia" Viennese Ethno medicine News Letter; vol.9,No.2(1999):PP.28-32.

________. Medical Pluralism in Ethiopia. German: Shaker Verlag GmbH, 2006.

Yilma Desta, and et al. "Traditional Medicine: Global and National Perspective." In Dawit Abeba (ed). Development and Utilization of Herbal Remedies in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research institute: Addis Ababa, (1996):PP.1-7.

Yoder, Don. "Folk Medicine" In Richard Dorson (ed). Folklore and Folk life; An Introduction. Chicago, London: University of Chicago Press, (1972): PP. 190-214.

Young, Allan Louis. Medical Beliefs and Practices of Begemder Amhara. Published PhD Dissertation in Philadelphia: University of Pensylvania, 1970.

Zerihun Doda. "Culture, Belief and Mental Illness Among The Zay" M.A Thesis, Department of Social Anthropology: A.A.U, 2001.

አባሪዎች፡-

አባሪ-1 የአውራና የንዑስ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | እድሜ | ፆታ | ወረዳ | ቀበሌ | ጎጥ | ሙያ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ | 84 | ወ | ግሼ | ራቤል | 02 ቀበሌ | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት የዜማ መምህር ናቸው፡፡ ጥበቡን ከአብነት መምህራን በወሎ ክፍለሃገር (አማራ ሳይንት ተድባበ ማሪያም፣ ዋድላ ደላንታ) እና በጎጃም (ሞጣ ቀራኒዮ ድማ ጊዮርጊስ) በመዘዋወር ለአስራ ሁለት ዓመታት ያህል ተምረዋል፡፡ በሙያው የ40 ዓመታት ልምድ አላቸው (አውራ መረጃ አቀባይ)፡፡ |
| 2 | መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ | 60 | ወ | ግሼ | ፈረስ ቤት | ጉበኛ | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት የቅኔ መምህር ናቸው፡፡ የባህል ህክምና ሙያውን ከአባታቸው፣ ከአብነት መምህራን፣ ከብራና የመድኃኒት አውደ ጥበብን በማንበብ ሙያውን አዳብረዋል፡፡ ሩብ ኔክታር በሚደርስ ማሳ ለመድኃኒት ግብዓት የሚያገለግሉ እፀዋትን አልምተዋል፡፡ በሙያው የ41 ዓመታት ተሞክሮ አላቸው (አውራ መረጃ አቀባይ)፡፡ |
| 3 | መሪ ጌታ/የኔታ/ ጌታቸር ሸዋንግዛው | 79 | ወ | ግሼ | ዳራት | ግንባርኛ | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት የቅኔ መምህር ናቸው፡፡ የባህል ህክምና ልምዱን ከመነኮሳት፣ ከገዳማትና ከአብነት ትምህርት ቤት ተምረዋል፡፡ ለአንዳንድ የቅኔ ተማሪዎቻቸው የባህል ህክምናን በማስተማርና በህክምና ቤታቸው በማሰራት የህክምና ጥበቡን እያስተማሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በሙያው የ18 ዓመታት ተሞክሮ አላቸው (አውራ መረጃ አቀባይ)፡፡ |
| 4 | የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ | 58 | ወ | ግሼ | ፈረስ ቤት | አባሎ በር | የባህል ህክምና ባለሙያ | የባህል ህክምና ጥበቡን ከአባታቸው፣ ከከንባታና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ በፓዌ ሰፈራ ጣቢያ አብረው በመኖር የህክምና ልምዱን ቀስመዋል፡፡ በህክምናው ዘርፍ ከ20 ዓመታት ያላነሰ ልምድ አላቸው (አውራ መረጃ አቀባይ)፡፡ |

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | እድሜ | ፆታ | ወረዳ | ቀበሌ | ጎጥ | ሙያ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ | 35 | ወ | ግሼ | ወጅት | ወጅት አንባ | የባህል ህክምና ባለሙያ | የባህል ህክምና ልምዱን ከአባታቸው በመውረስ፣ ባህላዊና ዘመናዊ የመድኃኒት አወደ ጥበብን በማንበብ፣ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ልምዱን እንዳዳበሩ ገልጸዋል። የውስጥ አካል በሽታዎችን በዋናነት ከእጅና ከእግር ነርቮች በመከታተል እንደሚለዩ ጠቁመዋል። በሙያው የ13 ዓመት ተሞክሮ አላቸው (አውራ መረጃ አቀባይ)። |
| 6 | መሪጌታ ኃይሉ ፍስሐ | 45 | ወ | ግሼ | ጎልታ መዘራ ዝር | ሽነት | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት የአቋቋም መምህር ናቸው። የህክምና ጥበቡን ከመነኮሳት፣ ከገዳማት፣ ከአብነት መምህራን በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር ተምረዋል። በሙያው የ12 ዓመት ልምድ አላቸው። |
| 7 | ደብተራ ጌታነህ ደበበ | 53 | ወ | ግሼ | ደል | አሾጌ | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት ደብተራ ናቸው። ጥበቡን ሙያው ካላቸው ግለሰቦች፣ ከቆሎ ትምህርት ቤት ተምራዋል። በዘርፉ ለ26 ዓመታት ያህል ሰርተዋል። |
| 8 | መሪጌታ ተሾመ ምንደሲል | 54 | ወ | ግሼ | ዳራት | ዳራት አቦ | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት መሪጌታ ናቸው። ሙያውን ከአባታቸው፣ ከገዳማትና የአብነት መምህራንን በመላካም ስነመግባር በመጠጋት አዳብረዋል። በህክምና ዘርፉ የ30 ዓመት ልምድ አላቸው። |
| 9 | መሪ ጌታ/የኔታ/ ዲበኩሉ አማረ | 43 | ወ | ግሼ | ደል | ደል ሚካኤል | የባህል ህክምና ባለሙያ | በቤተክህነት ትምህርት የቅኔ መምህር ሲሆኑ የህክምና ጥበቡን ከአብነት መምህራን፣ ከገዳማትና ከመነኮሳት እንደተማሩ ገልጸዋል። ለአስር አመታት ያህል በጎንደር፣ በጎጃም፣ በትግራይና በሱዳን በመዘዋወር የህክምና ልምዱን እንደቀሰሙ ጠቁመዋል። በሙያው ላይም ለ12 ዓመታት ያህል ሰርተዋል። |

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | እድሜ | ፆታ | ወረዳ | ቀበሌ | ጎጥ | ሙ.ያ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ደብተራ በየነ አበጋዝ | 56 | ወ | ግሼ | ጎልታ መዘራ ዝር | ሎል መንደር | የባህል ህክምና ባለሙ.ያ | በቤተክህነት ትምህርት ደብተራ ናቸው፡፡ ሙ.ያውን ከአባታቸው በመውረስና ከአብነት መምህራን መልካም ግንኙነት በመፍጠር ጥበቡን ተምረዋል፡፡ በሙ.ያው ለ17 ዓመታት ያህል ሰርተዋል፡፡ |
| 11 | መሪ ጌታ ጌታቸር ሙላቱ | 69 | ወ | ግሼ | ራቤል | 01 ቀበሌ | የባህል ህክምና ባለሙ.ያ | በቤተክህነት ትምህርት የአቋቋምና የዜማ መምህር ናቸው፡፡ የባህል ህክምና ልምዱን ከስጋ ዘመዶቻቸው፣ ከአብነት መምህራኖቻቸው እንደቀሰሙት አስረድተዋል፡፡ በዘረፍ የ28 ዓመታት ተሞክሮ አላቸው፡፡ |
| 12 | የጤና መኮንን ሐኪም ዘላለም ግርማ | 45 | ወ | ግሼ | ራቤል | 01 ቀበሌ | የዘመናዊ ህክምና ባለቡ.ያ | በዘመናዊ ህክምና የጤና መኮንን ደረጃ አላቸው፡፡ በህክምና ዘርፉ ለ10 ዓመት አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ |
| 13 | ሐኪም ማሞ ተስፋዬ | 38 | ወ | ግሼ | ራቤል | 01 ቀበሌ | የዘመናዊ ህክምና ባለሙ.ያ | በዘመናዊ ህክምና የማህጸንና የህፃናት እንክብካቤ የቡድን መሪ ናቸው፡፡ በሙ.ያው የ11 ዓመታት የስራ ልምድ አላቸው፡፡ |

በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማህተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ

አባሪ- 2. የአውራ መረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ



መሪ ጌታ መስፍን ገብሬ



መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ



መሪ ጌታ(የኔታ) ጌታቸር ሸዋንግዛው



የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይና



የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ

አባሪ-3 የመረጃ አቀባይ ታካሚዎች ዳራዊ መግለጫ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባይ ስም | እድሜ | ፆታ | ሃይማኖት | የጋብቻ ሁኔታ | ቀበሌ | ጎጥ | መረጃ የተሰበሰበበት እለት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ በየነ ተገኝ | 64 | ወ | ኦርቶዶክስ | ባለትዳር | ፈረስ ቤት | ጉብኛ | 19/8/2003ዓ.ም |
| 2 | አቶ ሉሌ ዘገየ | 38 | ወ | ኦርቶዶክስ | ባለትዳር | ጎልታ | አባውጦ | 27/8/2003ዓ.ም |
| 3 | ወ/ሮ ታደለች አያሌው | 29 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ባለትዳር | ፈረስ ቤት | አባሎ በር | 20/8/2003ዓ.ም |
| 4 | ወ/ሮ ታደለች ሽመልስ | 42 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ባለትዳር | ዳራት | ዳራት አቦ | 18/8/2003ዓ.ም |
| 5 | አቶ ሞገስ አብይ | 43 | ወ | ኦርቶዶክስ | ባለትዳር | ጎልታ | ክትክቴ | 27/8/2003ዓ.ም |

አባሪ-4 የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደት መግለጫ

የበሽታ ዓይነትን፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የበሽታው ዓይነት | ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት እንስሳት፣ ማዕድናትና ነፍሳት | ለመድኃኒት የሚውለው የእፀዋት ክፍል፣ የእንስሳት አካል፣ የማዕድናት እና የነፍሳት አይነት | የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለራስ ምታት | ጎርጠብና ቃጫ | ቅርፊትና ስሩ | የጎርጠብ ቅርፊትና የቃጫ ሥሩን አድርቆና ወቅጦ ዱቄቱን በንጹህ ጨርቅ አስሮ በአፍንጫ መሳብ |
| 2 | ለፎረፎር | አፀፋሪስና ጌሾ | ቅጠልና ፍሬው | የአጸ ፋሪስና የጌሾ ቅጠልና ፍሬ አድርቆና ወቅጦ በለጋ ቅቤ ለውሶ መቀባት |
| 3 | ለጆሮ መግል | አሜኬላና እፀዮዲት | ወተትና ስሩ | የአሜኬላ ወተትና የእፀዮዲት ስር ዘፍዝሮ፣ አንጥሮና አጥሎ ሁለት ጠብት መጨመር |
| 4 | ለዳፍንት | ምስርና አጣጥ | አበባና ቅጠሉ | የምስር አበባና የአጣጥ ቅጠል ቀቅሎና አጥሎ ማታ ማታ አንድ ጠብታ አድርጎ መተኛት |
| 5 | ለዓይን ጥራኮማ | ክትክታ | ስሩ | የክትክታ ስሩን በምጣድ አሳርሮ ክሰሉን ደቁሶ እንደ ኩል መኳል |
| 6 | ለአፍንጫ ቁስል | ብሳና እና እፀሜሮን | ስራቸው | የብሳና እና የእፀሜሮን ስር አድርቆና ወቅጦ በማር ለውሶ መቀባት |
| 7 | ለአፍንጫ ነስር | አረንጭ | ስርና ቅርፊቱ | የአረንጭ ስርና ቅርፊት ወቅጦ በማር ለውሶ አፍንጫን መቀባትና በጨርቅ አስሮ መማግ |
| 8 | ለድድ ድማት | አሽከት | ፍሬው | የአሽከት ፍሬውን አድርቆና ወቅጦ በሚደማው በኩል ዱቄቱን መደምደም |
| 9 | ለብጉር | አመራሮና አሞጭ | ፍሬና ስሩ | የአመራሮና የአሞጭ ፍሬና ስር ወቅጦ ዱቄቱን በማር ለውሶ በዶሮ ላባ መቀባት |
| 10 | ለጥርስ ሕመም | ውልክፋ | ስሩ | የውልክፋ ስሩን አድርቆና ወቅጦ በማር ለውሶ መቀባትና መጉመጥመጥ |
| 11 | ለአንጥል መውረድ | ጌሾና ሚጥሽ | ቅጠል፣ ስርና ቅርፊት | የጌሾና የሚጥሽ ቅርፍት፣ ስርና ቅጠል በአንድ ላይ አፍልቶና አጥሎ እንደ የሾርባ ማንኪያ ውሃ ማጠጣት |

| ተ.ቁ | የበሽታው ዓይነት | ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት እንስሳት፣ ማዕድናትና ነፍሳት | ለመድኃኒት የሚውለው የእፀዋት ክፍል፣ የእንስሳት አካል፣ የማዕድናት እና የነፍሳት አይነት | የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ |
|---|---|---|---|---|
| 12 | ለከርክር | ወገርትና ችፍርግ | ስራቸው | የወገርትና የችፍርግ ስር በአንድ ላይ ወቅጦ ዱቄቱን ከእማምሳይ ላም ቅቤ ጋር አዋህዶ መቀባት |
| 13 | ቂጥኝ | አጋም፣ ሰንሰልና የእምድር እንቧይ | ስራቸው | የአጋም፣ የሰንሰልና የእምድር እንቧይ ስር ወቅጦ መዘፍዘፍ፤ በማግስቱ አፍልቶና አጥሎ አንድ ሾርባ ማንኪይ ፈሳሽ ከአንድ ስኒ ማር ጋር ለውሶ ማጠጣት |
| 14 | ለሳንባ ነቀርሳ | ለንቋጣና ሰንሰል | ስራቸው | የለንቋጣና የሰንሰል ሥርቸውን ወቅጦ ከእንቁላል አስኳል ጋር አደባልቆ ማጠጣት |
| 15 | ለወንዴ ኪንታሮት | አብላሊት፣በለስና ብሳና | ስራቸው | የአብላሊት፣ የበለስና የብሳና ስራቸውን ዘፍዝፎ፣ አድርቆና ወቅጦ በጣዝማ ማር አዋህዶ በየሁለት ቀኑ እያፀዱ መቀባት |
| 16 | ለሴንጥጣ ኪንታሮት | ገመሮ፣ አሜራና ምስርች | ቅጠልና ስርቸው | የገመሮ፣ የአሜራና የምስርች ቅጠልና ቅርፊት አድርቆና ወቅጦ፤ ዱቄቱን በጣዝማማር ለውሶ በየሁለት ቀኑ እያፀዱ መቀባት |
| 17 | ለተቀማጥ | እንቆቆና ብሳና | ፍሬያቸው | የእንቆቆና ብሳና ፍሬ አድርቆና ወቅጦ ከኑግ ጥፍጥፍ ጋር ለውሶ ማብላት |
| 18 | ለአሜባ | አባሎና ሰንሰል | ስርቸው | የአባሎና የሰንሰል ስራቸውን ወቅጦ አንድ መንኪያ ዱቄት ከአንድስኒ ማርጋር ለውሶ ማጠጣተ |
| 19 | ለጉስምት | ጦስኝና ዝንጅብል | ቅጠልና ፊሬያቸው | የጦስኝና የዝንጅብል ቅጠልና ፍሬ ወቅጦ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንደ ስኒ ወለላ ማር ጋር ለውሶ ማጠጣት |
| 20 | ለወስፋት | አዛምር፣ ጠንበለልና ወገርት | ስራቸው | የአዛምር፣ የጠንበለልና የወገርት ስር አድርቆና ወቅጦ አንድ መንኪያ ዱቄት ከኑግ ጥፍጥፍ ጋር ደባልቆ በባዶ ሆድ ማብላት |
| 21 | ለስራይ | ቁንዶ በርበሬና መካን እንዶድ | ስራቸው | የቁንዶ በርበሬና የመካን እንዶድ ስራቸውን አድርቆና ሰልቆ አንድ ማንኪያ ዱቄት አበንድ ሽክና ጠላ ማጠጣት |
| 22 | ለእንገዴ ለጅ ማሶረጃ | ድግጣና እፀሄናክ | ስራቸው | የድግጣና የእፀሄናክ ስራቸውን አድርቆና ወቅጦ አንድ መንኪያ ዱቄት ከአንድ ብርጭቆ የሱፍ ውሃ ጋር ደባልቆ ማጠጣት |
| 23 | ለጡት | የምድር እንቧይና | ፍሬያቸው | የምድር እንቧይና የድግጣ ፍሬያቸውን ወቅጦ በማር ለውሶ መቀባት |

| | ህመም | ድግጣ | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የበሽታው ዓይነት | ለመድኃኒት የሚያገለግሉ እፀዋት እንስሳት፣ ማዕድናትና ነፍሳት | ለመድኃኒት የሚውለው የእፀዋት ክፍል፣ የእንስሳት አካል፣ የማዕድናት እና የነፍሳት አይነት | የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ |
| 24 | ለጉስምት | ጭቁኝና ጦስኝ | ቅጠልና ስራቸው | የጭቁኝ ስርና የጦስኝ ቅጠል አድርቆና ሰልቆ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ ማር ጋር ለውሶ ማጠጣት |
| 25 | ለውጋት | ችፍርግና አጣጥ | ስራቸው | የችፍርግና የአጣጥ ስራቸውን ወቅጦ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንድሌትር ውሃ ጋር አፍልቶ ጧት ጧት አንድ ስኒ ማጠጣት |
| 26 | ለደም ብዛት | አቱችና ወርቅ በሜዳ | ስራቸው | የአቱችና የወርቅ በሜዳ ስራቸውን አድርቆና ወቅጦ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ብርጭቆ ውሃ ጋር ቀላቅሎ ማጠጣት |
| 27 | ለቁርጥማት | ፍየለፌጅ | ፍሬ፣ ቅርፊትና ስር | የፍየለፌጅ ፍሬ፣ ቅርፊትና ስሩን ወቅጦና ሰልቆ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከኑግ ጋር በጠብጦ አንድ አንድ ብርጭቆ ጧት ጧት ማጠጣት |
| 28 | ለትውከት | ጠንበለልና ድግጣ | ስር፣ ፍሬና አበባው | የጠንበለል አበባና የድግጣ ስርና ፍሬውን ወቅጦ በማር ለውሶ ማብላት |
| 29 | ለወባ | የፈረስ ዘንፍና ሰንሰል | ፍሬና ስር | የፈረስ ዘንግ ፍሬና የሰንሰል ስሩን አድርቆና ወቅጦ አንድ ማንኪያ ዱቅት ከአንድ ብርጭቆ ውሃ ጋር አዋህዶ ጧትና ማታ ማጠጣት |
| 30 | ለሾተላይ | ጥንገፉትና ሎሚ | ተቀፅላቸው | የጥንገፉትና የሎሚ ተቀፅላቸውን አድርቆና ወቅጦ በወለላ ማር አድበልብሎ በየወሩ አንድ እንክብል መዋጥ |
| 31 | ለሚደነግጥ ህፃን | ፍየለፌጅና አጋም | ስራቸው | የፍየለፌጅና የአጋም ስር አድርቆና ወቅጦ አንድ ማንኪያ ዱቄት ከአንድ ስኒ ማር ጋር ለውሶ በባዶ ሆድ ጧት ጧት ማጠጣት |
| 32 | ለእጅ ሰብ | ፌጦ፣ ችፍርግና አጋም | ስራቸው | የፌጦ፣ የችፍርግና የአጋም ስራቸውን ወቅጦ ከድኝ ቀላቅሎ በእማምሳይ ላያ ቅቤ ለውሶ ራሱን መቀባትና ማጠን |
| 33 | ለእባብ ንድፍት | ቀበርቾ ፣ ሮማንና ጥድ | ስርና ሙጫ | የጥድ ሙጫ፣ የቀበርቾና የሮማን ስራቸውን ወቅጦ በአልቴት ለውሶና ከሙጫው ጋር ደባልቆ በተነደፈው ቦታ ላይ መቀባትና ማሰር |
| 34 | ለድግምት | ጅብ እንስሳት | የግራ ቅንድቡ | የጅብ የግራ ቅንድቡን በክታብ መልክ አሰርቶ መያዝ ድግምትን ያፈርሳል |
| 35 | ለቡዳ | ዲኚ ማዕድን | ለቡዳ መዳኒት | ዲኚን ከአልቴት፣ ከጤናዳም፣ከጦስኝ፣ ከድንብላል አዋህዶ በመቀመም በንፁህ ጨርቅ ጠቅልሎ ማሽተትና በጭሱ መታጠን |
| 36 | ለቁስል | ነብር እንስሳት | ደሙ | የነብር ደሙን ከድንብላል ዱቄት ጋር በማዋሃድ ቁስሉን መቀባት |

አባሪ-5 በግሼ ወረዳ የሚገኙ የባህል ሐከሞችን ምርጫ መሰረት በማድረግ በቅደም ተከተል የተሰደሩ በሽታዎች

ሀ/ በባህል ህክምና ጎልተው የሚታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ (Top Ten Diseases) አይነቶች፤ እንደ የባህል ሐኪሞቹ ምርጫ

| ተ.ቁ | መሪ ጌታ በስፍን ገብሬ | የባህል ሐኪም ጌታነህ ታደሰ | መሪ ጌታ ካሳ መንገሻ | መሪ ጌታ/የኔታ/ ጌታቸር ሽዋንግዛው | የባህል ሐኪም ታለእግዜር ይናዱ | መሪ ጌታ/የኔታ/ ዲበኩሉ አማረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለወፍ | ለነቀርሳ | ለእንጥል | ለወፍ | ለብርድ በሽታ | ለኪንታሮት |
| 2 | ለኪንታሮት | ለጨብጥ | ለኪንታሮት | ለሚጥል በሽታ | አልማዝ ባለጭራ | ለስኳር |
| 3 | ለኮሶ | ለችፌ | ለወስፋት | ለህፃናት ለቅሶና ቅዥት | ለእባጭ | ለአውድቅ |
| 4 | ለወስፋት | ለቁንጣጭ | ቡዳ ለበላው | ለእጀ ሰብ | ለአጥንት ስብራት | ለወፍ |
| 5 | ለጆሮ መግል | ለገስጋሽ | ለጨንራ | ለጨብጥ | ለጭርት | ለነቀርሳ |
| 6 | ለነቀርሳ | ለወፍ | ለኮሶ | ለእንግዴ ልጅ ማስወረጃ | ደም ወደ ውስጥ ለፈሰሰው | ለብጉር |
| 7 | ለእብድ ውሻ በሽታ | ለአልማዝ ባለጭራ | ለስንፈተ ወሲብ | ለኮሶ | ለስኳር በሽታ | ለፎረፎር ና ቆረቆር |
| 8 | ለእንጥል | ለኮሶ | ለአንጀት መታጠፍ | ለጭርት | ለጆሮ መግል | ለወስፋት |
| 9 | ለሚጥል በሽታ | ለቋቁቻ | ለእብድ ውሻ በሽታ | ለአልማዝ ባለጭራ | ቡዳ ለወረደው | ለእብድ ውሻ በሽታ |
| 10 | ለስኳር | ለወባ | ለወፍ | ለስኳር በሽት | ለወፍ | ለጨብጥ |

በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማህተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ

ለ/ በባህል ህክምና ጎልተው የሚታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ (Top Ten Diseases) አይነቶች፤ እንደ ባህል ሐኪሞቹ ምርጫ

| ተ.ቁ | መሪ ጌታ ኃይሉ ፍስሐ | መሪ ጌታ ተሾመ ጌታቸው | መሪ ጌታ ጌታቸር ሙላቱ | ደብተራ በየነ አበጋዝ | ደብተራ ጌታነህ ደበበ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኮሶ ለተጣባው | ለእንጥል | ለልብ ህመም | ለወፍ | ለማዲያት |
| 2 | ለእከክ | ለልጆች ቅዥቶችና ለቅሶ | ለብርድ በሽታ | ለኮሶ | ለወፍ |
| 3 | ለወፍ | ለመፍትሄ ስራይ | ለቆረቆር | ለሾተላይ | ለጥርስ ህመም |
| 4 | ለመጋኛ | ለጭርት ለኮሶ | ለእባጭ | ለጨጓራ ህመም | ለጨጓራ ህመም |
| 5 | ለእንጥል | ለኮሶ | እንግዴ ልጅ ለሚቀይባት | ለጭርት | ለሚጥል በሽታ |
| 6 | ለነቀርሳ | ለአልማዝ ባለጭራ | ለጆሮ ህመም | ለብርድ | ለእከክ |
| 7 | ለወር አበባ መዛባት | ለልክፍት | ለአፍ ውስጥ ጠረን | ለቆረቆር | ለራስ ምታት |
| 8 | ለስኳር በሽታ | ለእብድ ውሻ በሽታ | ለሚጥል በሽታ | ለኪንታሮት | ለአሜባ |
| 9 | ለወሲብ ችግር | ለራስ ምታት | ለእንጥል | ለወባ | ለፎረፎር |
| 10 | ለጨጓራ ህመም | ለደም ብዛት | ለወር አበባ መዛባት | ለራስ ምታት | ለደም ብዛት |

በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማህተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ

አባሪ-6 በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት በ2001 እና 2002 ዓ.ም ጎልተው የታዩ በሽታዎች ዝርዝር

ከአስራ አራቱ አስሩን በቅደም ተከተል በመጥቀስ የቀረበ መረጃ

ሀ/ በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በ2001ዓ.ም ጎልተው የታዩ አስር ዋና ዋና የበሽታ (Top Ten Diseases) አይነቶች

| ተ.ቁ | የበሽታው አይነት | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በቁጥር | ጎልተው የታዩ በሽታዎች በፐርሰንት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ተለይቶ ያልታወቀ ትኩሳት | 468 | 19 | |
| 2 | አሜባ | 317 | 12.9 | |
| 3 | የላይኛው መተንፈሻ አካል በሽታ | 273 | 11.1 | |
| 4 | ቁርጥማት | 261 | 10.6 | |
| 5 | የጨጓራ ህመም | 243 | 9.9 | |
| 6 | የቆዳላይ ቁስሎች | 158 | 6.4 | |
| 7 | በአደጋ የደረሰ ጉዳት | 157 | 6.4 | |
| 8 | ቶንሲል | 114 | 4.6 | |
| 9 | ሌሎች የመተንፈሻ አካል | 103 | 4.2 | |
| 10 | የሆድ ጥገኛ ታላትል /ወስፋት/ | 99 | 4 | |

በግሼ ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማህተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ

አባሪ-7 በግሼ ወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ የባህል መድኃኒት አዋቂዎች፣ ወጌሻዎች፣ የልምድ አዋላጆችና የፀበል ቦታዎች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | ቀበሌ | ጎጥ | የባህል መድኃኒት አቃቂ | ወጌሻ | የልምድ ደዋላጅ | የፀበል ቦታ | የመረጃ ሰባሳቢው ስምና አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ዘነበች ታደሰ | ራቤል | 02 | | | ✓ | | ወ/ሮ<br>ፀሐይ ተሾመ<br>አድራሻ፡-ራቤል ከተማ<br>እድሜ፡-47 |
| 2 | ወ/ሮ ፀሐይ ተሾመ | ራቤል | 01 | | | ✓ | | |
| 3 | ወ/ሮ ታደለች ታደሰ | ራቤል | 01 | | | ✓ | | |
| 4 | አቶ ደበበ ተሰማ | ራቤል | 02 | ✓ | | | | |
| 5 | አቡነ አረጋይ ፀበል | ወፍለቅ | ሆሎተገን | | | | ✓ | |
| 6 | ጊዮርጊስ ፀበል | ወፍለቅ | ለምጨቅ | | | | ✓ | አቶ አጥላው ጣሴ<br>አድራሻ፡-ወፍ ለቅ<br>ታች አንባ ጎጥ<br>እድሜ፡-51 |
| 7 | አቶ ስለሺ ኪዳነ ማሪያም | ወፍለቅ | ሆሎተገን | | ✓ | | | |
| 8 | ወ/ሮ እናኒ ቸሬ | ወፍለቅ | ጤፍ ሜዳ | | | ✓ | | |
| 9 | አቶ አጥላው ጣሴ | ወፍለቅ | ታች አንባ | ✓ | | | | |
| 10 | መሪ ጌታ እሸቱ ተሸመ | ወፍለቅ | ሰላድንጋይ | ✓ | | | | |
| 11 | አቶ አራጋው ተገኝ | ወፍለቅ | ዋዲያት | | ✓ | | | |
| 12 | አቶ ምታው ግዛው | ወፍለቅ | መልሓምባ | | ✓ | | | |
| 13 | አቦ ፀበላ | ወፍለቅ | ግም ውሃ | | | | ✓ | |
| 14 | አቶ አበራ ደመቀ | ወፍለቅ | ይቴም | | ✓ | | | |
| 15 | አቶ በላይሁን ታደሰ | ጎልታ | መስቀል ዋሻ | ✓ | | | | አቶ ፀጋው በየነ<br>አድራሻ ጎልታ<br>እድሜ፡-30 |
| 16 | አቶ ክብረት ግዛው | ጎልታ | ሸነት | ✓ | | | | |
| 17 | ወ/ሮ በላይነሽ ጥላሁን | ጎልታ | መስከረት | | | ✓ | | |
| 18 | ወ/ሮ ሸወንዜ ተሰማ | ጎልታ | መስቀል ዋሻ | | | ✓ | | |
| 19 | አቶ አራጌ መንገሻ | ጎልታ | አለኔ | ✓ | | | | |
| 20 | አቶ ቸሩ ገላግሌ | ጎልታ | ሸነት | | ✓ | | | |
| 21 | ጊዮርጊስ ፀበል | ጎልታ | መስከረት | | | | ✓ | |
| 22 | አማኑኤል ፀበል | ጎልታ | አማኑኤል | | | | ✓ | |
| 23 | አቦ ፀበል | ጎልታ | ጤፍ ሜዳ | | | | ✓ | |

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | ቀበሌ | ጎጥ | የባህል መድኃኒት አቃቂ | ወጌሻ | የልምድ ደዋላጅ | የፀበል ቦታ | የመረጃ ሰባሳቢው ስምና አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | አቶ መኩሪያ ገብረማሪያም | ዳራት | አንቃፊት | | | ✓ | | አቶ መኩሪያ ገ/ማሪያም አድራሻ:-ዳራት እድሜ:-39 |
| 25 | ወ/ሮ ማሚቴ ዳምጠው | ዳራት | እቡስ ቀራ | | | ✓ | | |
| 26 | መድኃኒአለም ፀበል | ዳራት | አረያ ገደል | | | | ✓ | |
| 27 | አቦ ፀበል | ዳራት | በር | | | | ✓ | |
| 28 | አቶ ወርቅነህ አለልኝ | ዳራት | ኮሎ ተገን | | ✓ | | | |
| 29 | አቶ ገዛኸኝ ጥእዛዙ | ዳራት | አጋም በር | ✓ | | | | |
| 30 | መሪ ጌታ ዘነበ እጅጉ | ዳራት | መድፈረስ ሜዳ | /መፀሐፍ ገላጭ/ | | | | |
| 31 | አቶ አያሌው መታፈሪያ | ደል | መትከል | ✓ | | | | አቶ ተስፋዬ አበበ አድራሻ:-ደል ጎጥ:-ሻመን እድሜ:-43 |
| 32 | አማኑኤል ፀበል | ደል | ቀይ አንባ | | | | ✓ | |
| 33 | አንቻ ጊዮርጊስ | ደል | ቸንቻ | | | | ✓ | |
| 34 | ወ/ሮ አልማዝ እጅጉ | ደል | ቀይ አንባ | | | ✓ | | |
| 35 | ወ/ሮ ብርቂ ጥላሁን | ደል | ቀይ አንባ | | ✓ | ✓ | | |
| 36 | ወ/ሮ ታደለች ሽፈራው | ደል | ቀይ አንባ | | | ✓ | | |
| 37 | አቶ ጌትነት ደበበ | ደል | ሻመን | ✓ | | | | |
| 38 | አቶ አለልኝ ካሳዬ | ደል | ሻመን | | ✓ | | | |
| 39 | ሚካኤል ፀበል | ደል | ሻመን | | | | ✓ | |
| 40 | ወ/ሮ እቴነሽ ዳምጠው | ደል | ደልሚካኤል | | ✓ | | | |
| 41 | አቶ ለማ ካሳዬ | ግራር አንባ | በን | | ✓ | | | |
| 42 | አቶ ኃይሉ ደሳለኝ | ግራር አንባ | በን | | ✓ | ✓ | | |
| 43 | አቦ ፀበል | ግራር አንባ | ሾላበር | | | | ✓ | |
| 44 | ሚካኤል ፀበል | ግራር አንባ | ሾላበር | | | | ✓ | |

| ተ.ቁ | ስም ዝርዝር | ቀበሌ | ጎጥ | የባህል መድኃኒት አቃቂ | ወጌሻ | የልምድ ደዋላጅ | የፀበል ቦታ | የመረጃ ሰባሳቢው ስምና አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 45 | አቶ አበባው ሃብቴ | ግራር አንባ | ክምር ድንጋይ | | ✓ | | | መሪጌታ አድገህ አስፋው አድራሻ፡-ፈረስቤት እድሜ፡-47 |
| 46 | መሪ ጌታ አድገህ አስፋው | ፈረስ ቤት | ፈረስቤት | መፀሐፍ ገላጭ | | | | |
| 47 | አቶ ስለሺ ኪ/ማሪያም | ፈረስ ቤት | ጎበኛ | | ✓ | | | |
| 48 | ሚካኤል ፀበል | ፈረስ ቤት | ጎበኛ | | | | ✓ | |
| 49 | አቦ ፀበል | ፈረስ ቤት | ፏፏቴ | | | | ✓ | |
| 50 | ወ/ሮ ተናኜ ግርማ | ፈረስ ቤት | አባሎ በር | | | ✓ | | |
| 51 | ወ/ሮ በቀሉ ሽዋታጠቅ | ፈረስ ቤት | ፈረስ ሜዳ | | | ✓ | | |

በግሺ ወረዳ ጤና ጥበቃ ዋና ጽ/ቤት ከተረገጠ ማህተም ሰነድ ጋር የተመሳከረ መረጃ

# <u>ማረጋገጫ</u>

ይህ ጥናት የእኔ ወጥ ሥራ (Original work) መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም፡-..ተመስገን በየና..........

ፊርማ፡-......................

ማስረከቢያ ቀን፡-...07/11/03 ዓ.ም..